# አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች (Arlington Public Schools)

## የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የጥናቶች ፕሮግራም

## 2021-2022

**GUNSTON**
**መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**
2700 South Lang Street
Arlington, VA 22206
(703) 228-6900

**KENMORE**
**መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**
200 South Carlin Springs Road
Arlington, VA 22204
(703) 228-6800

**DOROTHY HAMM**
**መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**
4100 Vacation Lane
Arlington, VA 22207
(703)228-2117

**SWANSON**
**መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**
5800 North Washington Blvd.
Arlington, VA 22205
(703) 228-5500

**THOMAS JEFFERSON**
**መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**
125 South Old Glebe Road
Arlington, VA 22204
(703) 228-5900

**WILLIAMSBURG**
**መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**
3600 North Harrison Street
Arlington, VA 22207
(703)228-2117

የመካከለኛ ደረጃ ት / ቤት የጥናት ፕሮግራም በእንግሊዝኛ ጽ / ቤቶች በሁሉም የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይገኛል ወይም ድር ጣቢያው ላይ: www.apsva.us

برنامج الدراسات للمدرسة المتوسطة متاح أيضًا باللغة الإنجليزية في مكاتب التوجيه في جميع مدارس Arlington العامة أو على الموقع الإلكتروني: www.apsva.us

Дунд сургуулийн сургалтын хөтөлбөрийг Арлингтон хотын бүх сургуулиудын холбогдох байгууллагуудаас англи хэл дээр авах боломжтой буюу энэ вэбсайтаар орж авна уу: www.apsva.us

*The Middle School Program of Studies is also available in English in guidance offices at all Arlington Public Schools or on the website:* www.apsva.us

**የአርሊንግተን የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የጥናቶች ፕሮግራም**
**ማውጫ**


የማስተማርና መማር ረዳት ዋና ተቆጣጣሪ የሆኑት Bridget Loft ያስተላለፉት መልዕክት ..... 3
መቅድም ..... 5
የዓላማ መግለጫ ..... 5
አእምሯዊ ዕድገት ..... 5
መሰረታዊ ስርዓተ-ትምህርት ..... 5
የአሰሳ/አስገዳጅነት የሌላቸው ትምህርቶች ፕሮግራም ..... 6
አክት II ..... 6
ልዩነት ማድረጊያ መመሪያዎች ..... 6
ፈታኝ ለሆኑ ኮርሶች መዘጋጀት ..... 8
በቅድሚያ የሚያስፈልጉ ልዩ ሁኔታዎች ..... 8
የጥናቱ ትምህርታዊ መስኮች ..... 8
  6ኛ ክፍል መሰረታዊ ስርዓተ ትምህርት ..... 10
  7ኛ ክፍል መሰረታዊ ስርዓተ ትምህርት ..... 16
  8ኛ ክፍል መሰረታዊ ስርዓተ ትምህርት ..... 24
ተጨማሪ ኮርሶች/ፕሮግራሞች ..... 36
  Gunston መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ..... 36
    የስፓኒሽ ባለ ሁለት ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም እና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ሞንቴሶሪ ፕሮግራም ..... 36
  Thomas Jefferson መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ..... 38
    ዓለም አቀፍ የባካሎሪያ መካከለኛ ዓመታት ፕሮግራም ..... 38
Kenmore መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ..... 40
    የጥበባት እና የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ላይ ያተኮረ ፕሮግራም ..... 40
  Swanson መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ..... 44
ልዩ ሕዝቦች ..... 45
  የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች ..... 45
  የእንግሊዝኛ ተማሪ (EL) አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች ..... 45
  ስጦታ ያላቸው አገልግሎቶች ..... 45
የቤተ መጻሕፍት አገልግሎቶች ..... 46
ከስርዓተ-ትምህርቱ ውጭ ያለ የአትሌቲክስ ፕሮግራም ..... 46
የማሕበረ-ስሜታዊ ዕድገት ..... 46
የመምህር አማካሪ ፕሮግራም ..... 47
የተማሪዎች አገልግሎቶችና ልዩ ትምህርት ..... 47
የቤት ውስጥ ትምህርት ..... 47
የተማሪዎች ተግባራት ..... 48
የቤት/ትምህርት ቤት ትብብር እና ግንኙነት ..... 48
በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ያለ ደረጃውን የጠበቀ ፈተና አሰጣጥ ..... 48
በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የሚያስገኙ ኮርሶች ..... 48
የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አማራጮች ..... 49
የሚጠቆሙ የ APS መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሒሳብ ትምህርት መስመሮች ..... 51
የዓለም ቋንቋዎች የጥናት ቅደም ተከተል ..... 53
የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመመረቂያ መስፈርቶች ..... 55

ጃንዋሪ 2021

ውድ የአርሊንግተን ቤተሰቦች፡-

ወደ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እንኳን በደህና መጣችሁ! በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሚወስዷቸውን ኮርሶች ቅደም ተከተል በሚያቅዱበት ወቅት ይህን ሰነድ እንደ ማጣቀሻና መምሪያ ይጠቀሙበታል የሚል ተስፋ አለን። የጥናቶች ፕሮግራም በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ስለሚሰጡ ስርዓተ ትምህርታዊ ዝግጅቶችና ትምህርቶች አጠቃላይና ውስን መረጃን ለተማሪዎችና ለወላጆች ይሰጣል። ግልጽና አጠር ማድረግን ለማሳካት በምናደርገው ጥረት፣ ከ APS መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች በርካታ ዋና ዋና ጉዳዮች ግልጽና ተጨባጭ መግለጫዎችን ጽፈናል። አብዛኞቹን አርእርስት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤትዎ የማማከር አገልግሎቶች ጽ/ቤት ስልክ መደወል ይችላሉ፡-

| | |
|---|---|
| Dorothy Hamm መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 703/ 228 - 2910 |
| Gunston መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 703/ 228 - 6909 |
| Jefferson መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 703/ 228 - 5908 |
| Kenmore መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 703/ 228 - 6798 |
| Swanson መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 703/ 228 - 5508 |
| Williamsburg መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 703/ 228 - 5445 |

ተማሪዎች ፍላጎታቸውን ለማሳካት ሲጓዙና ተሞክሮዎቻቸውን ሲያሰፉ በርካታ አማራጮች ይኖራቸዋል። ተማሪው፣ ወላጆችና አማካሪው የሶስት ዓመት የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ቆይታን ለማቀድና በሒደትም አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችን ለማድረግ በጋራ መስራት አለባቸው። የእርስዎ ውሳኔ አሰጣጥ መመራት ያለበት በተማሪው የረዥም ጊዜ ግቦችና ፍላጎቶች፣ እንደዚሁም ለምረቃ በሚያስፈልጉ ሁኔታዎች መሰረት ነው። የ2021-22 የጥናቶች ፕሮግራም ዕቅድ የማውጣትና ወደፊት የማየት ሒደትን ይደግፋል። በተጨማሪም፣ ከት/ቤትዎ የማማከር አገልግሎቶች ጽ/ቤቶች ጋር ትብብር ማድረግ ለልጅዎ የሚቀርቡ ሌሎች በርካታ ድጋፎችን ለመለየት ያግዛል።

አብዛኞቹ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአትኩሮት ፕሮግራሞችንም የሚሰጡ ሲሆን እነርሱም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተማሪዎቻቸውን የተለያዩ ፍላጎቶች ለማሟላት የተከተሏቸውን ለየት ያሉ አቅጣጫዎች የሚያንጸባርቁ ናቸው። ሌሎቹ ኮርሶች በሙሉ የሚሰጡት በአምስቱም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ነው።

በአጠቃላይ ገለጻ፣ ወደ ት/ቤት በመመለሻ ምሽት እና በሌሎች ፕሮግራም በተያዘላቸው አጋጣሚዎች አማካይነት ከት/ቤትዎ ጋር ያለዎትን ግንኙነት እንዲያስቀጥሉ እናበረታታዎታለን። ለልጅዎ አማካሪ ስልክ በመደወል የብቃዎት ቀጠሮ እንዲያዝልዎት ማድረግም ይችላሉ።

በልጅዎ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ቆይታ ወቅት የሚቀርቡልዎትን በርካታ አጋጣሚዎች ይጠቀማሉ የሚል ተስፋ አለን።

ከልባዊ ሰላምታ ጋር፣

Bridget Loft
የማስተማርና መማር ትምህርት ክፍል፣ ረዳት ዋና ተቆጣጣሪ

## የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የጥናቶች ፕሮግራም

### መቅድም

በአርሊንግተን ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የእያንዳንዱን ልጅ አእምሯዊ፣ አካላዊ፣ ማሕበራዊ እና ስሜታዊ ዕድገትን ለማጎልበት በሚያስችል ሁኔታ የተደራጀ ነው። መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች በእነዚህ መስኮች ለ6ኛ፣ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚያቀርቧቸውን የአካዳሚክ ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶች እና ተግባራት በጥናቶች ፕሮግራም ውስጥ ተገልጸዋል።

ከአካባቢው መለኪያ መስፈርቶች በተጨማሪ፣ የቨርጂኒያ ግዛት የትምህርት ቦርድና የደቡባዊ ኮሌጆችና ት/ቤቶች ማህበር ጥራት ላለው ትምህርት መሰረት የመጣል ዓላማ ያላቸውን የዕውቅና አሰጣጥ መለኪያ መስፈርቶች አውጥተዋል። የዕውቅና አሰጣጥ መለኪያ መስፈርቶች ት/ቤቶች የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎቶች፣ ጥቅሞችና የወደፊት ምኞቶች የሚያሳኩ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ለማቅረብ በሚያደርጓቸው ቀጣይነት ያላቸው ጥረቶች ላይ አመራርና አቅጣጫን ይሰጣሉ። የዕውቅና አሰጣጥ መለኪያ መስፈርቶች የተቀረጹት የሚከተሉትን ዓላማዎች ለማሳካት ነው፡-

1. ት/ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት መስጠታቸውን ለማረጋገጥ።

2. የት/ቤት ፕሮግራም ላይ ተከታታይ ምዘና እና ማሻሻያ እንዲደረግ ለማበረታታት።

3. የሕዝቡን እምነት ለማጎልበት

4. በሌሎች የትምህርት ተቋማት ዘንድ እውቅና መገኘቱን ለማረጋገጥ።

### የዓላማ መግለጫ

የአርሊንግተን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ዕድሜያቸው ከአስር እስከ አስራ አራት ዓመት ለሆናቸው ታዳጊ ወጣቶች ተከታታይነት ያለው ትምህርት፣ ማሕበራዊ ዕድገትና አካላዊ ደህንነትን ለማረጋገጥ ልጆች ላይ ያተኮረ አቀራረብ መከተላቸውን ያረጋግጣሉ። መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቱ ከመምህራን፣ ሰራተኞች፣ ወላጆች፣ ማህበረሰብ እና ተማሪዎች በሚያገኘው የማያቋርጥ ድጋፍ አማካይነት ብዝሃነት ለሚንጸባረቅበት የተማሪ ማህበረሰብ የመቀበል፣ የመረዳትና የመከባበር ሁኔታን ይፈጥራል።

ከ6ኛ-8ኛ ክፍል ድረስ የሚያስተምሩ የአርሊንግተን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለታዳጊ ወጣቶች በአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መካከል በሚኖራቸው የሽግግር ዓመታት ውስጥ የሚማሩበትና የሚያድጉበትን ፍትሃዊ የመማሪያ አካባቢ ይፈጥሩላቸዋል። የስርዓት ትምህርቱና የሰራተኞች ማጎልበቻ ስራዎች ዋነኛ ትኩረት የሚሆነው የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አእምሯዊ፣ ማሕበራዊ፣ ስሜታዊና አካላዊ ዕድገት ነው። የተለያዩ ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራንን በቡድን ማደራጀት፣ እንደሁኔታው የሚቀያየር የብሎክ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት፣ የመምህራን አማካሪነት ፕሮግራሞች፣ አዳዲስ ነገሮችን የማሰስ አማራጮችና መጠነ ሰፊ የድሕረ ት/ቤት ተግባር ፕሮግራም የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማይነጣጠሉ አካላት ይሆናሉ። እንክብካቤ በተሞላ አካባቢ በሚኖር ውጤታማና ሁሉን አቀፍ አካዳሚያዊ ትምህርት አማካይነት፣ ተማሪዎች አርቆ አሳቢ፣ አምራችና ለማሕበረሰቡ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ አባላት የመሆን ዕድል ይኖራቸዋል።

### አእምሯዊ ዕድገት

የትምህርት ተቀዳሚ ተግባር ሰራተኞች ለተማሪዎች በሚያዘጋጇቸውና በሚመሯቸው የመማር ተግባራት አማካይነት አእምሯዊ ዕድገትን ማጎልበት ነው። በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ፣ የ6ኛ፣ 7ኛና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተቀመጠላቸው የተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የአካዳሚክ ትምህርት ዓይነቶችን መሰረታዊ ስርዓት-ትምህርት የሚወስዱ ሲሆን (እንግሊዝኛ፣ ሒሳብ፣ ሳይንስና ሶሻል ስተዲስ ከ6ኛ ክፍል ንባብ ጋር) ከዚያም በቀረው የቀኑ ክፍለ ጊዜ ደግሞ የአሰሳ/አስገዳጅ ያልሆኑና መሰረታዊ ያልሆኑ የትምህርት ዓይነቶችን ያጠናሉ።

### መሰረታዊ ስርዓት-ትምህርት

ተማሪዎች በመሰረታዊ የትምህርት ዓይነቶቻቸው መሰረት በቡድን ይደራጃሉ። ይህም ማለት፣ ቁጥራቸው በግምት ከሃምሳ እስከ አንድ መቶ ሃያ አምስት የሚሆኑ በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች መሰረታዊ ትምህርቶችን ወደሚያስተምሩና ከሁለት እስከ አምስት መምህራን ወዳሉበት አንድ ቡድን ይመደባሉ ማለት ነው። እነዚህ መምህራን፣ በቡድን ዕቅድ ማውጫ ጊዜ ወቅት ተገናኝተው የተማሪዎችን ትምህርታዊ ፍላጎቶች በተመለከተ ይወያያሉ፣ ቀጣይ ተግባራትን ያቅዳሉ፣ በትምህርት ፍላጎት መሰረት መሰረታዊ የጊዜ ገደብን ይከፋፍላሉ፣ እንደዚሁም ስርዓት-ትምህርታዊ መስኮችን ያቀናጃሉ። የመምህራን ቡድኖች እንዳግባብነቱ የትምህርት ዓይነቶችን የሚያጣምሩ ሲሆን፣ ይህን የሚያደርጉት ደግሞ የስርዓት ትምህርቶችን የእርስ በርስ ተደጋጋፊነት አጽንኦት የሚሰጡ የትምህርት ተሞክሮዎችን በመቅረጽ ነው፤ ይህም በፕሮጀክቶች፣ የተለመደ ከህሎት ትምህርት፣ ተዛማጅ ፅንሰ ሃሳቦች ወይም ገላጭ በሆኑ ክፍሎች አማካይነት ሊሆን ይችላል። ቡድኖቹ የስራ ዘመን ትምህርታዊ ተግባራትንም በመሰረታዊ ስርዓት-ትምህርት ውስጥ ያካትታሉ። ምንም እንኳን ተማሪዎች በተወሰኑ ቡድኖች ውስጥ ቢመደቡም፣ በቡድኑ ውስጥ ያሉት መምህራን ለተወሰኑ ትምህርታዊ ተግባራት አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ተማሪዎችን እንደገና

ያደራጃሉ። መምህራን እንደዚህ ዓይነት ዳግም የማደራጀት ውሳኔዎችን የሚወስኑት በቡድን ስብሰባዎች ወቅት ሲሆን፣ የእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎትና እመርታም የውሳኔያቸው መሰረት ይሆናል። በተወሰኑ የክህሎት መስኮች መሻሻል የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በመሰረታዊ የጊዜ ገደብ ውስጥ ወይም በሌሎች ኮርሶች እና/ወይም ፕሮግራሞች አማካይነት የማሻሻያ እገዛዎችን ያገኛሉ።

## የአሰሳ/አስገዳጅነት የሌላቸው ትምህርቶች ፕሮግራም

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቱ በአሰሳ/አስገዳጅነት የሌላቸው ኮርሶች አማካይነት የተለያዩ የትምህርት አማራጮችን ያቀርባል። በእነዚህ ኮርሶች አማካይነት ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቱ ልዩ ስልጠና የወሰዱ ሰራተኞችና አገልግሎት መስጫዎች በመታገዝ አዳዲስ ፍላጎቶችን ማጎልበትና አዳዲስ ችሎታዎችን ፈልገው ማግኘት ይችላሉ። አስገዳጅነት የሌላቸው ኮርሶች የሚሰጡት በቂ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ከተመዘገቡ ነው። የአሰሳ እና አስገዳጅነት የሌላቸው ትምህርቶች በስብሰባ መርሃ ግብራቸውና በሚሸፍኑት የስርዓተ ትምህርት መጠን ይለያያሉ።

በጥናቶች ፕሮግራም ውስጥ የተዘረዘሩት ሁሉም ኮርሶች በተማሪ ጥያቄ መሰረት የሚሰጡ ናቸው። የማጠናቀቂያ ኮርስ መርሃ ግብሮች በሚጠናቀቁበት ወቅት፣ ከ15 ተማሪ በታች ያላቸው ኮርሶች በተማሪ ፍላጎትና በበጀት ታሳቢ ሁኔታዎች መሰረት ላይሰጡ ይችላሉ። ስለዚህ፣ አማራጭ የኮርስ መረጣዎችም በትክክለኛ የዕቅድ አወጣጥ ሒደት ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። የሚጋጩ ፕሮግራሞችን ማስተካከል አማራጭ የኮርስ መረጣዎችን መርሃ ግብር ማውጣትንም ይጠይቃል። በመጀመሪያው ት/ቤት የሚሰጥ ኮርስ ከተሰረዘ፣ ተማሪው ቦታ እስካለ ድረስ በካውንቲው ውስጥ በሚገኝ ሌላ ት/ቤት ለኮርሱ መመዝገብ ይችላል። ወላጆች የትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረብ ያስፈልጋቸው ይሆናል። ኮርሶች ሲሰረዙ ወይም የኮርስ መጣረስ ሲፈጠር የተማሪውን ጥቅሞችና ፍላጎቶች ለማስተናገድ ማንኛውም ጥረት ይደረጋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በበጀት ምክንያት የተነሳ ኮርሶች በአንድ የተወሰነ ዓመት ላይሰጡና በዚህ ምክንያት ተማሪዎቹ አማራጭ ኮርስ እንዲመርጡ ሊገደዱ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በቂ የተመዝጋቢ ቁጥር የሌላቸው ኮርሶች በርቀት ወይም በኦንላይን ትምህርት አማካይነት ሊሰጡ ይችላሉ።

## አክት II

አክት II ተማሪዎች ተጨማሪና አስገዳጅ ያልሆኑ ኮርሶችን ከት/ቤት በኋላ እንዲወስዱ ዕድል ይፈጥርላቸዋል። በአክት II አማካይነት የሚቀርቡ ኮርሶች በጥናቶች ፕሮግራም ውስጥ አስገዳጅነት የሌላቸው ሲሆኑ በተማሪዎች ጥቅምና በጊዜ መርሃ ግብር ምክንያት በእያንዳንዱ ት/ቤት የተለያዩ ናቸው። የትምህርት ክፍለ ጊዜ በአማራጭ መርሃ ግብር ይሰጣል (ማለትም፣ በሳምንት 2 ቀን ሆኖ ክፍለ ጊዜው ረዘም ያለ ወይም ሌሎች ለውጦች ያሉበት) የትምህርቱ አሰጣጥም በቀኑ ክፍለ ጊዜ ከሚኖር የትምህርት ክፍለ ጊዜ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የሚሰጥ ነው። በክፍል ውስጥ መገኘት ግዴታ ሲሆን የፈተና ውጤትም ይሰጣል። ነባሩን አርፍዶ የሚጓዝ የአውቶብስ የጉዞ መርሃ ግብር በመጠቀም የትራንስፖርት አገልግሎት ይቀርባል።

የኮርስ የጊዜ መርሃ ግብር ሲዘጋጅ የአክት II ትምህርቶችን ለመከታተል ያለዎትን ፍላጎት ያመልክቱ ወይም በእያንዳንዱ ሴሚስተር በት/ቤትዎ በኩል የሚቀርቡ የአክት II ዕድሎችን በተመለከተ ለክፍል ደረጃዎ የተመደቡትን አማካሪ ያነጋግሩ።

## ልዩነት ማድረጊያ መመሪያዎች

ልዩነት ማድረግ ማለት የማስተማርና የመማር ሒደት ሲሆን መነሻ ሃሳቡም ሁሉም ተማሪዎች በተመሳሳይ መንገዶች ላይማሩ ይችላሉ የሚል ነው። በሚከተሉት ላይም የተመሰረተ ነው፡

- ዝግጁነት (ተማሪው ቀደም ሲል ያለው እውቀት፣ ግንዛቤና ክህሎት)
- ፍላጎት (ተማሪውን ተጨማሪ ነገር እንዲያውቅ "የሚገፋፋው" ተማሪው ለማወቅ ያለው ጉጉትና እምቅ ፍላጎት)
- የትምህርት ታሪክ መግለጫ (ተማሪው ለመማር የሚፈልግበት መንገድ)

መምህራን የማስተማር ዘዴ ላይ ልዩነት ሲያደርጉ፣ የተለያዩ ትምህርታዊ አቀራረቦችን የሚነድፉና የሚተገብሩ ሲሆን እነዚህም አቀራረቦች፡

- የተማሪውን ዝግጁነት፣ ፍላጎት እና/ወይም የመማር አጠቃላይ ታሪክ ይመዘናሉ
- የተማሪዎችን ትምህርት በተለያዩ ዘዴዎች በማገዝ ተማሪው ውስብስብ በሆኑ ስራዎች ላይ ስኬታማ እንዲሆን ያግዛሉ
- ይዘት (ተማሪው ምን እንደሚማር)፣ ሒደት (ተማሪው የሚማርባቸው ተግባራት) ወይም ውጤትን (ተማሪው የተማረውን ነገር በተግባር ማሳየት) ያሻሽላሉ
 (አንድ ተማሪ የሚማረውን ማሳያ)

የተለያየ የስኬት ደረጃ ያላቸው ተማሪዎች ወደ መምህር አማካሪ፣ የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት፣ አስገዳጅ ወዳልሆኑና የአሰሳ ኮርሶች ይመደባሉ። የተለያዩ የስኬት ደረጃዎች ያላቸው ተማሪዎች በመሰረታዊ የአካዳሚክ የትምሕርት ዓይነቶች ለመማር ወደሚያስችሉ ቡድኖች ይመደባሉ። መምህራን የማስተማሪያ ፍላጎቶቻቸውን የሚያስተናግዱት በልየታ አማካይነት ሲሆን፣ ይህ ደግሞ እንደሁኔታው ተለዋዋጭ የማስተማሪያ ቡድኖችን መጠቀምን ሊያካትት ይችላል።

መምህራን እንደሁኔታው ተለዋዋጭ የቡድን ውሳኔዎችን የሚወስኑት በተለያዩ የማስተማሪያ አቀራረቦች፣ ቀደም ሲል የነበሩ የመማር ደረጃዎች ምዘናዎች፣ የትምህርት ዓይነት ላይ ያተኮሩ መለያ ፈተናዎች፣ ተማሪዎች በወቅታዊና የቀድሞ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ላይ ያሳዩት ብቃትና መምህሩ ስለተማሪዎቹ ልዩ መገለጫ ባህርያት ባለው እውቀት ላይ በመመስረት ነው።

## ፈታኝ ለሆኑ ኮርሶች መዘጋጀት

የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ሁሉም ተማሪዎች በአድቫንስድ ኮርሶች እንዲመዘገቡና ስኬታማ እንዲሆኑ ያበረታታሉ። በአድቫንስድ ኮርሶች ውስጥ ስኬታማ የሆነ ተሳትፎ መኖሩ በተማሪው ውስጥ የስኬታማነት መንፈስ፣ ከፍተኛ ግለ-ክብር፣ የተሻሻለ የጥናት ክህሎትና በቀጣይ የአድቫንስድ ኮርሶችና ከት/ቤት ባሻገር ላለው ሕይወት ስኬታማ እንዲሆኑ የላቀ መሰረት እንዲኖራቸው ያስችላል። ይሁን እንጂ፣ ተማሪዎች በአድቫንስድ ኮርሶች ውስጥ ለመመዝገብ ፍላጎት ማሳየታቸው ብቻ በቂ አይደለም። ጠንካራ የሆነ የእውቀትና የክህሎቶች መሰረት አስፈላጊ ሲሆን በአድቫንስድ ኮርሶች ላይም ለሚኖር ስኬት መልካም አመላካች ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ፣ ተማሪዎች ለአካዳሚክ ስኬት ጠንካራ መሰረት ለመገንባት በሁሉም ኮርሶች ውስጥ የተቻላቸውን ጥረት ለማድረግ መትጋት ይኖርባቸዋል። በዚህ ውስጥ ደግሞ የሚካተቱት ውጤታማ የአጠናን ልማዶች፣ አሳይመንቶችን ማጠናቀቅ፣ ቀነ ገደቦችን ማክበር፣ አስፈላጊ ሲሆን ተጨማሪ እገዛ መጠየቅ ወይም ተጨማሪ ጊዜን መጠቀምና ለአድቫንስድ ኮርሶች በመሰረትነት በሚያገለግሉ መሰረታዊ ኮርሶች ስኬታማ መሆን ይገኙባቸዋል። የተቻለ ጥረት ማድረግ ማለት ደግሞ ፕሮጀክቶችን ወይም ሌሎች የማበልጸጊያ ወይም የክህሎት ግንባታ ተግባራትን በማጠናቀቅ ከሚፈለገው ዝቅተኛ መስፈርቶች በላይ መስራት ማለት ነው። ተማሪዎችና ወላጆች ከመምህራንና አማካሪዎች ጋር በቅርበት በመስራት እነዚህን ክህሎቶች በመገንባት፣ በመደገፍና በማጎልበት በአድቫንስድ ኮርሶች የመመዝገብና ስኬታማ የመሆን ዕድሎችን ማስፋት አለባቸው። ሁሉም የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ከአማካሪዎችና ወላጆች ጋር በመመካከር የስድስት ዓመት የአካዳሚክ ዕቅድ ማጠናቀቅና በእያንዳንዱ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የክፍል ደረጃ ሲሸጋገሩ ይህንኑ ዕቅድ ማዘመንና ማጥራት ይኖርባቸዋል። 9ኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ፣ የስድስት ዓመቱ ዕቅድ በአራት ዓመት ዕቅድ የሚተካ ሲሆን፣ ይህም ዕቅድ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሚኖራቸው እምርታ በየዓመቱ የሚዘምንና የሚጠራ ነው።

አድቫንስድ ኮርሶች የሚባሉት አንድ ተማሪ የበለጸገ ወይም የተፋጠነ ይዘት ያለውን ኮርስ ሲወስድ ማለት ሆኖ "አድቫንስድ" ወይም "የላቀ" ሊባልም ይችላል። ለምሳሌ፣ ጂኦሜትሪ ለ8ኛ ክፍል አድቫንስድ ኮርስ ሲሆን ለ10ኛ ክፍል ግን ጂኦሜትሪ አድቫንስድ ኮርስ አይሆንም። በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት፣ አድቫንስድ ኮርሶች የሚባሉት የተመረጡ ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ እንደ የዓለም ቋንቋ፣ አልጀብራ I፣ ወይም ጂኦሜትሪ (ሁሉም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የሚወስዱት ጂኦግራፊ እንደ አድቫንስድ ኮርስ አይቆጠርም) በመሳሰሉ ኮርሶች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲቶችን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። እነዚህ ኮርሶች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለሚሰጡ ኮርሶችም እንደ መግቢያ ያገለግላሉ። ከታች ያለው ሰንጠረዥ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሚከናወኑ የፈታኝ ኮርስ መረጣዎች ተማሪዎች በኋላ ላይ የሚኖራቸው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ አማራጮችና ዕድሎች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩባቸውን ሁለት ምሳሌዎች ያቀርባል።

| ኮርስ፡- | አንድምታ፡- |
|---|---|
| አልጀብራ I | የሒሳብ ኮርሶች ቅደም ተከተል አልጀብራ I፣ ጂኦሜትሪ እና አልጀብራ II ነው። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ፈታኝ የሳይንስ ኮርሶችን የመውሰድ ፍላጎት ያለው ተማሪ 10ኛ ክፍል ላይ ኢንቴንሲፋይድ ኬሚስትሪን ይወስዳል። (አድቫንስድ የምደባ ኮርሶች ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ እያሉ የኮሌጅ ክሬዲቶችን እንዲያገኙ ያስችሏቸዋል) አልጀብራ II ለኢንቴንሲፋይድ ኬሚስትሪ ከሚያስፈልጉ ኮርሶች መካከል አንዱ ነው። በተጨማሪም፣ አልጀብራ I የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ በመሆኑ፣ 8ኛ ክፍል ላይ አልጀብራ I ን በሚገባ ማጠናቀቅ ተማሪው አስቀድሞ ለመመረቅ የሚያበቃውን ክሬዲት እንዲያገኝ ያስችለዋል። |
| ስፓኒሽ I እና II | 9ኛ ክፍል ላይ ስፓኒሽ II የወሰደ ተማሪ 10ኛ፣ 11ኛ እና/ወይም 12ኛ ክፍል ላይ ስፓኒሽ III፣ IV እና V መውሰድ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ቢያንስ ለሁለት ዓመት ሌላ ቋንቋ ለመማር ያስችለዋል። ወደ ኮሌጅ ለመግባት ይበልጥ አጋዥ የሆነውን የአድቫንስድ ጥናቶች ዲፕሎማ ለማግኘት አንድን የውጭ ቋንቋ ለሶስት ዓመት ወይም ሁለት የተለያዩ የውጭ ሃገር ቋንቋዎችን ለሁለት ዓመት መማር እንደሚያስፈልግ ይገነዘቡ። |

## በቅድሚያ የሚያስፈልጉ ልዩ ሁኔታዎች

ተማሪዎች ከመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ጀምሮ በቅድሚያ የሚወሰዱ ኮርሶችን ሊያስቀምጡ በሚችሉ አድቫንስድ ኮርሶች ውስጥ የመመዝገብ ዕድል አላቸው። በቅድሚያ የሚያስፈልጉት ነገሮች የተዘረዘሩት አንድ ተማሪ በኮርሱ ስኬታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ሊያስፈልጉ የሚችሉ ክህሎቶች ወይም ተሞክሮዎች ምን እንደሆኑ ለተማሪዎችና ለቤተሰቦች ለማሳወቅ እንዲቻል ነው። ወላጆች ልጆቻቸው በቅድሚያ የሚያስፈልጉ ትምህርቶችን ሳያጠናቅቁ ለእነዚህ ኮርሶች እንዲመዘገቡ ማድረግ ቢችሉም፣ ይህን መመሪያ መከተል ግን በእጅጉ ይመከራል። ወላጆች ምርጫዎቻቸውን በተመለከተ ከት/ቤቱ ሰራተኞች በተለይም ከልጃቸው አማካሪ ጋር መወያየት አለባቸው። ይህ ግብረ-መልስ የሚጠየቅበት ምክንያት የተማሪውን ስኬታማነት ዕድል ለመጨመርና የእነዚህን ኮርሶች አካዳሚያዊ ጥልቀትና ተፈላጊ ሁኔታዎች ለወላጆች ለማሳወቅ ነው። አንድ ወላጅ በመጀመሪያ ለተማሪው ላልተመከረ ኮርስ ተማሪውን ካስመዘገበ፣ የትምህርት ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት ወይም ወላጅ የምደባው ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ በተቻለ ፍጥነት ወላጅ ስለዚህ ውሳኔ ለት/ቤቱ ሰራተኞች ማሳወቅ አለበት።

## የጥናቱ ትምህርታዊ መስኮች

ተማሪዎች ለተወሰኑ ኮርሶች ተመዝግበው እያለ በእያንዳንዱ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የክፍል ደረጃ ላይ እንዲማሩ የሚጠበቁባቸው ዋና ዋና ክህሎቶችና ይዘቶች በቀጣዮቹ ገጾች ውስጥ ተዘርዝረዋል። **ይህ ማሳያ ተማሪዎች ምን እንደሚማሩና ምን እንዲያሳኩ እንደሚጠበቅባቸው የተሟላ ዝርዝር እንደያዘ ተደርጎ አይቆጠርም።** የክፍል ደረጃ ዓላማዎችን ወይም የፕሮግራም መግለጫዎችን በሙሉ ለማየት የሚፈልጉ ወላጆች በእያንዳንዱ ት/ቤት የሚገኙ የአካባቢና የግዛት የስርዓተ ትምህርት መምሪያዎችንና የተጻፉ ማቴሪያሎችን እንዲያነብቡ እና/ወይም የትምህርታዊ መስክ ሱፐርቫይዘርን እንዲያነጋግሩ ይበረታታሉ።

የአርት ትምህርት፣ Pam Farrell፣ ሱፐርቫይዘር ........................................................................................................703-228-6169

ቢዝነስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ኮምፒዩተር ሳይንስና ማርኬቲንግ፣ የቴክኖሎጂ ትምህርት እና የቤተሰብና የሸማቾች ሳይንስ፣ Phyllis Gandy፣ ሱፐርቫይዘር........................703-228-7213

የኬሪዬር፣ ቴክኒክ እና የጎልማሶች ትምህርት፣ Kris Martini፣ ዳይሬክተር ........................703-228-7207

ስርዓተ ትምህርትና ኢንስትራክሽን Sarah Putnam፣ ዳይሬክተር........................703-228-2879

የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት፣ Lori Silver፣ ሱፐርቫይዘር ........................703-228-8045

የእንግሊዝኛ ተማሪዎች፣ Sam Klein፣ ሱፐርቫይዘር ........................703-228-6091

ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች አገልግሎት (GIFTED SERVICES)፣ Cheryl McCullough፣ ሱፐርቫይዘር ........................703-228-6160

ጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት፣ Deborah DeFranco፣ ሱፐርቫይዘር ........................703-228-6165

ሒሳብ፣ Shannan Ellis፣ ሱፐርቫይዘር........................703-228-6135

ሳይንስ፣ Dat Le፣ ሱፐርቫይዘር........................703-228-6166

ሶሻል ስተዲስ፣ Kerri Hirsch፣ ሱፐርቫይዘር ........................703-228-6140

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ Tyrone Byrd፣ ዳይሬክተር ........................703-228-7222

ሁለተኛ ደረጃ ልዩ ትምህርት፣ Heather Rothenbuescher፣ ጊዜያዊ ዳይሬክተር ........................703-228-6055

የዓለም ቋንቋዎች፣ Elisabeth Harrington፣ ሱፐርቫይዘር ........................703-228-6097

## 6ኛ ክፍል መሰረታዊ ስርዓተ ትምህርት

የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በመሰረታዊ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚከተሉትን የትምህርት ዓይነቶች ያጠናሉ። በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት፣ ተማሪዎች እንዳግባብነቱ ማሻሻያና ማበልጸጊያ ይሰጣቸዋል። (ልዩነት ስለማድረግ መረጃን ከገጽ 6 ይመልከቱ።)

*ማስታወሻ፡- ከ15 ተማሪ በታች ያላቸው ኮርሶች በተማሪ ፍላጎትና በበጀት ታሳቢ ሁኔታዎች መሰረት ላይሰጡ ይችላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በበጀት ምክንያት የተነሳ ኮርሶች በአንድ የተወሰነ ዓመት ላይሰጡና በዚህ ምክንያት ተማሪዎቹ አማራጭ ኮርስ እንዲመርጡ ሊገደዱ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በቂ የተመዘገቢ ቁጥር የሌላቸው ኮርሶች በርቀት ወይም በኦንላይን ትምህርት አማካይነት ሊሰጡ ይችላሉ።*

### የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት
### የ6ኛ ክፍል እንግሊዝኛ (11109)

በሁሉም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርትስ ፕሮግራም የሚያተኩረው በቨርጂኒያ የትምህርት እንግሊዝኛ መስፈርቶች ላይ በተገለጸው መሰረት በአራት ማደራጃ አርእስት ላይ ነው፡- ኮሙኒኬሽንና መልቲሞዳል ሊትሬሲ፣ ንባብ፣ መጻፍ እና ምርምር። በእነዚህ መስኮች ላይ ብቁ መሆን ተማሪው የላቀ አስተሳሰብ እንዲኖረውና በት/ቤት ውስጥም ሆነ ከት/ቤት ውጭ ስኬታማ እንዲሆን ያስችለዋል። ስርዓተ ትምህርቱ በጽንሰ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ማዕቀፍን የሚከተል ሲሆን፣ የሚያተኩረውም በዘላቂ ግንዛቤዎችና ወሳኝ ጥያቄዎች ላይ ነው።

- አንብቦ መረዳት የሚያተኩረው ልቦለዳዊና ኢ-ልቦለዳዊ ጽሑፎችን ማነጻጸር ላይ ነው። በልቦለድ ፅሑፎች ውስጥ፣ ተማሪዎች የተራኪ መዋቅሮችን ክፍሎች የሚለዩ ሲሆን በዚህም ውስጥ መገለጫን መለየትና ዘይቤያዊ ቋንቋዎችን መለየት ይገኝበታል። ምክንያታዊ ማጠቃለያዎችን በመፍጠርና ጽሑፋዊ ማስረጃዎችን በመጠቀም መደምደሚያ ላይ በመድረስ አማካይነት ለኢ-ልቦለዳዊ ንባብ አጽንኦት ይሰጣል።
- ተማሪው የቃላትን ስር ማጥናት ይጀምርና የቃላት መጠኑን ማሳደጉን ይቀጥላል።
- ተማሪው በተለያዩ መልኮች ጽሑፍ የማቀድ፣ የማርቀቅ፣ የመከለስና የማረም ስራን የሚሰራ ሲሆን ለተራኪና ገላጭ አጻጻፍም አጽንኦት ይሰጣል።
- ተማሪዎች በተናጠልና በትብብር ቡድኖች አማካይነት መልቲሞዳል ፕረዘንቴሽን ያቀርባሉ። ተማሪዎች በተለያዩ የሚድያ ቅርጾች የቀረበ መረጃን ይተረጉማሉ።
- ተማሪዎች ለትብብራዊ የቡድን ስራ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፣ እንደዚሁም ያመቻቻሉ።
- ተማሪው ለምርምር ውጤት የሚሆኑ አግባብነት ያላቸውን ግብዓቶች ይፈልጋል፣ ይመዝንና ይመርጣል፣ የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ምንጮችንም ይጠቅሳል። የሌላ ሰውን ስራ የራስ አስመስሎ ማቅረብ ምንነትና ለሚያስከትላቸው ውጤቶች አጽንኦት ይሰጣል።

### የ6ኛ ክፍል ንባብ
### ሙሉ ዓመት (11106)
### ሴሚስተር (11108) (በ Thomas Jefferson መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት አይሰጥም)

*ለሴሚስተሩ ኮርስ በቅድሚያ የሚያስፈልግ ሁኔታ። ከዚህ በፊት በተደረጉ የንባብ ምዘናዎች ላይ ከፍተኛ አካዳሚያዊ ውጤት ማስመዝገብ።*

የስድስተኛ ክፍል ሙሉ ዓመት የንባብ ኮርስ ለሁሉም ተማሪዎች የሚመከር ሲሆን ዓላማውም ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ማንበብን ከመማር ወደ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማንበብን መማር ሽግግር የሚያግዝ ማዕቀፍ ይዘረጋል። የዚህ ኮርስ ትኩረት ኮሙኒኬሽንና መልቲሞዳል ሊትሬሲስ እና የቨርጂኒያ የመማር ደረጃዎች የንባብ ክፍሎች ናቸው። በ6ኛ ክፍል ንባብ ወቅት መምህራን በሚከተሉት የንባብ መመሪያ ክፍሎች ላይ ያተኩራሉ፡- የንባብ ሒደት፣ በቃላት ስር ላይ የሚያተኩር የቃላት መምሪያ፣ እና የልቦለዳዊና ኢ-ልቦለዳዊ ጽሑፎች አቀራረብ። ውጤታማ አንባቢያን ከማንበባቸው በፊት፣ በሚያነብቡት ወቅትና ካነበቡ በኋላ የአንድን ጽሑፍ ፍቺ ለመረዳት ስትራቴጂዎችን መተግበር እንዳላቸው ተማሪዎች ይማራሉ። ተማሪዎች በይዘት መስኮች ላይ ንባብን እንደ ትምህርት መሳሪያ ይጠቀማሉ። የአንብቦ መረዳት ስትራቴጂዎች ላይ ግልጽ የሆነ መመሪያ፣ ስትራቴጂዎቹ እንዴት እንደሚተገበሩ በመመሪያ የታገዘ አሰራርና ራስን ችሎ ማንበብ—የመጽሐፍት ክበባትና ለደስታ ማንበብን ጨምሮ—የኮርሱ ዋነኛ አካላት ናቸው።

እባክዎ የሴሚስተሩ አማራጭ በሁሉም ት/ቤቶች *የማይገኙ* መሆናቸውን ያስተውሉ፤ የዚህ ምክንያት ደግሞ የተዘጋጀበት ዓላማ ከዓለም ቋንቋ ትውውቅ (ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ፣ ላቲን)፣ ስፓኒሽ በደንብ ለሚናገሩ ወይም የመሸጋገሪያ ስፓኒሽ ትውውቅ ጋር ይጣመራል። የሴሚስተር አማራጭን የሚመርጡ ተማሪዎች ከዚህ በፊት በወሰዷቸው የንባብ መመዘኛ ፈተናዎች ላይ ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ይጠበቅባቸዋል። የሴሚስተር አማራጩ አግባብነት ያለው ስለመሆን ወይም አለመሆኑ ከመምህርዎና ከአማካሪዎ ጋር ይመካከሩ።

### የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት
### የ6ኛ ክፍል የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት (17110)

ሁሉም የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፋሉ።
የጤና ትምህርት ፕሮግራም አጽንኦት የሚሰጠው ተማሪዎች ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ለማሳካት ምን ማወቅ፣ መገንዘብና ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ነው። የትምህርት አሰጣጡ የወጣቶችን የጤና ጉዳዮች፣ የውሳኔ አሰጣጥ ክህሎቶችና የሚያስከትሉትን ውጤቶች ይሸፍናል። ተማሪዎች የአቻ ግፊትን፣ የግለሰቦችን ልዩነትና ሃሳቦች ማክበርን ይገነዘባሉ። ተማሪዎች ውጤታማ የሆኑ የፊት ለፊትና ኦንላይን የተግባቦት ክህሎቶችን ይማራሉ። ከጥናት መስኮች መካከል ስሜታዊ፣ አእምሯዊ፣ ማሕበራዊ እና የአካባቢ ጤና፣ ደህንነትና የአጣዳፊ ሁኔታ ዝግጁነት፣ ግንኙነቶች፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነትና በሽታ መከላከልና የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ይገኙበታል። የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ፕሮግራም በእንቅስቃሴ መርሆዎች ላይ አናቶሚካል መዋቅሮችን እውቀት በመተግበር የአፈጻጸም ብቃትን ያሻሽላል። ተማሪዎች በእንቅስቃሴ ክህሎቶች ላይ መተማመንና ብቃትን የሚያሳዩ ሲሆን በተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴ ሁኔታዎች በሕብረት ስራና በአነስተኛ ቡድን ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች በኢነርጂ ባላንስ፣ ስነ-ምግብና፣ ደህንነት መካከል ያለውን ትስስር ያስረዳሉ።

### ሒሳብ
### ሒሳብ 6 (13110)

ሒሳብ 6 መሰረታዊ ኮርስ ሆኖ ለስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ጥልቀት ባለው መልኩ ይዘትን ያስተምራል።

የ6ኛ ክፍል መለኪያ መስፈርቶች በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሙሉ ቁጥር ከተሰጠው አጽንኦት ወደ አልጀብራ መሰረታዊያን የሚደረጉ ሽግግሮች ናቸው።

ተማሪዎች በእነዚህ መስኮች ላይ ግንዛቤን ያዳብራሉ፡-

1. ቁጥር እና ቁጥርን መረዳት
2. ስሌትና ግመታ
3. ልኬትና ጂኦሜትሪ
4. ፕሮባብሊቲ እና ስታስቲክስ
5. ፓተርኖች፣ ተግባራትና አልጀብራ

በተጨማሪም፣ የስታንዳርዶች ይዘት ሒሳብን ለመማር የሚከተሉትን የሒደት ግቦች ለማገዝ የታሰበ ነው፦ ችግር አፈታት፣ ተግባቦቶች፣ ትስስሮች፣ ውክልናዎችና ምክንያት አሰጣጥ።

የቨርጂኒያ የ6ኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርት ደረጃዎች የይዘት ክፍሎች ይበልጥ ውስን ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

- በክፍልፋዮች፣ አስርዮሽና መቶኛዎች የሚከናወኑ ኦፕሬሽኖች፣ ወካይ ሞዴሎችና ተጨባጭ መልመጃዎችን ጨምሮ።
- ክፍልፋዮች፣ ቅይጥ ቁጥሮችና አስርዮሽን የሚያካትቱ ባለብዙ ሒደት ተጨባጭ መልመጃዎች።
- የኢንቲጀር ሞዴልና የኦፕሬሽኖችን ቅደም ተከተል ጨምሮ የኢንቲጀር ኦፕሬሽኖች።
- ፓይ፣ ክበባትና የክበብ ግራፎችን መለየትና ማሰስ።
- የማዕከላዊ ዝንባሌ መለኪያዎች፣ አማካይ ውጤት እንደ ባላንስ ነጥብ ጨምሮ።
- ተመጣጣኝ ግንኙነቶች፣ ቃላዊ መግለጫዎች፣ ተመኖች፣ የጥምርታ ሰንጠረዦችና ግራፎችን ጨምሮ።
- ኢክዌዥንና ኢንኢኩዋሊቲስ።

**ቅድመ አልጀብራ ለ6ኛ ክፍል ተማሪዎች (6/7/8)**
**ሙሉ ዓመት (13128)**

የ6ኛ ክፍል (6/7/8) ተማሪዎች ቅድመ አልጀብራ በቨርጂኒያ የ6ኛ፣ 7ኛና 8ኛ ክፍል የመማር ደረጃዎች ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሒሳብ ይዘቶች በጥልቀት የሚያስተምር ነው። ይህ መጠነ ሰፊ ኮርስ ተማሪዎች አልጀብራ I፣ ኢንቴንሲፋይድ እና ጂኦሜትሪን ከማጥናታቸው በፊት በደንብ ሊማሩ የሚገባቸውን ሁሉንም የቅድመ አልጀብራ ይዘት ያካተተ ነው።

ተማሪዎች በእያንዳንዱ የቅድመ አልጀብራ መስክ ላይ ግንዛቤን ያዳብራሉ፦

1. ቁጥር እና ቁጥርን መረዳት
2. ስሌትና ግመታ
3. ልኬትና ጂኦሜትሪ
4. ፕሮባቢሊቲ እና ስታስቲክስ
5. ፓተርኖች፣ ተግባራትና አልጀብራ

በተጨማሪም፣ የስታንዳርዶች ይዘት ሒሳብን ለመማር የሚከተሉትን የሒደት ግቦች ለማገዝ የታሰበ ነው፦ ችግር አፈታት፣ ተግባቦቶች፣ ትስስሮች፣ ውክልናዎችና ምክንያት አሰጣጥ።

የዚህ ኮርስ ይዘትን በተመለከተ ተጨማሪ ውስን ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

- በክፍልፋዮች፣ አስርዮሽና መቶኛዎች የሚከናወኑ ኦፕሬሽኖች፣ ወካይ ሞዴሎችና ተጨባጭ መልመጃዎችን ጨምሮ።
- ክፍልፋዮች፣ ቅይጥ ቁጥሮችና አስርዮሽን የሚያካትቱ ባለብዙ ሒደት ተጨባጭ መልመጃዎች።
- የኢንቲጀር ሞዴልና የኦፕሬሽኖችን ቅደም ተከተል ጨምሮ የኢንቲጀር ኦፕሬሽኖች።
- ፓይ፣ ክበባትና የክበብ ግራፎችን መለየትና ማሰስ።
- የማዕከላዊ ዝንባሌ መለኪያዎች፣ አማካይ ውጤት እንደ ባላንስ ነጥብ ጨምሮ።
- ተመጣጣኝ ግንኙነቶች፣ ቃላዊ መግለጫዎች፣ ተመኖች፣ የጥምርታ ሰንጠረዦችና ግራፎችን ጨምሮ።
- ስሌትንና በስርዓቱ ንዑስ ስብስቦች መመደብን ጨምሮ የተጨባጭ ቁጥር ስርዓት።
- የኦፕሬሽኖች ቅደም ተከተልን ጨምሮ ፖዘቲቭና ነጌቲቭ ኤክስፖነንቶች።
- መደበኛ ቁጥሮች፣ ተመጣጣኝ ምክንያታዊነት፣ እና ተመሳሳይነትን የሚያካትቱ የተለያዩ ተጨባጭ መልመጃዎችን መፍታት።
- ስሎፕ እንደ ለውጥ መጠን።
- ከመስመር ላይ ግራፍ መሳል ጋር የተዛመዱ ተመጣጣኝ ግንኙነቶች እና ደማሪ ግንኙነቶችና ሌሎች ተጨባጭ መልመጃዎች።
- የሸማቾች መተግበሪያዎችን የሚያካትቱ ተጨባጭ መልመጃዎች።
- እኩል አራት ማዕዘን ያላቸው።
- በማዕዘን ዝምድና ላይ ተመስርተው የማይታወቁ ማዕዘናትን ልኬት መወሰን።
- የተለያዩ ምስሎችን መጠንና ስፋት የሚመለከቱ ተጨባጭ መልመጃዎችን መፍታት፣ የተለዋዋጭ ባህርያትን ውጤቶች ትንተና እና መግለጫን ጨምሮ።
- ትርጉሞችን፣ የሃሳብ ገለጻዎችና ዲላቴሽን ጨምሮ ትራንስፎርሜሽኖችን መተግበር።
- ከተለያዩ እይታዎች አንጻር ባለ ሶስት አቅጣጫ ሞዴሎችን መገንባት።
- የፓይታጎሪያን ቴረምን መተግበርና ማጣራት።
- ኮምፖዛይት ምስሎች ያሉባቸውን ተጨባጭ የስፋትና የፔሪሜትር መልመጃዎችን መፍታት።
- የኢ-ጥገኛና ጥገኛ ክስተቶችን ፕሮባቢሊቲ ማነጻጸርና ፕሮባቢሊቲዎችን ማስላት።
- ቦክስ ፕሎትስ፣ ስካተርፕሎትስ እና ሂስቶግራምስን ጨምሮ የተለያዩ ዓይነት ግራፎችን በመጠቀም ዳታዎችን መግለጽ፣ መታዘብና ለመደምደሚያ መነሻ ማድረግ፣ ማነጻጸርና መተንተን።
- የአልጀብራ አገላለጾችን መገምገምና ማቅለል።
- ዶሜይን፣ ሬንጅ፣ ጥገኛና ኢ-ጥገኛ ተለዋዋጮች።
- ስሎፕን መለየትና መተርጎም እንደዚሁም የተሰጠ ዋጋ ተግባርን ማስቀምና በቃላዊ መግለጫዎች፣ ሰንጠረዦች፣ ኢኩዌዥኖችና ግራፎች መካከል ትስስር መፍጠር።
- በአንድ ወይም በሁለቱም በኩል በአንድ ተለዋዋጭ ላይ ያሉ ባለ ብዙ ደረጃ ሊኒየር ኢኩዌዥኖችና ኢንኢኩዋሊቲስን ተጨባጭ የመልመጃ መተግበሪያን በመጠቀም መፍታት።

**ሳይንስ**
**የ6ኛ ክፍል ሳይንስ (14105)**

በ6ኛ ክፍል ሳይንስ ወቅት፣ ተማሪዎች በፀሐይ አወቃቀር ውስጥ ካለው የመሬት አቀማመጥ አንስቶ በምድር ላይ እስከሚገኘው የውኃ፣ የኃይል፣ የአየር፣ እና የሥነ ምህዳር መስተጋብር ድረስ የአለማቸውን ባሕርያት ይመረምራሉ። በተጨማሪም የ6ኛ ክፍል ስታንዳርዶች የሳይንስን ተፈጥሮ በመገንዘብ ረገድ በተማሪ ዕድገት ላይ ማተኮራቸውን ይቀጥላሉ። ይህ ሳይንሳዊ እይታ የተፈጥሮ ማብራሪያዎች የሚደራጁበትና የሚሞከሩበት ምልከታ፣ ሙከራ፣ ሞዴሎች፣ ማስረጃ፣ እና ስልታዊ ሒደቶችን በመጠቀም ነው የሚለውን ሃሳብ ይገልጻል። ሳይንሳዊ ማብራሪያዎች በአመክንዮአዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን፤ በማስረጃ ሕግ የሚገዙ መሆናቸውን፤ ከምልከታ፣ ከማጣቀሻና ሙከራዊ ማስረጃ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን፤ ለምክንያታዊ ትችት ክፍት መሆናቸውን፤ አዳዲስ ሳይንሳዊ መረጃ ተጨምሮባቸው ለመተራትና ለመቀየር እንደሚችሉ የሚያትቱ ጽንሰ ሃሳቦች በሳይንስ ተፈጥሮ ውስጥ ይካተታሉ። የሳይንስ ባህርይ ስለተፈጥሮ ማብራሪያዎችን መስጠት ይችላል፣ የእርምጃዎችን ተከታይ ውጤቶች ለመተንበይ ይችላል፣ *ነገር ግን ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ ሊያገለግል አይችልም*። ተማሪዎች ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ችግሮችን በማብራራት፣ ምርመራዎችን በማቀድና በማካሄድ (ኤስአይ - ዓለም አቀፍ የመለኪያዎች ሲስተምን በመጠቀም)፣ ዳታን በመተርጎም፣ በመተንተን እና በመገምገም፣ ማጠቃለያዎችን እና ማብራሪያዎችን በመገንባት እና በመተቸት፣ ሞዴሎችን በማዳበር እና በመጠቀም፣ እና መረጃን በማግኘት፣ በመገምገም እና ግንኙነት በመፍጠር የሳይንሳዊ እና የምህንድስና አሰራሮች ግንዛቤን ያሳያሉ።

ተማሪዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች ለመመርመርና ለመገንዘብ ይችላሉ፡

- የፀሐይ አወቃቀር የተደራጀ ሲሆን በፀሐይ አወቃቀር ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካላት እርስ በርስ እንደሚገናኙ፣
- በፀሐይ፣ በመሬት እና በጨረቃ መካከል ግንኙነት መኖሩን፣
- መሠረታዊ የኃይል ምንጮች መኖራቸውን እና ኃይል መለወጥ እንደሚችል፣
- ሁሉም ነገር ከአተሞች የተዋቀረ መሆኑን፣
- ውሃ ልዩ አካላዊ ባሕርያት እንዳሉትና በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ አካባቢ ውስጥ ሚና እንዳለው።
- አየር ባህሪዎች እንዳሉት እና የምድር ከባቢ አየርም የራሱ መዋቅር እንዳለውና ተለዋዋጭ መሆኑን፣
- መሬት እና ውሃ በውሃ ተፋሰስ ስርዓቶች ውስጥ ሚና እንዳላቸው እናም
- ሰዎች በአካባቢው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ እንዲሁም ግለሰቦች ከኃይል እና ከአካባቢ ጋር በተያያዙ የሕዝብ ፖሊሲ ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ።

**ማህበራዊ ጥናቶች**
**የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክ እስካሁን ድረስ (12354)**
የ6ኛ ክፍል የማሕበራዊ ጥናቶች ጭብጥ፣ SURVIVAL የሚል ነው። ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ገለጻ አማካይነት የዩናይትድ ስቴትስን ታሪክ ይመረምራሉ። ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ማስረጃዎችን መርምረው ስለቀድሞ ሁኔታ ግንዛቤያቸውን ለመፍጠር ታሪካዊ የአስተሳሰብ ክህሎቶችን ይጠቀማሉ። የኮርሱ ይዘት የሚያተኩረው ዩናይትድ ስቴትስ በጊዜ ሒደት በነበራት መልክዓ ምድር ላይና አሰሳና መስፋፋት፣ አብዮትና ተሐድሶ፣ ኢኮኖሚያዊ ተግባቦቶችና ርዕዮተ ዓለማዊ ግጭትና እምርታን ገላጭ በሆነ መንገድ ማስቀመጥ ላይ ነው። አበይት ክስተቶችና ቁልፍ ሰዎች ከእነዚህ ጭብጦች ጋር በነበራቸው ተግባቦት በኩል ይጠናሉ። ይህም ተማሪዎቹ ስለ ዘመናት ስሌት ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እንዲሁም ውሳኔዎች ወደፊት በሚከናወኑ ነገሮች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉት እንዴት እንደሆነ እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል።

ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ዓላማዎች መማር ይጠበቅባቸዋል፡-
ተማሪዎች፡-

- ለታሪካዊና መልክዓ ምድራዊ ትንታኔ የሚሆኑ ክህሎቶችን ያዳብራሉ።
- ካርታዎችን፣ ሉሎችን፣ ፎቶዎች፣ ምስሎችን፣ ካርቱኖችንና ሰንጠረዦችን ይጠቀማሉ።
- ቀደምት ባህሎች በሰሜን አሜሪካ እንዴት እንደዳበሩ ይመረምራሉ።
- አውሮፓውያን በሰሜን አሜሪካ እና ምዕራብ አፍሪካ ያደረጉትን አሰሳ ይገልጻሉ።
- የቅኝ ገዥ አሜሪካን ቅርጽ የቀየሩ ጉዳዮችን ይለያሉ።
- የአሜሪካ አብዮትን መንስኤዎችና ውጤቶች ይተነትናሉ።
- ከ1801 እስከ 1861 ድረስ አሜሪካው ውስጥ በስተምዕራብ የተደረገውን ማስፋፊያና ተሐድሶ ይመረምራሉ።
- የእርስ በርስ ጦርነቱን መንስኤዎች፣ ዋና ዋና ክስተቶችና ውጤቶችን ይገነዘባሉ።
- ከእርስ በርስ ጦርነቱ በኋላ በመልሶ ግንባታው ምክንያት ሕይወት እንዴት እንደተቀየረ ይገልጻሉ።
- ዩናይትድ ስቴትስ ከአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እስከሚካሄድ ድረስ የነበራትን ተለዋዋጭ ሚና ያስረዳሉ።
- የሃያኛው ክፍለ ዘመንን ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ቴክኖሎጂያዊ ለውጦችን ይመረምራሉ።
- አሜሪካ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ውስጥ የነበራት ተሳትፎ ዋና ዋና መንስኤዎችና ውጤቶችን ይለያሉ።
- የሲቪል መብቶች ንቅናቄን ጨምሮ የሃያኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ወቅት የነበሩትን አበይት የሃገር ውስጥ ጉዳዮች ይመረምራሉ።

---

**የ6ኛ ክፍል የአሰሳ ፕሮግራም**
**ሙሉ ዓመት (19000)**
የአሰሳ ዊል (ኤክስፐሎራቶሪ ዊል) የተቀረጸበት ዓላማ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ የሚቀርቡ አማራጭ ትምህርቶችን ናሙና የሚፈትሹበት ዕድል መስጠት ነው። በኤክስፐሎራቶሪ ዊል ላይ ያሉ ተማሪዎች በትምህርት ክፍሎች ውስጥ የሚዘዋወሩ ሲሆን ክፍሎቹም ስነ-ጥበብ፣ ተግባራዊ ጥበብ እና/ወይም ስነ-ቋንቋን ይወክላሉ። ተማሪዎች በቡድን እየተጓዙ በሚቀርቡላቸው የተለያዩ ክፍሎች በኩል ይሽከረከራሉ። በእያንዳንዱ ት/ቤት የጊዜ መርሃ ግብር መሰረት የሚቀርቡ ትምህርቶች ይለያያሉ። በምርጫ የሚሰጡ ኮርሶች በድሕረ ት/ቤት አክት II ፕሮግራም በኩል የሚቀርቡ ከሆነ ተማሪዎች በእነዚህ ኮርሶች ላይም ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ። (ገጽ 6ን ተመልከት።)

በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃን የሚመርጡ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎችና ትምህርታዊ ጥናቶችን መውሰድ ያለባቸው ወይም ሌላ የክህሎት ማጎልበቻ ኮርስ መውሰድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ከኤክስፐሎራቶሪ ዊል ይልቅ በእነዚህ የትምህርት ክፍሎች ላይ በየቀኑ ይሳተፋሉ።

**የስነ ጥበብ ትምህርት**
ቪዡዋል አርት፣ ሙዚቃና የቴአትር አርት ክፍሎች በሙሉ ለፈጠራዊ ሒደቱ ልምድ ላይ የተመሰረተ አቀራረብን ይጠቀማሉ። በጥበባት የትምህርት ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የቪዡዋል አርት ስራዎችንና ሙዚቃዊ የቴአትር ዝግጅቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልግ አመለካከት፣ ዲስፕሊን እና አስፈላጊ ክህሎትን ያጎለብታሉ፣ ያጣራሉ።

**የድምጽ አወጣጥ ትምህርት (Exploring Chorus) 6**
*ተማሪዎች፡-*

- ጥሩ የድምፅ ቃና ለማውጣት የሚያስፈልግ ትክክለኛ የሰውነት አቋም፣ የትንፋሽ ቁጥጥር እና የአፍ ቅርጽን በተግባር ያሳያሉ።
- ሙዚቃ ማንበብና ተጓዳኝ ሙዚቃዊ አተረጓጎም ለትክክለኛ ፒች፣ ቅኝት፣ የጊዜ አመልካች፣ የቁልፍ አመልካች፣ ቴምፖ እና ገላጭ ምልክቶችን ለማግኘት መሰረታዊነታቸውን ይገነዘባሉ።
- ዲያቶኒክ ፒች ሲስተምን በመጠቀምና በስብስቡ ውስጥ የተወሰነ ክፍልን በመያዝ በትክክል ፒችን የማዛመድ ችሎታን ያዳብራሉ።
- ርዝመታቸው ከ1 እስከ 2 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- የባንድ መሪው ለሚያሳየው የአካል እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።
- በተለያዩ ዓይነቶች ዘይቤዎች በሚደረጉ ዝግጅቶችና ፕረዘንቴሽኖች አማካይነት የተማሩትን በተግባር ያሳያሉ።

**የስነ ተውኔት ትምህርት(Exploring Theatre Arts)**
*ተማሪዎች፡-*

- በመደበኛና ኢ-መደበኛ ሁኔታዎች ውስጥ ውጤታማ የተግባቦት ቴክኒኮችን በተግባር ያሳያሉ።
- በስክሪፕት የተጻፉ ትዕይንቶችን ማዘጋጀትና ሂስ ማቅረብ ይችላሉ።
- በድራማ/ቴአትር ውስጥ ያሉ ጭብጦችን ማወቅና ማሰስ ይችላሉ።
- ማሻሻያዎችን በመጠቀም ገጸ ባህርይ መፍጠር፣ ሃሳቦችን ማሰስና አዳዲ የሆኑ ክስተቶችን ያዘጋጃሉ።
- የቴክኒካዊ ቴአትር አላባውያን በተመልካቹ ላይ ተጽእኖ ስለሚያሳድሩ እነርሱን ተገንዝቦ ምላሽ ይሰጣሉ።
- ሚናን በመተወን ስለ ራስና ስለሌሎች ያላቸውን ግንዛቤ ያሻሽላሉ።

**ቪዥዋል አርትስ ማሰስ (Exploring Visual Arts)**

*ተማሪዎች፡-*

- የጥበብ አላባውያንና የዲዛይን መርሆዎችን በሁለት እና ሶስት አቅጣጫ የጥበብ ስራዎች ላይ ይተገብራሉ።
- በጥበብ ስራዎቻቸው ውስጥ የተለያዩ ቴክኒኮችና ማቴሪያሎችን ይዳስሳሉ።
- በጥበብ ስራዎች ውስጥ ግላዊ ሃሳቦችና አሳሳቢ ጉዳዮችን በማስተላለፍ በፈጠራዊ ሒደት በኩል ችግሮችን ይፈታሉ።
- የተለያዩ ቴክኒኮችን በመጠቀም የቀለም ቅብ፣ ስዕል መሳል፣ ቅይጥ ሚድያና ቅርጻ ቅርጽን ይለማመዳሉ።
- በስዕሎቻቸውና በጥበብ ስራዎቻቸው ሊኒዬር አተያዮችን ይጠቀማሉ።

**ቢዝነስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ**

**ቢዝነስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ማሰስ**

*ተማሪዎች ስለኪቦርድ አጠቃቀም፣ ኮድ አሰጣጥ፣ የማይክሮ ኮምፒዩተር መተግባሪያዎችና የኬሪዬር ዳሰሳን እንዲያውቁ ይደረጋሉ። ተማሪዎች በንክኪ የመጻፍ ዘዴ፣ ፍጥነት፣ ትክክለኛነት፣ ጥሩ የአገጃጀት ክህሎቶች፣ ቅንብር፣ የቋንቋ ጥበባትን ጨምሮ ትክክለኛ የኪቦርድ አጠቃቀም ቴክኒኮችንና የመሳሪያውን ትክክለኛ አጠቃቀምና እንክብካቤ ይማራሉ። የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ የቴክኖሎጂ ስታንዳርዶች በኮርስ ይዘቱ ውስጠ ተካትተዋል።*

*ተማሪዎች፡-*

- የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን አካላትና በቢዝነስና በግል አጠቃቀም የቢዝነስ ችግሮችን ለመፍታት ያላቸውን ተግባራት ይማራሉ።
- “የንክኪ ቴክኒክ” ዘዴን በመጠቀም በኪቦርድ አጠቃቀም ብቃታቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- አካዳሚክና ግላዊ ክህሎቶችን ለማጎልበት ሰነዶችን በማዘጋጀት STEM ጨምሮ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ይቀርጻሉ።
- መተግበሪያ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የኮድ አሰጣጥ (የኮምፒዩተር ፕሮግራም) መርሆዎችን ይማራሉ።

**እንግሊዝኛ**

**ጋዜጠኝነትን ማሰስ**

ይህ የአሰሳ ኮርስ ተማሪዎች ጋዜጣ ወይም ኦዲዮ/ቪድዮ ዜናዎችን እንዲያዘጋጁ ይጠይቃል። ተማሪዎች በስራቸው አማካይነት ስለ ጋዜጣና ብሮድካስት አጻጻፍና አዘገጃጀት ይማራሉ።

*ተማሪዎች፡-*

- የጋዜጠኝነት ዘዴዎችን ተምረው ጥቅም ላይ ያውላሉ።
- የሕትመት እና/ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስቶችን ይዘትና ቴክኒካዊ ጥራት ይተነትናሉ።
- ኤዲቶሪያሎች፣ ፊቸሮችና ስፖርት ጨምሮ የዜና ጽሑፎችን ይጽፋሉ እና/ወይም የንግድ ማስታወቂያዎች፣ የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያዎችን ወይም የዜና ሾው፣ የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያዎችና የንግድ ማስታወቂያዎችን ጨምሮ አጫጭር የብሮድካስት መልእክቶችን ይጽፋሉ።
- የተለያዩ የጋዜጠኝነት ስራ ተግባራትን ለምሳሌ አርትኦት፣ የምስል ንድፍና ኮፒ፣ አርእስት፣ የስክሪፕት ዝግጅት አጻጻፍና የመጨረሻ ፕሮዳክሽን ይለማመዳሉ።

**የቤተሰብና የሸማች ሳይንሶች**

**የቤተሰብና የሸማቾች ሳይንስን ማሰስ**

የቤተሰብና የሸማቾች ሳይንስ አሰሳ ተማሪዎችን የ21ኛው ክፍለ ዘመን አኗኗር ለሚጠይቃቸው ሁኔታዎች ያዘጋጃቸዋል። ይህ ኮርስ ግላዊ፣ ቤተሰባዊ፣ የስራ እና የማህበረሰብ ደንቦችና ኃላፊነቶች ለማስተዳደር የሚያስችል መሰረት ይጥላል።

*ተማሪዎች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ፡-*

- የግለሰባዊ ዕድገት መስኮች
- የግብ አወጣጥ
- ቤተሰቦችን ማጠናከር
- የግል ደህንነትና ጤንነት ግንዛቤ
- የቁጠባና የወጪ አወጣጥ አሰራሮች
- የልብስ እንክብካቤ
- የምግብ ዝግጅት
- ከሌሎች ጋር የሚኖር አዎንታዊና በእንክብካቤ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት

የማስተማር ተግባሩ እንዳግባብነቱ ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ እና ሒሳብ (STEM) ጽንሰ ሃሳቦች አጽንኦት ይሰጣል።

**የዓለም ቋንቋዎች**

የዓለም ቋንቋ አሰሳ ኮርሶች የሚሰጡት ለ6ኛ ክፍል ሲሆን ለቋንቋ እና ባሕል መግቢያ ናቸው። በ7ኛ ክፍል ደረጃ I ቋንቋ ለመውሰድ የአሰሳ ኮርሶች መውሰድ አያስፈልግም። ይሁን እንጂ፣ ኮርሶቹን መውሰድ ይመከራል።

**ፈረንሳይኛ እና/ወይም ስፓኒሽ ማሰስ**

*ተማሪዎች መዳረሻ ቋንቋን እንዲያውቁ ተደርገው የሚከተሉትን መሰረታዊ የተግባቦት ክህሎቶች ይማራሉ፡- ስለ ራስ መገንዘብ፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ እና መመለስ፤ በመሰረታዊ ማህበራዊ ተግባቦቶች ውስጥ ይሳተፋሉ፤ ከሰላምታ፣ ቀለማት፣ ቁጥሮችና ምግብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ውስን ሐረጋትና የመልዕክት ሃሳቦች ተገንዝበው ይጠቀማሉ።*

**ላቲን ማሰስ**

*ተማሪዎች የሮማውያን ቋንቋና ባሕልን ይተዋወቃሉ። ተማሪዎች ጀማሪ የላቲን ቃላትን ሲማሩ ቋንቋን የተመለከቱ መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች ይቀርባሉ። የላቲን ቃላት ምስረታ ላይ ጠንካራ አጽንኦት ይሰጣል።*

**የቴክኖሎጂ ትምህርት**

**ቴክኖሎጂን ማሰስ**

*ተማሪዎች በቅድሚያ የሚያጠኑት የሁሉንም ቴክኖሎጂ መሰረታዊ ክፍሎች ሲሆን እነርሱም ውስጥ ሒደቶች፣ ኢነርጂ፣ መረጃ እና ሰዎች ይገኙበታል። እስከ አራት የሚደርሱ የቴክኖሎጂ ሲስተሞችን የሚያስሱ ሲሆን በዚህም ውስጥ ባዮቴክኖሎጂ፣ ኢነርጂ፣ ኮንስትራክሽን፣ ትራንስፖርት፣ ኮሙኒኬሽን፣ ማምረት/ማኑፋክቸሪንግ ይገኙበታል። በመጨረሻ፣ ቴክኖሎጂ በማህበረሰብ፣ በአካባቢ እና ባሕል ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ከወደፊት ተከታይ ውጤቶችና ውሳኔዎች ጋር ያስተሳስራሉ።*

*ተማሪዎች፡-*

- የችግር አፈታት ሒደትን ማብራራትና መጠቀም ይችላሉ።
- የድራፍቲንግና የመለኪያ መሳሪያዎችን መምረጥና መጠቀም ይችላሉ።

- በቴክኖሎጂ ትምህርት ላብራቶሪ ውስጥ ያሉ መሳሪያዎችን፣ ማሽኖችና ዕቃዎችን መለየትና መጠቀም ይችላሉ።
- በላብራቶሪ ውስጥ ያሉትን የሃይልና የእጅ መሳሪያዎች በሚጠቀሙበት ጊዜ ጥሩ የሆነ ደህንነትና አሰራሮችን በተግባር ያሳያሉ።
- በላብራቶሪው ውስጥ ያሉትን መሳሪያዎችና ማሽኖችን ዓላማ ይገነዘባሉ።
- ቀላል ዕቅድ በመተንተን ይህን መረጃ እንዴት ማንበብና ለተጠናቀቀ ፕሮጀክት ማስተላለፍ እንደሚችሉ ይገነዘባሉ።
- መሳሪያዎች፣ ቁሳቁስ፣ ሒሳብና ሳይንስን በመተግበር መልመጃን ይፈታሉ።
- ሞጁሎችን ወይም ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ወይም ከትራንስፖርት፣ ምርትና ኮሙኒኬሽን ጋር በተያያዙ የውድድር ዝግጅቶች ላይ ያሳያሉ።

---

**6ኛ ክፍል ሴሚስተር ወይም ዓመቱን በሙሉ**
***መሰረታዊ ያልሆኑ የትምህርት ክፍሎች***

**የስነ ጥበብ ትምህርት**
***በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃ***
ከእያንዳንዱ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ዓላማዎች መካከል ከታች የተዘረዘሩት ይገኙበታል። በእያንዳንዱ ት/ቤት ለእነዚህ የሙዚቃ ቡድኖች የየራሳቸው ስሞች ሊሰጣቸው ይችላል።

በ ***ጀማሪ ባንድ፣*** *ሙሉ ዓመት*
Brass & Percussion **(19233)**, Woodwinds **(19234)**
*ተማሪዎች:-*
- *የሙዚቃ መሳሪያ ትክክለኛ አጠቃቀምና አያያዝን በተግባር ያሳያሉ።*
- *ገላጭ የሆነ ድምፅ ለማውጣት ትክክለኛውን የአጨዋወት ቴክኒክ በተግባር ያሳያሉ።*
- *ሙዚቃ ማንበብና ተጓዳኝ ሙዚቃዊ አተረጓጎም ለትክክለኛ ፒች፣ ቅኝት፣ የጊዜ አመልካች፣ የቁልፍ አመልካች፣ ቴምፖ እና ገላጭ ምልክቶችን ለማግኘት መሰረታዊነታቸውን ይገነዘባሉ።*
- የአንድ ከግማሽ አክታቭና መሰረታዊ ነጥቦችን (*የምት መሳሪያዎች*) ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን ክህሎቶች የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል።
- *መቃኛ በመጠቀም የሙዚቃ መሳሪያውን ድምፅ የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ።*
- ርዝመታቸው ከ1 እስከ 2 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- ሜትሮኖም በመጠቀምና የባንድ መሪውን የሰውነት እንቅስቃሴ በመከተል ቀጥ ካለ ምት ጋር የጋራ ሙዚቃ ይጫወታሉ።
- በተለያዩ ዓይነቶች ዘይቤዎች በሚደረጉ ዝግጅቶችና ፐረዘንቴሽኖች አማካይነት የተማሩትን በተግባር ያሳያሉ።

በ ***መካከለኛ ደረጃ ባንድ፣*** *ሙሉ ዓመት* **(19201)** *ተማሪዎች:*
- ለመካከለኛ ደረጃ ባንድ የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ክህሎት ይኖራቸዋል።
- የሙዚቃ ኖታዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ፣ በዚህም ውስጥ አርቲኩሌሽንስ፣ ኮምፓውንድ ሜትርስ፣ ንኡስ ክፍሎችና የቁልፍ አመልካቾችና በርካታ ድንገተኛዎች ይገኙበታል።
- የአንድ ከግማሽ አክታቭ ወይም የተሟሉ መሰረታዊ ነጥቦችን (የምት *መሳሪያዎች*) ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል።
- የሙዚቃ መሳሪያውን ቅኝት በጆሮ ሰምተው የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ።
- ርዝመታቸው ከ2-4 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- የቴምፖ፣ የአርቲኩሌሽን እና የዘይቤ ለውጦችን በተመለከተ ከባንዱ መሪ ለሚያዩት የሰውነት እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።
- የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ የአንደኛና ክፍል ስነ-ጽሑፍን በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- ከኮንሰርት ስነ-ጽሑፍ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ።

በ ***ጀማሪ ኦርኬስትራ፣*** *ሙሉ ዓመት* **(19237)** *ተማሪዎች:*
- የሙዚቃ መሳሪያ ትክክለኛ አጠቃቀምና አያያዝንና አመታትን በተግባር ያሳያሉ።
- ፒዚካቶና መሰረታዊ የአመታት ቴክኒኮችን ጨምሮ ገላጭ የሆነ ድምፅ ለማውጣት ትክክለኛውን የአጨዋወት ቴክኒክ በተግባር ያሳያሉ።
- ሙዚቃ ማንበብና ተጓዳኝ ሙዚቃዊ አተረጓጎም ለትክክለኛ ፒች፣ ቅኝት፣ የጊዜ አመልካች፣ የቁልፍ አመልካች፣ ቴምፖ እና ገላጭ ምልክቶችን ለማግኘት መሰረታዊነታቸውን ይገነዘባሉ።
- አንድ አክታቭ (የመጀመሪያ አቀማመጥ) እና ጥንድ ማቆሚያዎችን በአንድ አውታር ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን ክህሎቶች የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል።
- መቃኛ በመጠቀም የሙዚቃ መሳሪያውን ድምፅ የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ።
- ርዝመታቸው ከ1 እስከ 2 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- ሜትሮኖም በመጠቀምና የባንድ መሪውን የሰውነት እንቅስቃሴ በመከተል ቀጥ ካለ ምት ጋር ይጫወታሉ።
- በተለያዩ ዓይነቶች ዘይቤዎች በሚደረጉ ዝግጅቶችና ፐረዘንቴሽኖች አማካይነት የተማሩትን በተግባር ያሳያሉ።

በ ***መካከለኛ ደረጃ ኦርኬስትራ፣*** *ሙሉ ዓመት* **(19242)** *ተማሪዎች:*
- ለመካከለኛ ደረጃ ኦርኬስትራ የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ክህሎት ይኖራቸዋል።
- የሙዚቃ ኖታዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ፣ በዚህም ውስጥ አርቲኩሌሽንስ፣ ኮምፓውንድ ሜትርስ፣ ንኡስ ክፍሎችና የቁልፍ አመልካቾችና ሁለት ከፍታዎች ይገኙበታል።
- ማራዘሚያዎችን በመጠቀምና የመምቻውን ክብደት፣ ፍጥነትና ንክኪ በመቆጣጠር በአንድ ተኩል አክታቭ ሬንጅ የመጫወት ክህሎትን ያዳብራሉ፤ እነዚህን ክህሎቶች የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል።
- የሙዚቃ መሳሪያውን ቅኝት በጆሮ ሰምተው የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ።
- ርዝመታቸው ከ2-4 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- የቴምፖ፣ የአርቲኩሌሽን እና የዘይቤ ለውጦችን በተመለከተ ከባንዱ መሪ ለሚያዩት የሰውነት እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።
- የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- ከኮንሰርት ስነ-ጽሑፍ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ።

**የቴአትር ጥበባት**
***ሙሉ ዓመት*** **(11391)**
**ሴሚስተር (11392)**
*ተማሪዎች:-*
- ደረጃቸውን የጠበቁ የቴአትር ኦዲሽን ሒደቶችን፣ የቃል ጥናት ልምምዶችንና ቴክኒካዊ ፕሮዳክሽኖችን ይለማመዳሉ።
- ድራማዊ ጽሑፎችን ለዝግጅት አቀራረብ መነሻ አድርገው መተንተንና መገምገም ይችላሉ።
- የገጸ ባህርያትን አካላዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ገጽታዎች ያካትታሉ።

- የዳሬክተሮችንና ተዋንያንን የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት ተገንዝበው ይተገብራሉ።
- በቴአትር ፕሮዳክሽኖች ላይ የማኔጅመንቱን ተግባራት ለይተው ይገነዘባሉ።
- ከሌሎች ጋር በመተባበር አርቲስቲክ ዲስፕሊን አዘጋጅተው ይተገብራሉ።

**ቪዥዋል አርትስ I**
***ሙሉ ዓመት* (19040)**
**ሴሚስተር (19041)**
*ተማሪዎች:-*

- *የዲዛይን መርሆዎችና የጥበብን አላባውያን በመተግበር የጥበብ ስራዎችን ይፈጥራሉ።*
- *የተለያዩ ቴክኒኮችንና ሒደቶችን በማቀናጀት ባለ ሶስት አቅጣጫ ስራዎችን ይፈጥራሉ።*
- *የተለያዩ የጥበብ ስራዎች ላይ ግላዊ ትርጓሜዎችንና የሒሲና ፍርድን ይሰጣሉ።*
- *የጥበብን ቃላት በመጠቀም ያለቁ የጥበብ ስራዎችን መተንተንና መተቸት ይችላሉ።*
- *በጥበብ አዘገጃጀት ላይ ስነ-ምግባራዊ ውሳኔዎችን ማስረዳትና መተግበር ይችላሉ።*

***የድምፅ ሙዚቃ***
ከእያንዳንዱ ትምህርት ክፍል ጊዜ ዓላማዎች መካከል ከታች የተዘረዘሩት ይገኙበታል። በእያንዳንዱ ት/ቤት ለእነዚህ የሙዚቃ ቡድኖች የየራሳቸው ስሞች ሊሰጣቸው ይችላል።

በ ***ጀማሪ የሙዚቀኞች ስብስብ፣*** ሙሉ ዓመት **(19261)**
ሴሚስተር **(19264)** *ተማሪዎች፡*

- *ጥሩ የድምፅ ቃና ለማውጣት የሚያስፈልግ ትክክለኛ የሰውነት አቋም፣ የትንፋሽ ቁጥጥር እና የአፍ ቅርጽን በተግባር ያሳያሉ።*
- *ሙዚቃ ማንበብና ተጓዳኝ ሙዚቃዊ አተረጓጎም ለትክክለኛ ፒች፣ ቅኝት፣ የጊዜ አመልካች፣ የቁልፍ አመልካች፣ ቴምፖ እና ገላጭ ምልክቶችን ለማግኘት መሰረታዊነታቸውን ይገነዘባሉ።*
- *ዲያቶኒክ ፒች ሲስተምን በመጠቀምና በስብስቡ ውስጥ የተወሰነ ክፍልን በመያዝ በትክክል ፒችን የማዛመድ ችሎታን ያዳብራሉ።*
- *ርዝመታቸው ከ1 እስከ 2 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።*
- *የባንድ መሪው ለሚያሳየው የአካል እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።*
- *በተለያዩ ዓይነቶች ዘይቤዎች በሚደረጉ ዝግጅቶችና ፕረዘንቴሽኖች አማካይነት የተማሩትን በተግባር ያሳያሉ።*

**ሒሳብ**
**የሒሳብ ስትራቴጂስ ለ6ኛ ክፍል**
***ሙሉ ዓመት* (13116)**
**ሴሚስተር (13121)**
የስትራቴጂስ ኮርስ በክፍል ደረጃ ሒሳብ ላይ ስኬታማ ለመሆን ተጨማሪ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በአማራጭነት የሚሰጥ ኮርስ ነው። በስትራቴጂስ ኮርስ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የመነሻ እውቀትን ያዳብራሉ፣ ስለይዘቱ ተጨማሪ ጽንሰ ሃሳባዊ አቀራረቦችን ይለማመዳሉ፣ መሰረታዊ የኮርሱን ይዘት ይበልጥ በጥልቀት ያጎለብታሉ።

**የልዩ ፍላጎት ትምህርት**
**ትምህርታዊ ጥናቶች፣ *ሙሉ ዓመት* (10028)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ:- ተማሪው የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት መሆኑ መለየት አለበት*
በተማሪው ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) መሰረት የኮርስ ስራ ግለሰባዊ የሚደረግ ሲሆን፣ የእያንዳንዱን ተማሪ አጠቃላይ የትምህርት ኮርሶችን ፍላጎትንም ያጠናክራል። በተጨማሪም፣ የማዳመጥ ክህሎቶች፣ የመጻፍ ክህሎቶች፣ የአደረጃጀትና አጠቃላይ የጥናት ክህሎቶች አጽንኦት ይሰጣቸዋል።

**ማህበራዊ ክህሎቶች፣ *ሙሉ ዓመት* (10023)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ:- ተማሪው የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት መሆኑ መለየት አለበት*
የማሕበራዊ ክህሎቶች ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ደረጃ ተማሪው ከሌሎች ሰዎች ጋር ተገቢነት ያላቸውን ማሕበራዊ ተግባቦቶች ለማድረግ የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን የመቅሰምና የመተግበር ዕድልን ይሰጠዋል። በትምህርትነት ከሚሰጡ ክህሎቶች መካከል ከሌሎች ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ አተያይን ማዳበር፣ የራስን ዕድል በራስ መወሰን፣ ከቡድኖች ጋር መስራት፣ ጫና እና ስልቹነትን የመቋቋሚያ ስትራቴጂዎች እና ለማሕበራዊ ጠባይ "ያልተጻፉ ደንቦችን" መገንዘብ ይገኙበታል። ድርጅታዊና ለራስ የመሟገት ክህሎቶችን ማዛመድም ይሸፈናሉ።

***የተማሪ ድጋፍ***
**ኮር ፕላስ (Core Plus)**
***ሙሉ ዓመት* (11129)**
**ሴሚስተር (11128)**
ይህ ኮርስ የተቀረጸው የአጠቃላይ ትምህርት ተማሪ ሆኖ ስለ አደረጃጀት፣ ማስታወሻ አያያዝ፣ ፈተና አወሳሰድና ተማሪዎች ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያግዟቸውን ሌሎች ቴክኒኮች በተመለከተ ተጨማሪ ለማወቅ ለሚፈልግ ተማሪ ነው።

*ተማሪዎች:-*

- *የራሳቸውን የጥናት ጊዜ መርሃ ግብር ያቅዳሉ።*
- *የማዳመጥ ክህሎቶችን ለማሻሻል የሚያስችሉ መንገዶችን ይማራሉ።*
- *በአሁኑ ጊዜ የት/ቤት ስራዎችን በተመለከተ ያሉ አመለካከቶችን ይገመግማሉ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በመለየትና ግቦችን በማስቀመጥ አዎንታዊ የሆኑትን ማጎልበት ይጀምራሉ።*
- *የተጻፈ ማቴሪያልን ለመገንዘብና ይዞ ለመቆየት የሚያስችል የጥናት ክህሎት ቀመርን ይጠቀማሉ።*

**የዓለም ቋንቋዎች**
**የስፓኒሽ *ማስተዋወቂያ* (15501)**
**የሴሚስተር ኮርስ**
*ተማሪዎች መዳረሻ ቋንቋን እንዲያውቁ ተደርገው የሚከተሉትን መሰረታዊ የተግባቦት ክህሎቶች ይማራሉ:- ስለ ራስ መገንዘብ፣ ጥያቄ መጠየቅና መመለስ፤ በመሰረታዊ ማህበራዊ ተግባቦቶች ውስጥ ይሳተፋሉ፤ ከሰላምታ፣ ቀለማት፣ ቁጥሮችና ምግብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ውስን ሐረጋትና የመልዕክት ሃሳቦች ተገንዝበው ይጠቀማሉ።*
ይህ ኮርስ የተቀረጸው ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የሚያስጥ ኮርስ ከመወሰዱ በፊት ለቋንቋው ተጋላጭነትን ለመፍጠር ነው። በመዳረሻ ቋንቋ መዋቅር ውስጥ መሰረት በማስቀመጥ ተሳታፊ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቂያ መስፈርቶችን ለማሟላት ባገለገለው የተመረጠ ቋንቋ ላይ ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።
**የመሸጋገሪያ *ስፓኒሽ* (15010)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ:- ለሶስት ዓመታት ያህል APS FLES (የውጭ ቋንቋ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት) የስፓኒሽ ቋንቋ ፕሮግራም ማጠናቀቅ ወይም በብቃት ምዘና ላይ የተመሰረተ የመምህር ምክረ ሃሳብ ማግኘት።*

ይህ ኮርስ የተቀረጸው ለ6ኛ ክፍል በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚሰጥ የውጭ ቋንቋ (FLES) ፕሮግራም ተከታይ ሆኖ ነው። ይህ ኮርስ በሁሉም ቦታዎች ላይሰጥ ይችላል። ይህ ኮርስ ለሴሚስተር ብቻ ከ6ኛ ክፍል ንባብ ጋር የተጣመረ በመሆኑ፣ የመሸጋገሪያ ስፓኒሽ ከዚህ በፊት የክፍል ደረጃ ንባብ SOL ፈተናዎችን ላላለፉ ተማሪዎች አይመከርም።

ይህ የመሸጋገሪያ ፕሮግራም በመረዳት፣ በመናገር፣ በማንበብና በመጻፍ ቀደም ሲል የዳበሩ ክህሎቶች ላይ የተመሰረተ ነው። ትኩረቱም በተግባራዊ ስራዎች፣ አጫጭር ዝግጅቶች፣ መዝሙሮች፣ የጥንድ የቃል ንግግር ተግባራትና ጨዋታዎች አማካይነት ቋንቋን በተጨባጩ ዓለም ጥቅም ላይ መዋል ነው። ሰዋሰው እና መዝገበ ቃላት ትርጉም ባላቸው መንገዶች የሚተዋወቁና የሚጠናከሩ ሲሆን ይህም ቋንቋን መረዳትን ለማገዝ ነው። የተለያየ የሂስፓኒክ ዓለም ባህላዊ ልማዶችና አሰራሮች የስርዓተ ትምህርቱ የማይነጣጠሉ አካላት ናቸው።

በዚህ ኮርስ፣ ተማሪዎች፡-

- ጓደኞች፣ ቤተሰብና ት/ቤትን በመሳሰሉ አርእስት ላይ በሚካሄዱ መሰረታዊ ጭውውቶች ላይ ይሳተፋሉ።
- ሜኑ፣ ምልክቶችና የትክክለኛ ማቴሪያሎችን አጫጭር ምሳሌዎች ያነብባሉ።
- አጫጭር መግለጫዎች፣ መልዕክቶችና የተመሩ ድርሰቶችን ይጽፋሉ።
- በተለያዩ የሂስፓኒክ ባሕሎች ዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ስላሉ ገጽታዎች ይማራሉ።

**ስፓኒሽ ብቃት ላላቸው ተናጋሪዎች 6ኛ ክፍል (15503)**
**የሴሚስተር ኮርስ**
*በቅድሚያ የሚወሰድ፡- በመምህሩ በሚወሰነው መሰረት በስፓኒሽ ንግግር ልህቀትን በተግባር ማሳየት።*
ይህ ኮርስ የተቀረጸው በስፓኒሽ ቋንቋ አፍ መፍቻ ቋንቋ በሚመስል ደረጃ ብቃት ኖሯቸው በስፓኒሽ መሰረታዊ የንባብና የመጻፍ ክህሎቶችን በላቀ ብቃት ማከናወን ላልቻሉ ተማሪዎች ነው። ተማሪዎች በንባብ፣ በአጻጻፍና በንግግር ላይ የተግባቦት ክህሎታቸውን በማዳበር የስፓኒሽ ሰዋሰው ማጥናት ይጀምራሉ። ተማሪዎች ስለሂስፓኒክ ባሕል አተያዮችና ልማዶች ጥልቅ ግንዛቤ ያዳብራሉ።

*ተማሪዎች፡-*

- በኢ-መደበኛ ጭውውቶችና ውይይቶች ላይ ይሳተፋሉ።
- ለአነስተኛ ቡድኖችና ለክፍሉ የቃል ገለጻዎችን ያቀርባሉ።
- በእውነተኛ ጽሑፎች ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ሃሳቦችና ሁለተኛ ደረጃ ሃሳቦችን ይለያሉ።
- አጫጭር ማጠቃለያ ጽሑፎችን ይጽፋሉ።
- የሂስፓኒክ ባሕልን ተጽእኖ ያጠናሉ።

---

## 7ኛ ክፍል መሰረታዊ ስርዓተ ትምህርት

የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በመሰረታዊ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚከተሉትን የትምህርት ዓይነቶች ያጠናሉ። በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት፣ ተማሪዎች እንዳግባብነቱ ማሻሻያና ማበልጸጊያ ይሰጣቸዋል። (ልዩነት ስለማድረግ መረጃን ከገጽ 6 ይመልከቱ።)

*ማስታወሻ፡- ከ15 ተማሪ በታች ያላቸው ኮርሶች በተማሪ ፍላጎትና በበጀት ታሳቢ ሁኔታዎች መሰረት ላይሰጡ ይችላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በበጀት ምክንያት የተነሳ ኮርሶች በአንድ የተወሰነ ዓመት ላይሰጡና በዚህ ምክንያት ተማሪዎቹ አማራጭ ኮርስ እንዲመርጡ ሊገደዱ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በቂ የተመዝጋቢ ቁጥር የሌላቸው ኮርሶች በርቀት ወይም በኦንላይን ትምህርት አማካይነት ሊሰጡ ይችላሉ።*

### የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት

**የ7ኛ ክፍል እንግሊዝኛ (11110)**
በሁሉም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርትስ ፕሮግራም የሚያተኩረው በቨርጂኒያ የትምህርት እንግሊዝኛ መስፈርቶች ላይ በተገለጸው መሰረት በአራት ማደራጃ አርእስት ላይ ነው፡- ኮሙኒኬሽንና መልቲሞዳል ሊትሬሲ፣ ንባብ፣ መጻፍ እና ምርምር። በእነዚህ መስኮች ላይ ብቁ መሆን ተማሪው የላቀ አስተሳሰብ እንዲኖረውና በት/ቤት ውስጥም ሆነ ከት/ቤት ውጭ ስኬታማ እንዲሆን ያስችለዋል። ስርዓተ ትምህርት በጽንሰ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ማዕቀፍን የሚከተል ሲሆን፣ የሚያተኩረውም በዘላቂ ግንዛቤዎችና ወሳኝ ጥያቄዎች ላይ ነው።

- ልቦለዳዊና ኢ-ልቦለዳዊ ጽሑፎችን በማነጻጸር ለአንብቦ መረዳት ቀጣይነት ያለው አጽንኦት ይሰጠዋል። በልቦለድ ጽሑፎች ውስጥ ተማሪዎች የተለያዩ ዘውጎችን አላባውያን በመለየት በደራሲው ዘይቤ ላይ ያተኩራሉ። ለኢ-ልቦለድ የበለጠ አጽንኦት የሚሰጥ ሲሆን ተማሪዎችም የጽሑፎችን ምንጭ፣ እይታ እና ዓላማ ይለያሉ።
- ተማሪው የቃላት መነሻዎችና ስሮችን ማጥናቱንና ፍካሬዎችን መለየቱን ይቀጥላል።
- ተማሪው በተለያዩ መልኮች ጽሑፍ ማቀድ፣ ማርቀቅ፣ መከለስና ማረም የሚችሉ ሲሆን ለገላጭና አሳማኝ አጻጻፍ አጽንኦት ይሰጣል። ተማሪዎች የአንድን ጽሑፍ ዋና ጭብጥ፣ ቅላጼ እና ድምፅ ለተደራሲው እና ለዓላማው በሚስማማ መልኩ ለማዘጋጀትና ለማሻሻል ይጽፋሉ።
- ተማሪዎች በተናጠልና በትብብር ቡድኖች አማካይነት መልቲሞዳል ፕረዘንቴሽን ማቅረባቸውን ይቀጥላሉ። ተማሪዎች በተለያዩ የሚድያ ቅርጸቶች የቀረበ መረጃን ይተረጉማሉ።
- ተማሪዎች እንደ አስተዋጽኦ አድራጊና እንደ አመቻች ሆነው የትብብር ስራን ኃላፊነት የሚጋሩ ሲሆን የጋራ መግባባትን ለመፍጠርም ይሰራሉ።
- ተማሪው የምርምር ግኝቶችን ለመጥቀስ፣ ለማጠቃለልና በራስ ቃል ለመግለጽ የምርምር ቴክኒኮችን የሚተገብር ሲሆን ምንጮችንም በአግባቡ ይጠቅሳል። የሌላ ሰውን ስራ የራስ አስመስሎ ማቅረብ ምንነትና ለሚያስከትላቸው ውጤቶች አጽንኦት ይሰጣል።

### የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት

**የ7ኛ ክፍል የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት (17120)**
ሁሉም የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፋሉ። የጤና ትምህርት ፕሮግራም አጽንኦት የሚሰጠው ተማሪዎች ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ለማሳካት ምን ማወቅ፣ መገንዘብና ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ነው። የትምህርት አሰጣጡ ለስጋት አዘል ባህርያት አዎንታዊ አማራጮችን ያቀርባል። ተማሪዎች የአቻ ግፊትን ለመቋቋምና ጫናን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ክህሎቶችን ተምረው ይጠቀማሉ። ከጥናት መስኮች መካከል ስሜታዊ፣ አእምሯዊ፣ ማሕበራዊ እና የአካባቢ ጤና፣ ደህንነትና የአጣዳፊ ሁኔታ ዝግጁነት፣ ግንኙነቶች፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነትና በሽታ መከላከልና የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ይገኙበታል። የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ፕሮግራም ተማሪዎች የተማሩትን ክህሎቶችና እውቀት እንዲጠቀሙ የሚያደርጉ የተለያዩ አካላዊ ተግባራትን ያስተዋውቃል። ተማሪዎች በተለዋዋጭና ሊገመቱ በማይችሉ የጨዋታ ሁኔታዎች ወቅት እንቅስቃሴን በተግባር ያሳያሉ። ተማሪዎች በግብ አቀማመጥ አማካይነት ብቃታቸውንና የግል ብቃት ዕቅዶቻቸውን መተንተን ይማራሉ። ተማሪዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴን አስፈላጊነት ከጤና በተለይም ከመጠን ያለፈ ውፍረት እና የውጥረት ስሜት ጋር ያያይዛሉ።

### ሒሳብ

**ሒሳብ 7 (13111)**
ማትስ 7 ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ይዘትን በጥልቀት እንዲማሩ የሚያስችል መሰረታዊ ኮርስ ነው።

የ7ኛ ክፍል ስታንዳርዶች ተማሪዎች ስምንተኛ ክፍልና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ ስኬታማ ለመሆን በሚያስፈልጓቸው የቅድመ አልጀብራ መሰረቶች ላይ ትኩረት ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ።

ተማሪዎች በእነዚህ መስኮች ላይ ግንዛቤን ያዳብራሉ፡-

1. ቁጥር እና ቁጥርን መረዳት
2. ስሌትና ግምታ
3. ልኬት
4. ፕሮባብሊቲ እና ስታስቲክስ
5. ፓተርኖች፣ ተግባራትና አልጀብራ

በተጨማሪም፣ የስታንዳርዶች ይዘት ሒሳብን ለመማር የሚከተሉትን የሒደት ግቦች ለማገዝ የታሰበ ነው፡- ችግር አፈታት፣ ተግባቦቶች፣ ትስስሮች፣ ውክልናዎችና ምክንያት አሰጣጥ።

የቨርጂኒያ የ7ኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርት ደረጃዎች የይዘት ክፍሎች ተጨማሪ ውስን ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- የኦፕሬሽኖች ቅደም ተከተልን ጨምሮ ፖዘቲቭና ነጌቲቭ ኤክስፖነንቶች።
- መደበኛ ቁጥሮች፣ ተመጣጣኝ ምክንያታዊነትና ተመሳሳይነትን የሚያካትቱ የተለያዩ ባለ ብዙ ደረጃ ተጨባጭ መልመጃዎችን መፍታት።
- የተለያዩ ምስሎችን ስፋትና መጠንን የሚመለከቱ ተጨባጭ መልመጃዎች።
- እኩል አራት ማዕዘን ያላቸው።
- ትራንስፎርሜሽንስ።
- ሂስቶግራምስና ሌሎች ግራፎች።
- ስሎፕ እንደ ለውጥ መጠን።
- ከመስመር ላይ ግራፍ መሳል ጋር የተዛመዱ ተመጣጣኝ ግንኙነቶች እና ደማሪ ግንኙነቶች።
- የቃል መግለጫዎች፣ ሰንጠረዦች፣ ኢኩዌዥኖችና ግራፎችን በመጠቀም ተመጣጣኝ ግንኙነቶችን ማገናኘት።
- አልጀብራዊ አገላለጾችን መመዘን።
- በተጨባጭ መልመጃዎች ላይ በማተኮር ባለ ሁለት ደረጃ ሊኒዬር ኢኩዌዥኖችና ኢንኢኩዋሊቲስ መፍታት።

### ቅድመ አልጀብራ ለ 7ኛ ክፍል ተማሪዎች (7/8) (13109)

የ7ኛ ክፍል (7/8) ተማሪዎች ቅድመ አልጀብራ በቨርጂኒያ የ7ኛና 8ኛ ክፍል የመማር ደረጃዎች ውስጥ የሚገኙ የአልጀብራ አርእስት በጥልቀት የሚያስተምር ነው። የስታንዳርዶቹ ትኩረት ተማሪዎች በስምንተኛ ክፍልና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሒሳብ ላይ በአልጀብራ I ወይም አልጀብራ I ኢንቴንሲፋይድ ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ በብቃት መማር የሚገባቸው የአልጀብራ መሰረቶች ላይ ነው።

ተማሪዎች በእነዚህ መስኮች ላይ ግንዛቤን ያዳብራሉ፡-

1. ቁጥር እና ቁጥርን መረዳት
2. ስሌትና ግምታ
3. ልኬት
4. ፕሮባብሊቲ እና ስታስቲክስ
5. ፓተርኖች፣ ተግባራትና አልጀብራ

በተጨማሪም፣ የስታንዳርዶች ይዘት ሒሳብን ለመማር የሚከተሉትን የሒደት ግቦች ለማገዝ የታሰበ ነው፡- ችግር አፈታት፣ ተግባቦቶች፣ ትስስሮች፣ ውክልናዎችና ምክንያት አሰጣጥ።

የኮርሱ የይዘት ክፍሎች ተጨማሪ ውስን ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- ስሌትንና በስርዓቱ ንዑስ ስብስቦች መመደብን ጨምሮ የተጨባጭ ቁጥር ስርዓት።
- የኦፕሬሽኖች ቅደም ተከተልን ጨምሮ ፖዘቲቭና ነጌቲቭ ኤክስፖነንቶች።
- መደበኛ ቁጥሮች፣ ተመጣጣኝ ምክንያታዊነትና ተመሳሳይነትን የሚያካትቱ የተለያዩ ባለ ብዙ ደረጃ ተጨባጭ መልመጃዎችን መፍታት።
- ስሎፕ እንደ ለውጥ መጠን።
- ከመስመር ላይ ግራፍ መሳል ጋር የተዛመዱ ተመጣጣኝ ግንኙነቶች እና ደማሪ ግንኙነቶች።
- የሸማቾች መተግበሪያዎችን የሚያካትቱ ተጨባጭ መልመጃዎች።
- እኩል አራት ማዕዘን ያላቸው
- በማዕዘን ዝምድና ላይ ተመስርተው የማይታወቁ ማዕዘናትን ልኬት መወሰን።
- የተለያዩ ምስሎችን መጠንና ስፋት የሚመለከቱ ተጨባጭ መልመጃዎችን መፍታት፣ የተለዋዋጭ ባህርያትን ውጤቶች ትንተና እና መግለጫን ጨምሮ።
- ትርጉሞችን፣ የሃሳብ ገለጻዎችና ዲላቴሽን ጨምሮ ትራንስፎርሜሽኖችን መተግበር።
- ከተለያዩ እይታዎች አንጻር ባለ ሶስት አቅጣጫ ሞዴሎችን መገንባት።
- የፓይታጎሪያን ቴረምን መተግበርና ማጣራት።
- ኮምፖዛይት ምስሎች ያሉባቸውን ተጨባጭ የስፋትና የፔሪሜትር መልመጃዎችን መፍታት።
- የኢ-ጥገኛና ጥገኛ ክስተቶችን ፕሮባብሊቲ ማነጻጸርና ፕሮባብሊቲዎችን ማስላት።
- ቦክስ ፕሎትስ፣ ስካተርፕሎትስ እና ሂስቶግራምስን ጨምሮ የተለያዩ ዓይነት ግራፎችን በመጠቀም ዳታዎችን መግለጽ፣ መታዘብና ለመደምደሚያ መነሻ ማድረግ፣ ማነጻጸርና መተንተን።
- የአልጀብራ አገላለጾችን መገምገምና ማቅለል።
- በአንድ ተግባር ውስጥ ያለ ግንኙነትን መወሰንና ዶሜይንና ሬንጅን እና ጥገኛና ኢ-ጥገኛ ተለዋዋጮችን መወሰን።
- ስሎፕን መለየትና መተርጎም እንደዚሁም የተሰጠ ዋጋ ተግባርን ማስቀምና በቃላዊ መግለጫዎች፣ ሰንጠረዦች፣ ኢኩዌዥኖችና ግራፎች መካከል ትስስር መፍጠር።
- በአንድ ወይም በሁለቱም በኩል በአንድ ተለዋዋጭ ላይ ያሉ ባለ ብዙ ደረጃ ሊኒየር ኢኩዌዥኖችና ኢንኢኩዋሊቲስን ተጨባጭ የመልመጃ መተግበሪያን በመጠቀም መፍታት።

### አልጀብራ I፣ ኢንቴንሲፋይድ (13140)

አልጀብራ I ኢንቴንሲፋይድ መሰረታዊ ኮርስ ሆኖ ለ6ኛ፣ 7ኛና 8ኛ ክፍሎች የቨርጂኒያ የትምህርት ደረጃዎች ከፍተኛ ብቃትን ላሳዩና ተጨማሪ አድቫንስድ አርእስትን ለማጥናት ዝግጁ ለሆኑ ሁሉም ተማሪዎች ይዘቱ ላይ ጥልቀት ያለው አሰጣጥን የሚከተል ነው።

አልጀብራ I ኢንቴንሲፋይድ የሚወስዱ ተማሪዎች በእነዚህ መስኮች ላይ ግንዛቤን ያዳብራሉ፡-

1. አገላለጾችና ኦፕሬሽኖች
2. ኢኩዌዥንስና እና ኢንኢኩዋሊቲስ
3. ተግባራት
4. ስታስቲክስ

በተጨማሪም፣ የስታንዳርዶች ይዘት ሒሳብን ለመማር የሚከተሉትን የሒደት ግቦች ለማገዝ የታሰበ ነው፡- ችግር አፈታት፣ ተግባቦቶች፣ ትስስሮች፣ ውክልናዎችና ምክንያት አሰጣጥ።

የቨርጂኒያ አልጀብራ I ትምህርት ደረጃዎች የይዘት ክፍሎች ተጨማሪ ውስን ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- ቃላዊና አሃዛዊ ሁኔታዎችን በአልጀብራዊ መንገድ በመወከል አገላለጾችን ይገመግማሉ።

- በፖሊኖሚያልስ ላይ ኦፕሬሽኖችን በማካሄድ የኤክስፖነንቶች፣ ኦፐሬሽኖችና ፋክተሪንግ ሕጎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ።
- ስኩዌር ሩቶችን እና ኪዩብ ሩቶችን ያቃልላሉ።
- ባለ ብዙ ደረጃ ኢኩዌዥኖችን በአንድ ተለዋዋጭ አልጀብራዊ በሆነ መንገድ መፍታት፤ በዚህም ውስጥ ሊኒዬር፣ ኩዋድራቲክ እና ሊትራል ሆነው ለተጨባጭ መልመጃ አፈታት አጽንኦት ይሰጣል።
- ሁለት ሊኒዬር ኢኩዌዥንስ ያሉባቸውን ሲስተሞች በሁለት ተለዋዋጮች በግራፍና በአልጀብራ መፍታት።
- የኢንኢኩዋሊቲስ ሲስተሞችን ጨምሮ የሊኒዬር ኢንኢኩዋሊቲስ ሶሉሽን በሁለት ተለዋዋጮች በግራፍ ማስቀመጥ።
- ስሎፐ መወሰን፣ ኢኩዌዥኖችን መጻፍና ሊኒዬር ኢኩዌዥኖችን በሁለት ተለዋዋጮች በግራፍ ማስቀመጥ።
- ሊኒዬር እና ኩዋድራቲክ ፈንክሽን ቤተሰቦችን አልጀብራዊና ግራፋዊ በሆነ መንገድ መመርመርና መተንተን።
- አንድን የዳታ ስብስብ ወይም ተጨባጭ ሁኔታን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ቀጥተኛ ወይም ተቃራኒ ለውጥ መኖሩን በመወሰን እነዚህን ሁኔታዎች አልጀብራዊና ግራፋዊ በሆነ መንገድ ማስቀመጥ።
- ተጨባጭ መፍትሔዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ዳታ መሰብሰብና መተንተን፣ በተሻለ ተስማሚ የሆነውን ኢኩዌዥን ከርቭ መወሰንና ለሊኒዬርና ኩዋድራቲክ ፈንክሽንስ ትንበያ መስራት።

አልጀብራ I ኢንቴንሲፋይድ የሚማሩ ተማሪዎች ከላይ የቀረቡትን አርእስት በበለጠ ጥልቀትና ውስብስብነት ይማራሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች በተለያዩ ተጨማሪ አርእስት ላይ ልምድ የሚያዳብሩ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል:

- አብሶሉት ቫልዩ ኢኩዌዥንስ እና ኢንኢኩዋሊቲስ
- ራዲካል መግለጫዎችና ኢኩዌዥንስ
- ራሽናል መግለጫዎችና ኢኩዌዥንስ
- በግራፋዊና አልጀብራዊ መንገድ ከኩዋድራቲክስ ጋር የሚሰራ ተጨማሪ ስራ
- ተጨማሪ ተግባራትን መመርመር
- ኤክስፖነንሺያል ግሮውዝ እና ዲኬይ
- ፓይታጎሪያን ቴረም
- ርቀት እና አካፋይ ነጥብ
- ፐርሚዩቴሽንስ፣ ጥምረቶች፣ ጥምር ክስተቶች፣ የዳሰሳ ጥናቶች፣ እና ናሙናዎችን ጨምሮ ፕሮባብሊቲ።

የስታንዳርዶች ይዘት ሒሳብን ለመማር የሚከተሉትን የሒደት ግቦች ለማገዝ የታሰበ ነው፡- ችግር አፈታት፣ ተግባቦቶች፣ ትስስሮች፣ ውክልናዎችና ምክንያት አሰጣጥ።

*ማስታወሻ፡- ይህ ኮርስ ከፍተኛ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት አለው፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶች ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል፣ በተማሪው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕት ላይም ይጻፋል። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ ገጽ 56 እና APS PIP I-11.6.30 በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲቶች ላይ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ይመልከቱ።*

.

## ሳይንስ

### የ7ኛ ክፍል የሕይወት ሳይንስ (14115)

በ7ኛ ክፍል የሕይወት ሳይንስ ላይ ተማሪዎች፣ በህያው ዓለም ውስጥ ባለ ለውጥ፣ ዑደቶች፣ ቅጦች እና ግንኙነቶች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። በተጨማሪም፣ የሕይወት ሳይንስ ስታንዳርዶች የሳይንስን ተፈጥሮ በመገንዘብ ረገድ በተማሪ ዕድገት ላይ ማተኮራቸውን ይቀጥላሉ። ይህ ሳይንሳዊ እይታ የተፈጥሮ ማብራሪያዎች የሚደራጁበትና የሚሞከሩበት ምልከታ፣ ሙከራ፣ ሞዴሎች፣ ማስረጃ፣ እና ስልታዊ ሒደቶችን በመጠቀም ነው የሚለውን ሃሳብ ይገልጻል። ሳይንሳዊ ማብራሪያዎች በአመክንዮአዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን፤ በማስረጃ ሕግ የሚገዙ መሆናቸውን፤ ከምልከታ፣ ከማጣቀሻና ሙከራዊ ማስረጃ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን፤ ለምክንያታዊ ትችት ክፍት መሆናቸውን፤ አዳዲስ ሳይንሳዊ መረጃ ተጨምሮባቸው ለመጥራትና ለመቀየር እንደሚችሉ የሚያትቱ ጽንሰ ሃሳቦች በሳይንስ ተፈጥሮ ውስጥ ይካተታሉ። የሳይንስ ባህርይ ስለተፈጥሮ ማብራሪያዎችን መስጠት ይችላል፣ የእርምጃዎችን ተከታይ ውጤቶች ለመተንበይ ይችላል፣ *ነገር ግን ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ ሊያገለግል አይችልም።* ተማሪዎች ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ችግሮችን በማብራራት፣ ምርመራዎችን በማቀድና በማካሄድ (ኤስአይ - ዓለም አቀፍ የመለኪያዎች ሲስተምን በመጠቀም)፣ ዳታን በመተርጎም፣ በመተንተን እና በመገምገም፣ ማጠቃለያዎችን እና ማብራሪያዎችን በመገንባት እና በመተቸት፣ ሞዴሎችን በማዳበር እና በመጠቀም፣ እና መረጃን በማግኘት፣ በመገምገም እና ግንኙነት በመፍጠር የሳይንሳዊ እና የምህንድስና አሰራሮች ግንዛቤን ያሳያሉ። ተማሪዎች በሚጋሩት ፍላጎት ዙሪያ ፕሮጀክት ለመንደፍ በቡድን ውስጥ በመሥራት ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ሊዘጋጁ ይችላሉ።

ተማሪዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች ለመመርመርና ለመገንዘብ ይችላሉ:

- ሁሉም ሕያዋን ፍጥረታት በሴል ቲዮሪ እንደተገለጸው የሕይወትን ሂደቶች ከሚደግፉ ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ሕዋሶች የተውጣጡ መሆናቸውን፣
- በሕያዋን ነገሮች ውስጥ የመዋቅር አደረጃጀት ደረጃዎች እንዳሉ፣
- ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ የኃይል ማስተላለፍ ኬሚካላዊ ሂደቶች እንዳሉ፣
- ባዮቲክ እና ኤ-ባዮቲክ ምክንያቶች ሥነ ምህዳር ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ፣
- በባዮሎጂያዊ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች እርስ በርስ የሚገናኙ ከመሆኑም በላይ እርስ በርስ እንደሚደጋገፉ፣
- ከአዳዲስ ሁኔታዎች ጋር መላመድ አንድ ፍጥረት በሥነ ምህዳር ውስጥ ሕልውናውን እንዲጠብቅ እንደሚረዳ፣
- ሥነ ምህዳሮች፣ ማህበረሰቦች፣ ሕዝቦች እና ህዋሳት ተለዋዋጭ እና በጊዜ ሂደት የሚለወጡ መሆናቸውን፣
- በስርዓተ ምህዳር ዳይናሚክስ እና በሰዎች እንቅስቃሴ መካከል ግንኙነቶች መኖራቸውን፣
- ሕያው ነገሮች ራሳቸውን የሚያባዙ መሆናቸውንና ለአዳዲስ ትውልዶች የዘረ መል መረጃን እንደሚያስተላልፉ፣
- የፍጥረታት ብዛት ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊለወጥ እንደሚችል።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ስነ-ዜጋ እና ኢኮኖሚክስ (12355)

የ7ኛ ክፍል ዋና ጭብጥ ከሁኔታ ጋር መላመድ የሚል ነው። ተማሪዎች በስነ-ዜጋ እና በኢኮኖሚክስ ጥናት አማካይነት በአሜሪካ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ውስጥ የዜግነት ኃላፊነቶች፣ መብቶች እና ግዴታዎች እንዲሁም ተግባሩን ይመረምራሉ። ተማሪዎች የአካባቢ፣ የግዛት እና የብሔራዊ መንግስታትን አወቃቀር እና አሠራር በጥያቄ ላይ በተመሰረተ አቀራረብ ይመረምራሉ። ተማሪዎች በመንግስት እና በኢኮኖሚው መካከል ያለውን ግንኙነት ለመረዳትና ለመተንተን ዕውቀታቸውን እና ክህሎቶቻቸውን ይጠቀማሉ። ተማሪዎች በእውቀት ላይ የተመሠረተ እና ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ መሆን ምን ማለት እንደሆነ ግንዛቤ እንዲያዳብሩ የተማሩትን በተግባር ላይ ያውላሉ።

*ተማሪዎች፡-*

- ካርታዎችን፣ ሉሎችን፣ ፎቶዎች፣ ምስሎችን፣ ካርቱኖችንና ሰንጠረዦችን ይጠቀማሉ።
- ለታሪካዊ፣ ሲቪክና መልክዓ ምድራዊ ትንተና ክህሎቶችን በተግባር ያሳያሉ።
- የአሜሪካን ሕገ-መንግስታዊ መንግስት መሰረቶች ይገነዘባሉ።
- ዜግነት እና የዜጎች መብቶች፣ ግዴታዎች እና ኃላፊነቶችን ይገነዘባሉ።
- በሲቪክ ሕይወት ውስጥ አሳቢ እና ውጤታማ ተሳትፎን የሚያመቻቹ የግል ባህሪ ልዩ ጠባያትን ያሳያሉ።

በአካባቢ፣ በግዛት እና በብሔራዊ የመንግስት ደረጃዎች ያለውን የፖለቲካ ሂደት ይገነዘባሉ።
- የአሜሪካን ሕገ-መንግስታዊ መንግስት በብሔራዊ፣ በግዛት እና በአካባቢያዊ ደረጃዎች ይገነዘባሉ።
- በቨርጂኒያ ሕገ-መንግስት እና በአሜሪካ ሕገ-መንግስት የተቋቋሙትን የፍትህ ስርዓቶች ይገነዘባሉ።
- በአካባቢ፣ በግዛት እና በአገር አቀፍ ደረጃ የመንግስት ፖሊሲ እንዴት እንደሚቀረጽ ይገነዘባሉ።
- የዩናይትድ ስቴትስ ኢኮኖሚን፣ ውሳኔዎች በገቢያ ውስጥ እንዴት እንደሚከናወኑ እና መንግስት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ሚና ይገነዘባሉ።
- የግል ፋይናንስ እና የሥራ ዕድሎችን ይገነዘባሉ።

*የትምህርት ምዘና የሲቪክስና ኢኮኖሚክ ስታንዳርዶች በ7ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ የሚከናወኑ ናቸው።*

---

## የ7ኛ ክፍል በምርጫ የሚወሰዱና መሰረታዊ ያልሆኑ ኮርሶች

የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የተለያዩ አማራጭ ኮርሶች ይቀርቡላቸዋል። የኮርሶቹ ጥምረት ከእያንዳንዱ ት/ቤት የጊዜ መርሃ ግብር አንጻር ይለያያል። በምርጫ የሚሰጡ ኮርሶች በድሕረ ት/ቤት አክት II ፕሮግራም በኩል የሚቀርቡ ከሆነ ተማሪዎች በእነዚህ ኮርሶች ላይም ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ። (ገጽ 6ን ተመልከት)

**የስነ ጥበብ ትምህርት**
***ጊታር ሙሉ ዓመት* (19246)**
***ሴሚስተር* (19245)**

*ተማሪዎች፦*
- *የሙዚቃ መሳሪያ ትክክለኛ አጠቃቀምና አያያዝን በተግባር ያሳያሉ።*
- *ገላጭ የሆነ ድምፅ ለማውጣት ትክክለኛውን የአጨዋወት ቴክኒክ በተግባር ያሳያሉ።*
- *መቃኛ በመጠቀም የሙዚቃ መሳሪያውን ድምፅ የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ።*
- *የጊታር መሰረታዊያን ትውውቅና ስታንዳርድ የሙዚቃ ኖታዎችን አነባበብ በተመለከተ ግንዛቤ ይኖራቸዋል።*
- *ተቀዳሚ የህብረ ድምፅ መዋቅሮችንና ሃርመኒ ይጫወታሉ።*
- *መሰረታዊ የቀኝ እጅ ቴክኒኮችና ሜሎዲክ አቀራረብ ዘይቤዎችን ይጫወታሉ።*
- *በአነስተኛ ቡድኖች ለመጫወት ወይም ጊታርን በጋራ ለመጫወት አጽንኦት በመስጠት በዝግጅቶችና አቀራረቦች አማካይነት መማርን በተግባር ያሳያሉ።*

*ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍት መግዛትና አኩስቲክ (ፎልክ ወይም ክላሲካል) ጊታር ሊኖራቸው ይገባል። ውስን ቁጥር ያላቸው የት/ቤቱ ንብረት የሆኑ የሙዚቃ መሳሪያዎችን መከራየት ይቻላል።*

**በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃ**
ከእያንዳንዱ ትምህርት ክፍል ጊዜ ዓላማዎች መካከል ከታች የተዘረዘሩት ይገኙበታል። በእያንዳንዱ ት/ቤት ለእነዚህ የሙዚቃ ቡድኖች የየራሳቸው ስሞች ሊሰጣቸው ይችላል።

በ ***ጀማሪ ባንድ፣*** *ሙሉ ዓመት* **(19232)** *ተማሪዎች፡*
- *የሙዚቃ መሳሪያ ትክክለኛ አጠቃቀምና አያያዝን በተግባር ያሳያሉ።*
- *ገላጭ የሆነ ድምፅ ለማውጣት ትክክለኛውን የአጨዋወት ቴክኒክ በተግባር ያሳያሉ።*
- *ሙዚቃ ማንበብና ተጓዳኝ ሙዚቃዊ አተረጓጎም ለትክክለኛ ፒች፣ ቅኝት፣ የጊዜ አመልካች፣ የቁልፍ አመልካች፣ ቴምፖ እና ገላጭ ምልክቶችን ለማግኘት መሰረታዊነታቸውን ይገነዘባሉ።*
- *የአንድ ከግማሽ አክታቭና መሰረታዊ ነጥቦችን (የምት መሳሪያዎች) ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን ክህሎቶች የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል።*
- *መቃኛ በመጠቀም የሙዚቃ መሳሪያውን ድምፅ የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ።*
- *ርዝመታቸው ከ1 እስከ 2 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።*
- *ሜትሮኖም በመጠቀምና የባንድ መሪውን የሰውነት እንቅስቃሴ በመከተል ቀጥ ካለ ምት ጋር የጋራ ሙዚቃ ይጫወታሉ።*
- *በተለያዩ ዓይነቶች ዘይቤዎች በሚደረጉ ዝግጅቶችና ፐረዘንቴሽኖች አማካይነት የተማሩትን በተግባር ያሳያሉ።*

በ ***መካከለኛ ደረጃ ባንድ፣*** *ሙሉ ዓመት* **(19201)** *ተማሪዎች፡*
- *ለ7ኛ ክፍል ጀማሪ ደረጃ ባንድ እና/ወይም ለመካከለኛ ባንድ የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ክህሎት ይኖራቸዋል።*
- *የሙዚቃ ኖታዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ፣ በዚህም ውስጥ አርቲኩሌሽንስ፣ ኮምፓውንድ ሜትርስ፣ ንኡስ ክፍሎችና የቁልፍ አመልካቾችና በርካታ ድንገተኛዎች ይገኙበታል።*
- *የአንድ ከግማሽ አክታቭ ወይም የተሟሉ መሰረታዊ ነጥቦችን (የምት መሳሪያዎች) ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል።*
- *የሙዚቃ መሳሪያውን ቅኝት በጆሮ ሰምተው የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ።*
- *ርዝመታቸው ከ2-4 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።*
- *የቴምፖ፣ የአርቲኩሌሽን እና የዘይቤ ለውጦችን በተመለከተ ከባንዱ መሪ ለሚያዩት የሰውነት እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።*
- *የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ የአንደኛና ክፍል ስነ-ጽሑፍን በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።*
- *ከኮንሰርት ስነ-ጽሑፍ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ።*

በ ***ከፍተኛ ባንድ፣*** *ሙሉ ዓመት* **(19228)** *ተማሪዎች፦*
- *7ኛ ክፍል ለመካከለኛ ደረጃ ባንድ የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ክህሎት ይኖራቸዋል።*
- *የሙዚቃ ማስታወሻዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ፣ በዚህም ውስጥ ሌሎች ንኡስ ክፍሎች (ትሪፕሌትስ፣ ዱፕሌትስ፣ ሳይንኮፔሽን)፣ በሌሎች ቋንቋዎች ያሉ መግለጫ ምልክቶች ይገኙበታል።*
- *የአንድ ከግማሽ አክታቭ ወይም የተሟሉ መሰረታዊ ነጥቦችን (የምት መሳሪያዎች) ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን ክህሎቶች ለመዋሃድና ለማመጣጠን ከሚሰጥ ስሱነት ጋር የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል።*
- *የቁልፍ አመላካቾችን በመለየት ተጓዳኝ ስኬሉን በቁልፍ አመላካቾች ላይ እስከ 4 ከፍታዎች ወይም ውርዶች ድረስ መጫወት ይችላሉ።*
- *ርዝመታቸው ከ2-4 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።*
- *የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ የአንደኛና ሁለተኛ ክፍል ስነ-ጽሑፍን በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።*
- *ከኮንሰርት ስነ-ጽሑፍ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ።*

በ ***ጀማሪ ኦርኬስትራ፣*** *ሙሉ ዓመት* **(19237)** *ተማሪዎች፡*

- የሙዚቃ መሳሪያ ትክክለኛ አጠቃቀምና አያያዝንና አመታትን በተግባር ያሳያሉ።
- ፒዚካቶና መሰረታዊ የአመታት ቴክኒኮችን ጨምሮ ገላጭ የሆነ ድምፅ ለማውጣት ትክክለኛውን የአጨዋወት ቴክኒክ በተግባር ያሳያሉ።
- ሙዚቃ ማንበብና ተጓዳኝ ሙዚቃዊ አተረጓጎም ለትክክለኛ ፒች፣ ቅኝት፣ የጊዜ አመልካች፣ የቁልፍ አመልካች፣ ቴምፖ እና ገላጭ ምልክቶችን ለማግኘት መሰረታዊነታቸውን ይገነዘባሉ።
- አንድ ኦክታቭ (የመጀመሪያ አቀማመጥ) እና ጥንድ ማቆሚያዎችን በአንድ አውታር ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን ክህሎቶች የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል።
- መቃኛ በመጠቀም የሙዚቃ መሳሪያውን ድምፅ የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ።
- ርዝመታቸው ከ1 እስከ 2 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- ሜትሮኖም በመጠቀምና የባንድ መሪውን የሰውነት እንቅስቃሴ በመከተል ቀጥ ካለ ምት ጋር ይጫወታሉ።
- በተለያዩ ዓይነቶች ዘይቤዎች በሚደረጉ ዝግጅቶችና ፐረዘንቴሽኖች አማካይነት የተማሩትን በተግባር ያሳያሉ።

በ ***መካከለኛ ደረጃ ኦርኬስትራ፣*** ሙሉ ዓመት **(19242)** *ተማሪዎች*፡
- ለ7ኛ ክፍል ጀማሪ ኦርኬስትራ የተቀመጡ እና/ወይም ለመካከለኛ ደረጃ ኦርኬስትራ የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ክህሎት ይኖራቸዋል።
- የሙዚቃ ኖታዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ፣ በዚህም ውስጥ አርቲኩሌሽንስ፣ ኮምፓውንድ ሜትርስ፣ ንኡስ ክፍሎችና የቁልፍ አመልካቾችና ሁለት ከፍታዎች ይገኙበታል።
- ማራዘሚያዎችን በመጠቀምና የመምቻውን ክብደት፣ ፍጥነት፣ እና ንክኪ በመቆጣጠር በአንድ ተኩል ኦክታቭ ሬንጅ የመጫወት ክህሎትን ያዳብራሉ፤ እነዚህን ክህሎቶች የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል።
- የሙዚቃ መሳሪያውን ቅኝት በጆሮ ሰምተው የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ።
- ርዝመታቸው ከ2-4 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- የቴምፖ፣ የአርቲኩሌሽን እና የዘይቤ ለውጦችን በተመለከተ ከባንዱ መሪ ለሚያዩት የሰውነት እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።
- የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- ከኮንሰርት ስነ-ጽሑፍ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ።

በ ***በከፍተኛ ኦርኬስትራ፣*** ሙሉ ዓመት **(19243)** *ተማሪዎች*፡
- ለ7ኛ ክፍል መካከለኛ ደረጃ ኦርኬስትራ የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ክህሎት ይኖራቸዋል።
- የሙዚቃ ማስታወሻዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ፣ በዚህም ውስጥ ሌሎች ንኡስ ክፍሎች (ትሪፐሌትስ፣ ዱፐሌትስ፣ ሳይንኮፔሽን)፣ በሌሎች ቋንቋዎች ያሉ ጸያፍ ነገሮችና መግለጫ ምልክቶች ይገኙበታል።
- ማራዘሚያዎችን በመጠቀም የአንድ ከግማሽ ኦክታቭ ወይም የተሟሉ መሰረታዊ ነጥቦችን ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን ክህሎቶች ለመዋሃድና ለማመጣጠን ከሚሰጥ ስሱነት ጋር የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል።
- የቁልፍ አመላካቾችን በመለየት ተጓዳኝ ስኬሉን በቁልፍ አመላካቾች ላይ እስከ 2 ከፍታዎች እና 1 ውርድ ድረስ መጫወት ይችላሉ።
- ርዝመታቸው ከ2-4 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- ከኮንሰርት ስነ-ጽሑፍ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ።

***የጃዝ ባንድ፣ ሙሉ ዓመት*** **(19239)**
የጃዝ ሁኔታዊ ማሻሻያዎችን ለምሳሌ ብሉዝ፣ ፔንታቶኒክ እና ቤቦፕ ስኬሎችን፣ የህብረ ድምጽ ምልክቶችን፣ የህብረ ድምጽ ለውጦችን መሰረታዊ ጉዳዩና ከእነዚህ የሙዚቃ አላባውያን ተነስቶ የአንድ ሰው ዝግጅት የማድረግ ጽንሰ ሃሳቦችን ይማራሉ። በትልቅ ባንድ እና/ወይም በአነስተኛ የጥምር ስብስብ ላይ ዝግጅት ያቀርባሉ።

**የቴአትር ጥበባት**
***ሙሉ ዓመት*** **(11391)**
**ሴሚስተር (11392)**
*ተማሪዎች፡-*
- ደረጃቸውን የጠበቁ የቴአትር ኦዲሽን ሒደቶችን፣ የቃል ጥናት ልምምዶችንና ቴክኒካዊ ፕሮዳክሽኖችን ይለማመዳሉ።
- ድራማዊ ጽሑፎችን ለዝግጅት አቀራረብ መነሻ አድርገው መተንተንና መገምገም ይችላሉ።
- የገጸ ባህርያትን አካላዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ገጽታዎች ያካትታሉ።
- የዳሬክተሮችንና ተዋንያንን የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት ተገንዝበው ይተገብራሉ።
- በቴአትር ፕሮዳክሽኖች ላይ የማኔጅመንቱን ተግባራት ለይተው ይገነዘባሉ።
- ከሌሎች ጋር በመተባበር አርቲስቲክ ዲስፐሊን አዘጋጅተው ይተገብራሉ።

**ቪዥዋል አርትስ I**
***ሙሉ ዓመት*** **(19040)**
**ሴሚስተር (19041)**
*ተማሪዎች፡-*
- የዲዛይን መርሆዎችና የጥበብን አላባውያን በመተግበር የጥበብ ስራዎችን ይፈጥራሉ።
- የተለያዩ ቴክኒኮችንና ሒደቶችን በማቀናጀት ባለ ሶስት አቅጣጫ ስራዎችን ይፈጥራሉ።
- የተለያዩ የጥበብ ስራዎች ላይ ግላዊ ትርጓሜዎችንና የሒሲና ፍርድን ይሰጣሉ።
- የጥበብን ቃላት በመጠቀም ያለቁ የጥበብ ስራዎችን መተንተንና መተቸት ይችላሉ።
- በጥበብ አዘገጃጀት ላይ ስነ-ምግባራዊ ውሳኔዎችን ማስረዳትና መተግበር ይችላሉ።

***የድምፅ ሙዚቃ***
ከእያንዳንዱ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ዓላማዎች መካከል ከታች የተዘረዘሩት ይገኙበታል። በእያንዳንዱ ት/ቤት ለእነዚህ የሙዚቃ ቡድኖች የየራሳቸው ስሞች ሊሰጣቸው ይችላል።

*በ **ጀማሪ ኦርኬስትራ፣*** ሙሉ ዓመት **(19261)** ሴሚስተር **(19264)** *ተማሪዎች*፡
- ጥሩ የድምፅ ቃና ለማውጣት የሚያስፈልግ ትክክለኛ የሰውነት አቋም፣ የትንፋሽ ቁጥጥር እና የአፍ ቅርጽን በተግባር ያሳያሉ።
- ሙዚቃ ማንበብና ተጓዳኝ ሙዚቃዊ አተረጓጎም ለትክክለኛ ፒች፣ ቅኝት፣ የጊዜ አመልካች፣ የቁልፍ አመልካች፣ ቴምፖ እና ገላጭ ምልክቶችን ለማግኘት መሰረታዊነታቸውን ይገነዘባሉ።

- ዲያቶኒክ ፒች ሲስተምን በመጠቀምና በስብስቡ ውስጥ የተወሰነ ክፍልን በመያዝ በትክክል ፒችን የማዛመድ ችሎታን ያዳብራሉ።
- ርዝመታቸው ከ1 እስከ 2 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- የባንድ መሪው ለሚያሳየው የአካል እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።
- በክፍል ደረጃ I ወይም II ላይ እንዳግባብነቱ በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።

በ ***መካከለኛ ደረጃ ኦርኬስትራ፣*** ሙሉ ዓመት **(19274)** ሴሚስተር **(19275)** ተማሪዎች:

- በ *ጀማሪ የሙዚቀኞች ስብስብ* ውስጥ የዳበሩ ክህሎቶችን ማሳደጋቸውን ይቀጥላሉ።
- በትሬብል ክሌፍ ውስጥ ያሉ የሙዚቃ ኖታዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ።
- በጉርምስና ዕድሜ ምክንያት ስለሚከሰት የድምፅ ለውጥና በእነዚህም ምክንያት በሬንጅ እና በድምፅ ቃና ከለር ላይ የሚፈጠሩ ለውጦችን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ይማራሉ።
- ባለ ሁለት እና ሶስት ክፍል ሃርመኒ እና ካፔላ ውስጥ ሲመዘገቡ ራሳቸውን ችለው የመቆም ችሎታን ያዳብራሉ።
- ጆሮ እና ድምፅ ከፒች ጋር እንዲጣጣምና በህብረ ድምጽ ውስጥ እንዲቆይ ለማድረግ ቅኝታቸውን ማዳበር።
- ርዝመታቸው ከ2-4 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- ለፌርማታ፣ አክስሌራንዶ እና ሪታርዳንዶ የባንድ መሪ ለሚያሳየው የሰውነት እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።
- የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ የሁለተኛና ሶስተኛ ክፍል ስነ-ጽሑፍን በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- በደረጃ I ሳይት ንባብ።

በ ***ከፍተኛ ኦርኬስትራ፣*** ሙሉ ዓመት **(19285)** ተማሪዎች:

- በትሬብልና ባስ ክሌፍ ውስጥ የሙዚቃ ኖታን በመረዳት ምላሽ ይሰጣሉ።
- ሰፊ በሆነ ሬንጅ ውስጥ የመዝፈን ክህሎትን በላቀ የነጻነት መንፈስ ማሳደግና እነዚህን ክህሎቶች የሙዚቃ ባንድ አካል ሆኖ በተግባር ማሳየት።
- ባለ ሶስትና አራት ክፍል ስነ-ጽሑፍ ላይ በካፔላ ዘፈን የተጣራ የፒች ማዛመድ ማስተካከያዎችን ለማድረግ የሚያስችል ችሎታን ያዳብራሉ።
- ርዝመታቸው ከ4-8 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- የቴምፖ፣ የአርቲኩሌሽን እና የዘይቤ ለውጦችን በተመለከተ ከባንዱ መሪ ለሚያዩት የሰውነት እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።
- የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ የ3ኛና 4ኛ ክፍል ስነ-ጽሑፍን በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- ከኮንሰርት ስነ-ጽሑፍ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ።

**ቢዝነስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ**

**ዲጂታል የግቤት ቴክኖሎጂዎች**

***ሙሉ ዓመት*** **(16607)**

**ሴሚስተር (16617)**

ዲጂታል የግቤት ቴክኖሎጂዎች አዳዲስና በቅርብ የመጡ የግቤት መሳሪያዎችን (ለምሳሌ:- የንግግርና የእጅ ጽሑፍን ማወቂያ ሶፍትዌሮች፣ ታብሌቶች፣ ክላውድ ኮምፒዩተር መተግበሪያዎች፣ የጆሮ ማዳመጫዎች/ማይክሮፎን፣ ስካነር፣ ዲጂታል ካሜራ፣ ዲጂታል የቪድዮ ካሜራዎች፣ የሞባይል መሳሪያዎች፣ የኮምፒዩተር ሲስተሞች) በማስተዋወቅ ተማሪዎች በስራ ቦታና በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ እየተለመዱ የመጡ መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ ያዘጋጃቸዋል።
ተማሪዎች:-

- በመንካት የመጻፍ ቴክኒኮችን በማሳደግ የኪቦርድ አጻጻፍ ፍጥነታቸውንና ትክክለኛነታቸውን ያሻሽላሉ።
- የዴስክቶፕ ፐብሊሽንግ አቅሞችን ጨምሮ የወርድ ፕሮሰሲንግ ሶፍትዌርን ሁሉንም አቅሞችና መለያ ባህርያት ተምረው ተግባራዊ ያደርጋሉ።
- አዲስ መልእክት የመጻፍና የማረም እንደዚሁም ወርድ ፕሮሰሲንግን ተጠቅመው ለአካዳሚክ ክፍሎች ሰነዶችን የማዘጋጀት ክህሎታቸውን ያሻሽላሉ።
- የቢዝነስና የግል ደብዳቤዎች፣ ኤንቨሎፕስ፣ ስፕሬድሽት፣ ቻርቶች፣ ሪፖርቶች፣ የሴሚስተር ወረቀቶችና የቢሮ ውስጥ መጻጻፊያዎችን ጨምሮ የተለያዩ ኤሌክትሮኒክ ሰነዶችን መጻፍና ቅርጸቱን ማስተካከል ይችላሉ።
- የተለያዩ ዓይነት የስራ ዘመን አማራጮችን በማፈላለግ ስራ ለመቀጠር ስለሚያስፈልጉ ክህሎቶች ማለትም የግል ታሪክ መረጃ አዘገጃጀትና የቃለ መጠይቅ አደራረግ ክህሎቶችን በተመለከተ ግንዛቤ ይኖራቸዋል።
- በአሜሪካ የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ ስለ ቢዝነስ ባለቤትነትና የቢዝነስ ተግባራት መረጃን ያስሳሉ።
- የግል በጀት መያዝ፣ የተንቀሳቃሽ ሒሳብን ማመዛዘን፣ የክፍያ ቼክን ምንነት መፍታት፣ ኢንሹራንስና መኪናን መግዛት፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ቤት መምረጥ፣ ኢንቨስት ማድረግና ሌሎች ከሸማቾች ጋር የተያያዙ ክህሎቶች ላይ ፕሮጀክቶችን ያጠናቅቃሉ።
- ለአዳዲስና በቅርብ ለተጀመሩ ቴክኖሎጂዎች (የስክሪን ላይ አጻጻፍ፣ ንግግርን ማወቂያ፣ iPads እና የሞባይል ቴክኖሎጂዎች) የስራ ቦታ መተግበሪያዎች ላይ ውይይት ያደርጋሉ።

**እንግሊዝኛ**

**የ7ኛ ክፍል የንባብ ስትራቴጂዎች**

***ሙሉ ዓመት*** **(11111)**

*የመምህር እና/ወይም የአማካሪ ምክረ ሃሳቦች*

የንባብ ስትራቴጂስ 7 ስፔሻላይዝድ የሆነ በምርጫ የሚወሰድ የእንግሊዝኛ ኮርስ ሲሆን ተማሪዎች መሰረታዊ የእውቀት ማዳበሪያ ክህሎቶችን ለመለማመድ ታላሚ የግንዛቤ መፍጠሪያ መመሪያና ተጨማሪ ጊዜ ይሰጣቸዋል። መምህራን ግልጽ መመሪያ የሚሰጡት ወሳኝ በሆኑ የንባብ ክፍሎች ላይ በማተኮር ነው:- ፎኒክስ፣ ፎነሚክ እውቀት፣ አንደበተ ርቱዕነት፣ የቃላት ግንባታና አንብቦ መረዳት። ከእነዚህ ወሳኝ የኮርስ ክፍሎች በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ ተማሪ የንባብ ስኬት ግቦችን ከማሳካት አንጻር ያሳየውን እምርታ ለመለካት በተወሰነ ወቅት ምዘናዎች ይካሄዳሉ። ተማሪዎች በተናጠልና በአነስተኛ ቡድን ውስጥ ሆነው በመስራት:-

- ንቁ የሆኑ የንባብ ስትራቴጂዎችን መማርና መለማመድ ይችላሉ።
- ስርዓት ባላቸው የትምህርት ልማዶች (ግልጽና ስልታዊ የማመስጠር/ኮድ የመፍታት ስራ) ውስጥ ይሳተፋሉ
- የንባብና የአጻጻፍ ጽናትና ርቱዕነት ያዳብራሉ።
- የቃላትን ብዛት ይጨምራሉ።
- አንብቦ መረዳትን ያሻሽላሉ።
- የንባብ ልምዳቸውን ያሰፋሉ።

***ጋዜጠኝነት***

***ሙሉ ዓመት*** **(11201)**

ይህ በምርጫ የሚወሰድ ኮርስ ተማሪዎች የጋዜጣ ወይም የኦዲዮ/ቪድዮ ዜና ስርጭት እንዲያዘጋጁ ይጠይቃል። ተማሪዎች በስራቸው አማካይነት ስለ ጋዜጣና ብሮድካስቲንግ አጻጻፍና አዘገጃጀት ይማራሉ።

*ተማሪዎች፡-*

- የጋዜጠኝነት ዘዴዎችን ተምረው ጥቅም ላይ ያውላሉ።
- የሕትመት እና/ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስቶችን ይዘትና ቴክኒካዊ ጥራት ይተነትናሉ።
- ኤዲቶሪያሎች፣ ፊቸሮችና ስፖርት ጨምሮ የዜና ጽሑፎችን ይጽፋሉ እና/ወይም የንግድ ማስታወቂያዎች፣ የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያዎችን ወይም የዜና ሾው፣ የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያዎችና የንግድ ማስታወቂያዎችን ጨምሮ አጫጭር የብሮድካስት መልእክቶችን ይጽፋሉ።
- የተለያዩ የጋዜጠኝነት ስራ ተግባራትን ለምሳሌ አርትኦት፣ የምስል ንድፍና ኮፒ፣ አርእስት፣ የስክሪፕት ዝግጅት አጻጻፍና የመጨረሻ ፕሮዳክሽን ይለማመዳሉ።

**የሚድያ ጋዜጠኝነት**

**ሴሚስተር (11204)**

ይህ በምርጫ የሚወሰድ ኮርስ ተማሪዎችን የተለያዩ አዳዲስ የሚድያ ጋዜጠኝነት መስኮችን መተርጎምንና ማዘጋጀትን እንዲያውቁ ያደርጋል። እነዚህ የተግባቦት መድረኮች በውስጣቸው ዲጂታል ቪድዮ፣ ዲጂታል ፎቶግራፊ፣ ዲጂታል ሙዚቃና ኦንላይን ሕትመትን ያካትታሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች የቨርጂኒያ የትምህርት ስታንዳርዶች ተግባቦትና መልቲሞዳል ግንዛቤን ይዳስሳሉ።

*ተማሪዎች፡-*

- የሁሉንም ዓይነት የሚድያ ጋዜጠኝነት ይዘትና ቴክኒካዊ ብቃት ይተነትናሉ።
- የአዲስ ሚድያ ይዘትን ምሳሌዎች ያቀርባሉ።
- ለእውነተኛ አንባቢ የሚሆን ስራን ኦንላይን ያሳትማሉ (በጦማሮችና በድረ ገጾች አማካይነት)
- iPads እና ሌሎች ዝግጁ የሆኑ የሚድያ መሳሪያዎችን በመጠቀም የዲጂታል ሚድያ ፕሮዳክሽን መሰረታዊ ጉዳዮችን ይማራሉ።
- የሚድያ እውቀት መሰረቶችን ይገነዘባሉ።

**የቤተሰብና የሸማች ሳይንሶች**

**የአፍላ ወጣት አኗኗር**

**ሴሚስተር (18207)**

የአፍላ ወጣት አኗኗር ዝግጁ በሆኑ ፕሮጀክት ተኮር መመሪያ አማካይነት የተለያዩ የኑሮ ሁኔታዎች ለሚጠይቁት ነገር ግላዊ ኃላፊነት መውሰድ ላይ አጽንኦት ይሰጣል።

*ተማሪዎች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ፡-*

- ግለሰባዊ ዕድገት።
- ግላዊ አካባቢያቸውን ማስጠበቅ።
- የስነ-ምግብና የጤናማነት ልማዶችን መተግበር።
- የሸማቾችና የቤተሰብ ሐብቶችን ማስተዳደር።
- የጨርቃ ጨርቅ፣ ፋሽንና የልብስ ምርቶችን ማዘጋጀት።
- ከቤተሰብና ሸማቾች ሳይንስ ጋር የተያያዙ የስራ ዘመን መረጃዎችን መዳሰስ።

በዚህ ኮርስ ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት እንዳግባብነቱ ለሳይንስ ቴክኖሎጂ፣ ለኢንጂነሪንግ፣ እና ሒሳብ (STEM) ጽንሰ ሃሳቦች ትኩረት ይሰጣል።

**ሒሳብ**

**የሒሳብ ስትራቴጂስ ለ7ኛ ክፍል**

***ሙሉ ዓመት* (13117)**

**ሴሚስተር (13120)**

የስትራቴጂስ ኮርስ በክፍል ደረጃ ሒሳብ ላይ ስኬታማ ለመሆን ተጨማሪ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በአማራጭነት የሚሰጥ ኮርስ ነው። በስትራቴጂስ ኮርስ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የመነሻ እውቀትን ያዳብራሉ፣ ስለይዘቱ ተጨማሪ ጽንሰ ሃሳባዊ አቀራረቦችን ይለማመዳሉ፣ መሰረታዊ የኮርሱን ይዘት ይበልጥ በጥልቀት ያጎለብታሉ።

**የልዩ ፍላጎት ትምህርት**

**ትምህርታዊ ጥናቶች**

***ሙሉ ዓመት* (10028)**

*በቅድሚያ የሚወሰድ፡- ተማሪው የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት መሆኑ መለየት አለበት*

በተማሪው ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) መሰረት የኮርስ ስራ ግለሰባዊ የሚደረግ ሲሆን፣ የእያንዳንዱን ተማሪ አጠቃላይ የትምህርት ኮርሶችን ፍላጎትንም ያጠናክራል። በተጨማሪም፣ የማዳመጥ ክህሎቶች፣ የመጻፍ ክህሎቶች፣ የአደረጃጀትና አጠቃላይ የጥናት ክህሎቶች አጽንኦት ይሰጣቸዋል።

**ማህበራዊ ክህሎቶች፣ *ሙሉ ዓመት* (10023)**

*በቅድሚያ የሚወሰድ፡- ተማሪው የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት መሆኑ መለየት አለበት*

የማሕበራዊ ክህሎቶች ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ደረጃ ተማሪው ከሌሎች ሰዎች ጋር ተገቢነት ያላቸውን ማሕበራዊ ተግባቦቶች ለማድረግ የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን የመቅሰምና የመተግበር ዕድልን ይሰጠዋል። በትምህርትነት ከሚሰጡ ክህሎቶች መካከል ከሌሎች ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ አተያይን ማዳበር፣ የራስን ዕድል በራስ መወሰን፣ ከቡድኖች ጋር መስራት፣ ጫና እና ስልቹነትን የመቋቋሚያ ስትራቴጂዎች እና ለማሕበራዊ ጠባይ "ያልተጻፉ ደንቦችን" መገንዘብ ይገኙበታል። ድርጅታዊና ለራስ የመሟገት ክህሎቶችን ማዛመድም ይሸፈናሉ።

**የተማሪ ድጋፍ**

**ኮር ፕላስ (Core Plus)**

***ሙሉ ዓመት* (11129)**

**ሴሚስተር (11128)**

ይህ ኮርስ የተቀረጸው የአጠቃላይ ትምህርት ተማሪ ሆኖ ስለ አደረጃጀት፣ ማስታወሻ አያያዝ፣ ፈተና አወሳሰድና ተማሪዎች ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያግዟቸውን ሌሎች ቴክኒኮች በተመለከተ ተጨማሪ ለማወቅ ለሚፈልግ ተማሪ ነው።

*ተማሪዎች፡-*

- የራሳቸውን የጥናት ጊዜ መርሃ ግብር ያቅዳሉ።
- የማዳመጥ ክህሎቶችን ለማሻሻል የሚያስችሉ መንገዶችን ይማራሉ።
- በአሁኑ ጊዜ የት/ቤት ስራዎችን በተመለከተ ያሉ አመለካከቶችን ይገመግማሉ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በመለየትና ግቦችን በማስቀመጥ አዎንታዊ የሆኑትን ማጎልበት ይጀምራሉ።
- የተጻፈ ማቴሪያልን ለመገንዘብና ይዞ ለመቆየት የሚያስችል የጥናት ክህሎት ቀመርን ይጠቀማሉ።

**የቴክኖሎጂ ትምህርት**

**አዳዲስ ፈጠራዎችና ኢኖቬሽንስ**

***ሙሉ ዓመት* (18464)**

**ሴሚስተር (18433)**

ተማሪዎች በታሪክ፣ በተራቀቀ ማህበረሰብ ላይ ተጽእኖ ያሳደሩና ዓለማችንን የቀየሩ ወሳኝ የፈጠራ ስራዎችና የኢንጂነሪንግ ስኬቶችን ይመረምራሉ። ግለሰቦች፣ ማህበረሰቦችና ዓለም ላይ የተጋረጡ ዘመን አመጣሽ የቴክኖሎጂ ጉዳዮችና ችግሮችን በመፈተሽ መፍትሄ ለማቅረብ፣ አዳዲስ ነገር ለመፍጠርና አዳዲስ ምርቶችን ለማፍለቅ ስልታዊ የዲዛይንና የማጎልበቻ አሰራሮችን ይተገብራሉ። የክፍል ትምህርቶች የሚታቀዱትና የሚዘጋጁት ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ እና ሒሳብ (STEM) ለማካተት በሚያስችል መልኩ ነው።

*ተማሪዎች፡-*

- የኢንጂሪንግ ችግር ፈቺ ሒደትን ተገንዝበው ተግባራዊ ያደርጋሉ።
- ቴክኖሎጂ በሰው ልጅ ታሪክ እመርታ ውስጥ ያለውን ሚና እና ተጽእኖ ይመረምራል።
- ታሪክ ቀያሪ ቴክኖሎጂያዊ መሻሻሎችና የኢንጂነሪንግ ስኬቶችን ይመረምራሉ
- የቴክኖሎጂና የኢንጂነሪንግ ስኬቶችን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎች ይመዝናሉ።
- ችግሮችን በመፍታትና ፕሮቶታይፖችን በመፍታት ረገድ የቡድን ስራንና ትብብርን ይለማመዳሉ።
- የፕሮዳክሽን ላብራቶሪውን መሳሪያዎች፣ ማሽኖችና ዕቃዎች በትክክልና ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ያንቀሳቅሳሉ።
- የዲዛይን ፕሮቶታይፖችን በመገንባት ወቅት መሳሪያዎችና የማምረት ሒደቶችን ይመርጣሉ።
- የተሻለውን ሃሳብ የመምረጥ ግብን በመያዝ አማራጭ መፍትሔዎችን መርምረው፣ የመመዘንና የመገምገም ስራ ይሰራሉ።
- የፈጠራ ሃሳብን መገንባትና እንዴት እንደሚሰራ በሚገባ ለመግለጽ በተግባር ያሳያሉ።
- በንድፎች፣ ባለ ብዙ ዕይታ ስእሎችና በኮምፒዩተር የሚታገዝ የዲዛይን ሶፍትዌርን በመጠቀም ሃሳቦችን ማስተላለፍ ይችላሉ

**የዓለም ቋንቋዎች**

በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ የሚማሩ የ7-12ኛ ክፍል ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውንና የዓለም ቋንቋዎችን በማጥናታቸው የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የዓለም ቋንቋ ክሬዲት ሊያገኙ ይችላሉ። የዓለም ቋንቋዎች ክሬዲት ለማግኘት፣ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው:-

- ለእያንዳንዱ ክሬዲት ቢያንስ የ140 ሰዓት መደበኛ የቋንቋ ትምህርት ስለመማሩ የሚያረጋግጥ ትራንስክሪፕት መቅረብ አለበት።
- ተማሪው የማለፊያ ነጥብ ያገኘ መሆን አለበት።
- ተማሪው በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ በቋንቋው ለመቀጠል ከፈለገ፣ በኮርሱ ያገኘው ውጤት “C” ወይም የተሻለ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።
- በፈተና ምዘና በግዛት ደረጃ የተፈቀደ ክሬዲት ተወስዶ ተማሪውም እስከ አራት ክሬዲት ሊያስገኝለት የሚችል የብቃት ደረጃ ያሳዩ መሆን አለበት።

በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ በትምህርትነት የሚሰጡ ሌሎች ቋንቋዎችን የሚናገሩ ተማሪዎች ለምደባ ፈተና ከአማካሪዎች ጋር መመካከር አለባቸው።

*የአድቫንስድ ስተዲስ ዲፕሎማ ለማግኘት የሚፈልጉ ተማሪዎች በአንድ ቋንቋ የሶስት ዓመት/ደረጃ ወይም በሁለቱ ቋንቋዎች የሁለት ዓመት ጥናት በማጠናቀቅ የዓለም ቋንቋ መስፈርቶችን ማሟላት ይችላሉ። እያንዳንዱን የዓለም ቋንቋ ኮርስ በሚገባ ማጠናቀቅ ለአድቫንስድ ስተዲስ ዲፕሎማ አንድ ክሬዲት ያስገኛል። አንዳንድ ኮሌጆች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቆይታን ለመቀጠል የዓለም ቋንቋዎችን ማጥናትን ይጠይቃሉ። ተማሪዎ የፍሬሽማን ዓመቱን እንዳጠናቀቀ ሶስት ዓመት የሚፈጅ ትምህርትን ካጠናቀቀ፣ ተማሪው የመረጠውን ኮሌጅ(ጆች) የመግቢያ መስፈርቶች ማየትዎን ያረጋግጡ።*

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ (ASL) በቨርጂኒያ ዩኒቨርሲቲና የማህበረሰብ ኮሌጅ የመግቢያ መስፈርቶች ውስጥ እንደ ዓለም ቋንቋ ሊቆጠር ይችላል። ከግዛቱ ውጭ ያሉ አንዳንድ ድሕረ ሁለተኛ ደረጃ ተቋማት ASL እንደ ዓለም ቋንቋ አይቆጥሩትም። ASL ዓለም አቀፍ የባካሎሪያ ቋንቋ አይደለም።**

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ I (15990)**
***ሙሉ ዓመት፣ አንድ ክሬዲት***
*በቅድሚያ የሚወሰድ:- ምንም*

ተማሪዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር በቤት፣ በት/ቤትና በማህበረሰብ አካባቢዎች ውስጥ በሚያደርጉት ዕለታዊ መስተጋብር አውድ ውስጥ መቀበያ እና ገላጭ ቋንቋን ይማራሉ። ተማሪዎች ስለ ቤተሰብ፣ ስለ ት/ቤት ዝግጅቶችና ስለ በዓላት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስን ይማራሉ። ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን መለዋወጥ ይችላሉ ለምሳሌ ራስን ማስተዋወቅ፣ ፈቃድ መጠየቅ፣ ትኩረት ማግኘትና አግባብነት ያላቸውን ማንዋል ያልሆኑ ባህሪያትን (ለምሳሌ:- የፊት ገለጻ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ስፓሻል አደረጃጀት) በመጠቀም የመፈረሚያ አካባቢን መደራደር ይችላሉ። ተማሪዎች የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን ታሪክ ተምረው መስማት የተሳናቸውን ሰዎች ባህል ያጠናሉ።

**አረብኛ I**
***ሙሉ ዓመት* (15800)**

ይህ ደረጃ ተማሪዎች የአረብኛ ፊደላትንና የድምፅ ስርዓትን እንዲያውቁ ያስችላል። ይህ ኮርስ በባህላዊና ታሪካዊ መረጃዎች በጣም የበለጸገ ነው። የአረብኛ ቋንቋ፣ የአረብኛ ቋንቋ የዘር ግንድና ስክሪፕት ታሪክ ይሰጣሉ። በድምፅና በአጻጻፍ ስርዓቶች ላይ መጀመሪያ ከሚሰጠው ትኩረት በተጨማሪ፣ ተማሪዎች ድምፆችን መማርና ማራባት፣ ለአካሄዶች አጽንኦት መስጠትና ስለቋንቋው የድምፅ ቃና ይማራሉ። መሰረታዊ የሰዋሰው አወቃቀሮችና የቃላት ብዛት የሚተዋወቁ ሲሆን፣ ይህም የሚደረገው ተማሪዎች በጣም መሰረታዊ የሆኑ መደበኛ የመልእክት ልውውጦችን በቀላል ዓረፍተ ነገሮችና የመልእክት ልውውጦች ለደረጃው አግባብነት ባላቸው አውዶች መግለጽ ይችላሉ። ተማሪዎች የሚነበቡላቸውን ቃላትና ዓ.ነገሮች በትክክል መጻፍ ይችላሉ፣ ከዚህ በፊት የተማሯቸውን ቃላትና ዓ.ነገሮች ማንበብ፣ ለሌሎች ሰዎች ሰላምታ መስጠትና ራስን ማስተዋወቅ፣ ቀላል ጥያቄዎችና መልሶችን ማዘጋጀት፣ መሰረታዊ ማህበራዊ ተግባቦቶች ውስጥ መሳተፍ፣ ስለራሳቸው፣ ስለቤተሰብ አባላቶቻቸውና ስለሌሎች ሰዎች መናገርና መሰረታዊ የሆኑ ግላዊ መረጃዎችን መለዋወጥ ይችላሉ። ቋንቋ የሚዳብርበት መሰረታዊ ርእስ የግልና የቤተሰብ ሕይወት ነው።

**ቻይንኛ I**
***ሙሉ ዓመት* (15615)**

ተማሪዎች መሰረታዊ የቋንቋ አወቃቀሮችን የያዙ ቀላል ዓ.ነገሮችን በመጠቀም ስለራሳቸውና በቅርባቸው ስላለ አካባቢ መልዕክት የማስተላለፍ ችሎታቸውን ያዳብራሉ። ይህ የመልዕክት ልውውጥ በአራቱም የቋንቋ ክህሎቶች ውስጥ ይንጸባረቃል:- ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ፤ በቃልና በጽሑፍ መልእክት ለመግለጽ ችሎታም አጽንኦት ይሰጠዋል። ተማሪዎች የግልና የቤተሰብ ሕይወት፣ የት/ቤት ሕይወት፣ ማሕበራዊ ሕይወትና የማህበረሰብ ሕይወትን በተመለከተ መዳሰስና ማጥናት ይጀምራሉ።

**ፈረንሳይኛ I**
***ሙሉ ዓመት* (15110)**

ቋንቋውን የመማር ትኩረት በተጨባጭ ሕይወት፣ በውይይቶች፣ ስኪትስና ሌሎች ፈጠራዊና ተጨባጭ ተግባራት አማካይነት ቋንቋውን ስራ ላይ ማዋል ነው። ተማሪዎች በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብና በመጻፍ ተግባራት አማካይነት ክህሎታቸውን ያዳብራሉ፣ መሰረታዊ መዋቅሮችና የቃላት ብዛታቸውን ያሳድጋሉ።

*ተማሪዎች:-*

- ሰላምታዎች፣ ስንብቶችና የአክብሮት መግለጫዎችን ይጠቀማሉ።
- ስለ ጓደኞች፣ ስለቤተሰብና ት/ቤት በሚደረግ መሰረታዊ ጭውውት ላይ ይሳተፋሉ።
- በሚያውቁት ማቴሪያል ላይ ተመስርተው ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ ይችላሉ።
- የምግብ ዝርዝሮች፣ ምልክቶች፣ የጊዜ መርሃ ግብሮችና ሌሎች እውነተኛ ማቴሪያሎችን ያነብባሉ።
- አጫጭር መግለጫዎች፣ መልዕክቶችና የተመሩ ድርሰቶችን ይጽፋሉ።
- በተደራሹ ቋንቋ ባሕሎች ዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ስላሉ ገጽታዎች ይማራሉ።

**ላቲን I**

**ሙሉ ዓመት (15310)**

በዚህ የመጀመሪያ የላቲን ኮርስ፣ ተማሪዎች ከጥንታዊ ሮም ቋንቋና ሕይወት ጋር ይተዋወቃሉ። የላቲን I ተቀዳሚ ዓላማ የንባብ ክህሎቶችን ማዳበር ሲሆን፣ ይህም በማዳመጥ፣ መናገርና መጻፍ ክህሎቶች የሚደገፍ ነው።

*ተማሪዎች፡-*

- ውርስ የላቲን ትረካዎችና ቀላል ኦሪጂናል ላቲን ያነብባሉ።
- የላቲን አነጋገርን መሰረታዊ ክፍሎች ይገነዘባሉ።
- መሰረታዊ የላቲን ቃላት ግንባታን ይማራሉ።
- የላቲን ስሞችና ግሶች መጨረሻና ተግባራቶቻቸውን ይማራሉ።
- የጀማሪ ላቲን ሰዋሰውን መሰረታዊ ግንዛቤ ያዳብራሉ።
- የላቲን ስርወ ቃላት፣ ቅድመ ቅጥያዎችና ድሕረ ቅጥያዎችን በማጥናት በላቲን እና በእንግሊዝኛ ውስጥ የቃላት ግንባታን እውቀት ይጨምራሉ።
- ስለ ሮማውያን ዕለታዊ ሕይወት፣ ልማድ፣ መንግስትና አፈ ታሪክ ይማራሉ።

**ስፓኒሽ I**

**ሙሉ ዓመት (15510)**

ቋንቋውን የመማር ትኩረት በተጨባጭ ሕይወት፣ በውይይቶች፣ ስኪትስና ሌሎች ፈጠራዊና ተጨባጭ ተግባራት አማካይነት ቋንቋውን ስራ ላይ ማዋል ነው። ተማሪዎች በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብና በመጻፍ ተግባራት አማካይነት ክህሎታቸውን ያዳብራሉ፣ መሰረታዊ መዋቅሮችና የቃላት ብዛታቸውን ያሳድጋሉ።

*ተማሪዎች፡-*

- ሰላምታዎች፣ ስንብቶችና የአክብሮት መግለጫዎችን ይጠቀማሉ።
- ስለ ጓደኞች፣ ስለቤተሰብና ት/ቤት በሚደረግ መሰረታዊ ጭውውት ላይ ይሳተፋሉ።
- በሚያውቁት ማቴሪያል ላይ ተመስርተው ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ ይችላሉ።
- የምግብ ዝርዝሮች፣ ምልክቶች፣ የጊዜ መርሃ ግብሮችና ሌሎች እውነተኛ ማቴሪያሎችን ያነብባሉ።
- አጫጭር መግለጫዎች፣ መልዕክቶችና የተመሩ ድርሰቶችን ይጽፋሉ።
- በተደራሹ ቋንቋ ባሕሎች ዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ስላሉ ገጽታዎች ይማራሉ።

**ስፓኒሽ I፣ ኢንቴንሲፋይድ**

**ሙሉ ዓመት (15516)**

*በቅድሚያ የሚወሰድ፡- ጊዜያዊ የስፓኒሽ ኮርስ ትውውቅ ወይም ከመምህር የሚሰጥ የድጋፍ ደብዳቤ*

ስፓኒሽ I ኢንቴንሲፋይድ የሚማሩ ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚሰጥ የውጭ ቋንቋ (FLES) ፕሮግራም ውስጥ ቢያንስ ለሶስት ዓመት የተሳተፉና የመሸጋገሪያ ስፓኒሽ ወይም የስፓኒሽ መግቢያ ኮርስን ያጠናቀቁ ናቸው። የዚህ ኮርስ ግብ ተማሪዎች ከዚህ በፊት በተማሩት የስፓኒሽ ጥናት መሰረት ደረጃው ከፍ ያለ ብቃት እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። ስርዓተ ትምህርቱ በስፓኒሽ I ውስጥ የተቀመጡትን ሁሉንም ዓላማዎች የሚያሳካ ሲሆን ጠንከር ያለ ይዘትና ተጨማሪ አድቫንስድ አርእስትን ያቀርባል። ይህ ኮርስ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው የቃል ተግባቦት ክህሎቶችን ለማዳበርና የስፓኒሽ ቋንቋ ተናጋሪ ሃገራትን ባህላዊ አተያዮችና ልማድ በበለጠ ጥልቀት ለማጥናት ነው።

**ስፓኒሽ አቀላጥፈው ለሚናገሩ I**

**ሙሉ ዓመት (15517)**

*በቅድሚያ የሚወሰድ፡- በመምህሩ በሚወሰነው መሰረት በስፓኒሽ ንግግር ልህቀትን በተግባር ማሳየት*

ይህ ኮርስ የተቀረጸው በስፓኒሽ ቋንቋ አፍ መፍቻ ቋንቋ በሚመስል ደረጃ ብቃት ኖሯቸው በስፓኒሽ መሰረታዊ የንባብና የመጻፍ ክህሎቶችን በላቀ ብቃት ማከናወን ላልቻሉ ተማሪዎች ነው። ተማሪዎች በንባብ፣ በአጻጻፍና በንግግር ላይ የተግባቦት ክህሎታቸውን በማዳበር የስፓኒሽ ሰዋሰው ማጥናት ይጀምራሉ። ተማሪዎች ስለሂስፓኒክ ባሕል አተያዮችና ልማዶች ጥልቅ ግንዛቤ ያዳብራሉ።

**ስፓኒሽ አቀላጥፈው ለሚናገሩ II፣**

**ሙሉ ዓመት (15527)**

*በቅድሚያ የሚወሰድ፡- ስፓኒሽ አቀላጥፈው ለሚናገሩ I በሚገባ ማጠናቀቅ ወይም በምደባ ፈተና በሚወሰነው መሰረት በቋንቋው ተመጣጣኝ ብቃት ያለው መሆን አለበት*

ይህ ኮርስ የተዘጋጀው ቀደም ሲል በመሰረታዊ ደረጃ ስፓኒሽ ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ተማሪዎች ነው። ተማሪዎች የቃላት አጻጻፋቸውንና ሜካኒክስ በማሻሻል አጫጭር ድርሰቶችን ይጽፋሉ። ወጥ ስራዎችን ማንበብና ትረካዎችና ግጥሞችን መተርጎም እና/ወይም መተንተን ይጀምራሉ። የሰዋሰው ጥናት ይቀጥላል። ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚኖራቸው ፕረዘንቴሽንና ሌሎች የእርስ በርስ ተግባራት አማካይነት የቃል ተግባቦት ክህሎታቸውን ያሻሽላሉ። ባህላዊ አተያዮች ልማዶች ይፈተሻሉ፣ በስነ-ጽሑፍ አውድ በኩልም ጥልቅ የሆነ ግንዛቤ ይፈጠራል።

---

**8ኛ ክፍል መሰረታዊ ስርዓተ ትምህርት**

*ማስታወሻ፡- ከ15 ተማሪ በታች ያላቸው ኮርሶች በተማሪ ፍላጎትና በበጀት ታሳቢ ሁኔታዎች መሰረት ላይሰጡ ይችላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በበጀት ምክንያት የተነሳ ኮርሶች በአንድ የተወሰነ ዓመት ላይሰጡና በዚህ ምክንያት ተማሪዎቹ አማራጭ ኮርስ እንዲመርጡ ሊገደዱ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በቂ የተመዘገቢ ቁጥር የሌላቸው ኮርሶች በርቀት ወይም በኦንላይን ትምህርት አማካይነት ሊሰጡ ይችላሉ።*

**የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት**

**የ8ኛ ክፍል እንግሊዝኛ (11120)**

በሁሉም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርትስ ፕሮግራም የሚያተኩረው በቨርጂኒያ የትምህርት እንግሊዝኛ መስፈርቶች ላይ በተገለጸው መሰረት በአራት ማደራጃ አርእስት ላይ ነው፡- ኮሙኒኬሽንና መልቲሞዳል ሊትሬሲ፣ ንባብ፣ መጻፍ እና ምርምር። በእነዚህ መስኮች ላይ ብቁ መሆን ተማሪው የላቀ አስተሳሰብ እንዲኖረውና በት/ቤት ውስጥም ሆነ ከት/ቤት ውጭ ስኬታማ እንዲሆን ያስችለዋል።

ስርዓተ ትምህርት በጽንሰ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ማዕቀፍን የሚከተል ሲሆን፣ የሚያተኩረውም በዘላቂ ግንዛቤዎችና ወሳኝ ጥያቄዎች ላይ ነው።

- ልቦለዳዊና ኢ-ልቦለዳዊ ጽሑፎችን በማነጻጸር ለአንብቦ መረዳት ቀጣይነት ያለው አጽንኦት ይሰጠዋል። በልቦለዳዊ ጽሑፎች ውስጥ፣ ተማሪዎች ዋና ሃሳብ የተዘጋጀበትን ሁኔታ ያስረዳሉ፣ የደራሲውን ዘይቤም ያወዳድራሉ/ያነጻጽራሉ። ለኢ-ልቦለድ ንባብ የበለጠ አጽንኦት የሚሰጥ ሲሆን ተማሪዎችም የደራሲዎችን ብቃት፣ እይታ እና ዘይቤ ይተነትናሉ።
- ተማሪው የቃላት መነሻ፣ ስርወ ግንድ፣ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺን ማጥናቱን ይቀጥላል።
- ተማሪው በተለያዩ መልኮች ጽሑፍ ማቀድ፣ ማርቀቅ፣ መከለስና ማረም የሚችሉ ሲሆን ለገላጭና አሳማኝ አጻጻፍ ትኩረት ይደረጋል። ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሑፍ መግለጫ በመጻፍ አቋማቸውንም በምክንያትና በማስረጃ ይከላከላሉ የመልስ መልስም ይሰጣሉ።

- ተማሪዎች የሚዲያ መልዕክቶችን ይገመግማሉ፣ ይተነትናሉ፣ ያዘጋጃሉና ያቀርባሉ። ተማሪዎች የተለያዩ ዕይታዎችን የሚያካትቱ መልቲሞዳል ፕረዘንቴሽንስ ያዘጋጃሉ።
- ተማሪዎች ከሌሎች ጋር በመተባበር ሃሳቦችን ይለዋወጣሉ፣ ውሳኔዎችን ያሳልፋሉ፣ ግቦችን ያሳካሉ፣ ችግሮችንም ይፈታሉ።
- ተማሪው የግንዛቤ ችግሮችንና አድሎአዊ ሁኔታዎችን በመለየት ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን የምርምር ቴክኒኮችን ተግባራዊ ያደርጋል። ተማሪዎች የ MLA ወይም APA ዘይቤን በመጠቀም የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ምንጮችን ይጠቀማሉ። የሌላ ሰውን ስራ የራስ አስመስሎ ማቅረብ ምንነትና ለሚያስከትላቸው ውጤቶች አጽንኦት ይሰጣል።

**የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት**
**የ8ኛ ክፍል የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት (17200)**

ሁሉም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፋሉ። የጤና ትምህርት ፕሮግራም አጽንኦት የሚሰጠው ተማሪዎች ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ለማሳካት ምን ማወቅ፣ መገንዘብና ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ነው። የጤና ትምህርት ተማሪዎች ስለ በሽታ መነሻዎችና መንስኤዎችን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላል። ተማሪዎች የጤና ምርጫዎችን ተከታይ ውጤቶች በማስተሳሰር የጤና ክህሎቶችን በግላዊ፣ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ አድቮኬሲ ላይ መተግበር ይጀምራሉ። ከጥናት መስኮች መካከል ስሜታዊ፣ አእምሯዊ፣ ማሕበራዊ እና የአካባቢ ጤና፣ ደህንነትና የአጣዳፊ ሁኔታ ዝግጁነት፣ ግንኙነቶች፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነትና በሽታ መከላከልና የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ይገኙበታል። የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ከተሻሻለ የእንቅስቃሴ መልክ ወደ ውስብስብ ትግበራ ያሸጋግራል። ተማሪዎች ስለ ሰውነታቸው አወቃቀርና ስርዓት እንደዚሁም ስለ ሰውነት እንቅስቃሴ ያላቸውን እውቀት ይተገብራሉ። ተማሪዎች ጤና ነክ ብቃትን ለማሻሻል ግቦችን አስቀምጦ እመርታውን ይከታተላሉ። ተማሪዎች በተለያዩ ስፖርቶች/ተግባራት ላይ ያላቸውን ችሎታ በተመለከተ በመመዝገብ በዕድሜ ልክ ተግባራት ላይ ብቃታቸውን ማስፋት ይጀምራሉ።

**ሒሳብ**
**ቅድመ አልጀብራ ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች (13112)**
ቅድመ አልጀብራ ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ይዘትን በጥልቀት እንዲማሩ የሚያስችል መሰረታዊ ኮርስ ነው።
የ8ኛ ክፍል ስታንዳርዶች ትኩረት ተማሪዎች በአልጀብራ I ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ በብቃት መማር የሚገባቸው የአልጀብራ መሰረቶች ላይ ነው። ተማሪዎች በእነዚህ መስኮች ላይ ግንዛቤን ያዳብራሉ፡-

1. ቁጥር እና ቁጥርን መረዳት
2. ስሌትና ግመታ
3. ልኬት
4. ፕሮባብሊቲ እና ስታስቲክስ
5. ፓተርኖች፣ ተግባራትና አልጀብራ

በተጨማሪም፣ የስታንዳርዶች ይዘት ሒሳብን ለመማር የሚከተሉትን የሒደት ግቦች ለማገዝ የታሰበ ነው፡- ችግር አፈታት፣ ተግባቦቶች፣ ትስስሮች፣ ውክልናዎችና ምክንያት አሰጣጥ።

የቨርጂኒያ የ8ኛ ክፍል ትምህርት ደረጃዎች የይዘት ክፍሎች ተጨማሪ ውስን ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-
- ስሌትንና በስርዓቱ ንዑስ ስብስቦች መመደብን ጨምሮ የተጨባጭ ቁጥር ስርዓት።
- የሸማቾች መተግበሪያዎችን የሚያካትቱ ተጨባጭ መልመጃዎች።
- በማዕዘን ዝምድና ላይ ተመስርተው የማይታወቁ ማዕዘናትን ልኬት መወሰን።
- የተለያዩ ምስሎችን መጠንና ስፋት የሚመለከቱ ተጨባጭ መልመጃዎችን መፍታት፣ የተለዋዋጭ ባህርያትን ውጤቶች ትንተና እና መግለጫን ጨምሮ።
- ትርጉሞችን፣ የሃሳብ ገለጻዎችና ዲላቴሽን ጨምሮ ትራንስፎርሜሽኖችን መተግበር።
- ከተለያዩ እይታዎች አንጻር ባለ ሶስት አቅጣጫ ሞዴሎችን መገንባት።
- የፓይታጎሪያን ቴረምን መተግበርና ማጣራት።
- ኮምፖዛይት ምስሎች ያሉባቸውን ተጨባጭ የስፋትና የፔሪሜትር መልመጃዎችን መፍታት።
- የኢ-ጥገኛና ጥገኛ ክስተቶችን ፕሮባብሊቲ ማነጻጸርና ፕሮባብሊቲዎችን ማስላት።
- ቦክስ ፕሎትስ፣ ስካተርፕሎትስ መግለጽ፣ መታዘብና ለመደምደሚያ መነሻ ማድረግ፣ ማነጻጸርና መተንተን።
- የአልጀብራ አገላለጾችን መገምገምና ማቅለል።
- በአንድ ተግባር ውስጥ ያለ ግንኙነትን መወሰንና ዶሜይንና ሬንጅን እና ጥገኛና ኢ-ጥገኛ ተለዋዋጮችን መወሰን።
- ስሎፕን መለየትና መተርጎም እንደዚሁም የተሰጠ ዋጋ ተግባርን ማስቀምና በቃላዊ መግለጫዎች፣ ሰንጠረዦች፣ ኢኩዌሽኖችና ግራፎች መካከል ትስስር መፍጠር።
- በአንድ ወይም በሁለቱም በኩል በአንድ ተለዋዋጭ ላይ ያሉ ባለ ብዙ ደረጃ ሊኒየር ኢኩዌዥኖችና ኢንኢኩዋሊቲስን ተጨባጭ የመልመጃ መተግበሪያን በመጠቀም መፍታት።

**አልጀብራ I (13130)**
አልጀብራ I መሰረታዊ ኮርስ ሆኖ ለ6ኛና 7ኛ ክፍሎች የቨርጂኒያ የትምህርት ደረጃዎች ከፍተኛ ብቃትን ላሳዩና ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ለቅድመ አልጀብራ ተጨማሪ ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ሁሉም ተማሪዎች ይዘቱ ላይ ጥልቀት ያለው አሰጣጥን የሚከተል ነው (VDOE Math 8)።
አልጀብራ የሚወስዱ ተማሪዎች በእነዚህ መስኮች ላይ ግንዛቤን ያዳብራሉ፡-

1. አገላለጾችና ኦፕሬሽኖች
2. ኢኩዌዥንስና እና ኢንኢኩዋሊቲስ
3. ተግባራት
4. ስታስቲክስ

በተጨማሪም፣ የስታንዳርዶች ይዘት ሒሳብን ለመማር የሚከተሉትን የሒደት ግቦች ለማገዝ የታሰበ ነው፡- ችግር አፈታት፣ ተግባቦቶች፣ ትስስሮች፣ ውክልናዎችና ምክንያት አሰጣጥ።
የቨርጂኒያ አልጀብራ I ትምህርት ደረጃዎች የይዘት ክፍሎች ተጨማሪ ውስን ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-
- ቃላዊና አሃዛዊ ሁኔታዎችን በአልጀብራዊ መንገድ በመወከል አገላለጾችን ይገመግማሉ።
- በፖሊኖሚያልስ ላይ ኦፕሬሽኖችን በማካሄድ የኤክስፖነንቶች፣ ኦፕሬሽኖችና ፋክተሪንግ ሕጎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ።
- ስኩዌር ሩቶችን እና ኪዩብ ሩቶችን ያቃልላሉ።
- ባለ ብዙ ደረጃ ኢኩዌዥኖችን በአንድ ተለዋዋጭ አልጀብራዊ በሆነ መንገድ መፍታት፤ በዚህም ውስጥ ሊኒዬር፣ ኩዋድራቲክ እና ሊትራል ሆነው ለተጨባጭ መልመጃ አፈታት አጽንኦት ይሰጣል።
- ሁለት ሊኒዬር ኢኩዌዥንስ ያሉባቸውን ሲስተሞች በሁለት ተለዋዋጮች በግራፍና በአልጀብራ መፍታት።
- የኢንኢኩዋሊቲስ ሲስተሞችን ጨምሮ የሊኒዬር ኢንኢኩዋሊቲስ ሶሉሽን በሁለት ተለዋዋጮች በግራፍ ማስቀመጥ።

- ስሎፐ መወሰን፣ ኢኩዌዥኖችን መጻፍና ሊኒዬር ኢኩዌዥኖችን በሁለት ተለዋዋጮች በግራፍ ማስቀመጥ።
- ሊኒዬር እና ኩዋድራቲክ ፈንክሽን ቤተሰቦችን አልጀብራዊና ግራፋዊ በሆነ መንገድ መመርመርና መተንተን።
- አንድን የዳታ ስብስብ ወይም ተጨባጭ ሁኔታን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ቀጥተኛ ወይም ተቃራኒ ለውጥ መኖሩን በመወሰን እነዚህን ሁኔታዎች አልጀብራዊና ግራፋዊ በሆነ መንገድ ማስቀመጥ።
- ተጨባጭ መፍትሔዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ዳታ መሰብሰብና መተንተን፣ በተሻለ ተስማሚ የሆነውን ኢኩዌዥን ከርቭ መወሰንና ለሊኒዬርና ኩዋድራቲክ ፈንክሽንስ ትንበያ መስራት።

*ማስታወሻ፡- ይህ ኮርስ ከፍተኛ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት አለው፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶች ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል፣ በተማሪው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕት ላይም ይጻፋል። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ ገጽ 56 እና APS PIP I-11.6.30 በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲቶች ላይ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ይመልከቱ።*

### አልጀብራ I፣ ኢንቴንሲፋይድ (13140)

አልጀብራ I ኢንቴንሲፋይድ መሰረታዊ ኮርስ ሆኖ ለ6ኛ፣ 7ኛና 8ኛ ክፍሎች የቨርጂኒያ የትምህርት ደረጃዎች ከፍተኛ ብቃትን ላሳዩና ተጨማሪ አድቫንስድ አርእስትን ለማጥናት ዝግጁ ለሆኑ ሁሉም ተማሪዎች ይዘቱ ላይ ጥልቀት ያለው አሰጣጥን የሚከተል ነው።

አልጀብራ I ኢንቴንሲፋይድ የሚወስዱ ተማሪዎች በእነዚህ መስኮች ላይ ግንዛቤን ያዳብራሉ፡-

1. አገላለጾችና ኦፐሬሽኖች
2. ኢኩዌዥንስና እና ኢንኢኩዋሊቲስ
3. ተግባራት
4. ስታስቲክስ

በተጨማሪም፣ የስታንዳርዶች ይዘት ሒሳብን ለመማር የሚከተሉትን የሒደት ግቦች ለማገዝ የታሰበ ነው፡- ችግር አፈታት፣ ተግባቦቶች፣ ትስስሮች፣ ውክልናዎችና ምክንያት አሰጣጥ።

የቨርጂኒያ አልጀብራ I ኢንቴንሲፋይድ ትምህርት ደረጃዎች የይዘት ክፍሎች ተጨማሪ ውስን ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- ቃላዊና አሃዛዊ ሁኔታዎችን በአልጀብራዊ መንገድ በመወከል አገላለጾችን ይገመግማሉ።
- በፖሊኖሚያልስ ላይ ኦፐሬሽኖችን በማካሄድ የኤክስፖነንቶች፣ ኦፐሬሽኖችና ፋክተሪንግ ሕጎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ።
- ስኩዌር ሩቶችን እና ኪዩብ ሩቶችን ያቃልላሉ።
- ባለ ብዙ ደረጃ ኢኩዌዥኖችን በአንድ ተለዋዋጭ አልጀብራዊ በሆነ መንገድ መፍታት፤ በዚህም ውስጥ ሊኒዬር፣ ኩዋድራቲክ እና ሊትራል ሆነው ለተጨባጭ መልመጃ አፈታት አጽንኦት ይሰጣል።
- ሁለት ሊኒዬር ኢኩዌዥንስ ያሉባቸውን ሲስተሞች በሁለት ተለዋዋጮች በግራፍና በአልጀብራ መፍታት።
- የኢንኢኩዋሊቲስ ሲስተሞችን ጨምሮ የሊኒዬር ኢንኢኩዋሊቲስ ሶሉሽን በሁለት ተለዋዋጮች በግራፍ ማስቀመጥ።
- ስሎፐ መወሰን፣ ኢኩዌዥኖችን መጻፍና ሊኒዬር ኢኩዌዥኖችን በሁለት ተለዋዋጮች በግራፍ ማስቀመጥ።
- ሊኒዬር እና ኩዋድራቲክ ፈንክሽን ቤተሰቦችን አልጀብራዊና ግራፋዊ በሆነ መንገድ መመርመርና መተንተን።
- አንድን የዳታ ስብስብ ወይም ተጨባጭ ሁኔታን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ቀጥተኛ ወይም ተቃራኒ ለውጥ መኖሩን በመወሰን እነዚህን ሁኔታዎች አልጀብራዊና ግራፋዊ በሆነ መንገድ ማስቀመጥ።
- ተጨባጭ መፍትሔዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ዳታ መሰብሰብና መተንተን፣ በተሻለ ተስማሚ የሆነውን ኢኩዌዥን ከርቭ መወሰንና ለሊኒዬርና ኩዋድራቲክ ፈንክሽንስ ትንበያ መስራት።

አልጀብራ I ኢንቴንሲፋይድ የሚማሩ ተማሪዎች ከላይ የቀረቡትን አርእስት በበለጠ ጥልቀትና ውስብስብነት ይማራሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች በተለያዩ ተጨማሪ አርእስት ላይ ልምድ የሚያዳብሩ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል፡-

- አብሶሉት ቫልዩ ኢኩዌዥንስ እና ኢንኢኩዋሊቲስ
- ራዲካል መግለጫዎችና ኢኩዌዥንስ
- ራሽናል መግለጫዎችና ኢኩዌዥንስ
- በግራፋዊና አልጀብራዊ መንገድ ከኩዋድራቲክስ ጋር የሚሰራ ተጨማሪ ስራ
- ተጨማሪ ተግባራትን መመርመር
- ኤክስፖነንሺያል ግሮውዝ እና ዲኬይ
- ፓይታጎሪያን ቴረም
- ርቀት እና አካፋይ ነጥብ
- ፐርሚዩቴሽንስ፣ ጥምረቶች፣ ጥምር ክስተቶች፣ የዳሰሳ ጥናቶች፣ እና ናሙናዎችን ጨምሮ ፐርባብሊቲ።

*ማስታወሻ፡- ይህ ኮርስ ከፍተኛ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት አለው፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶች ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል፣ በተማሪው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕት ላይም ይጻፋል። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ ገጽ 56 እና APS PIP I-11.6.30 በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲቶች ላይ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ይመልከቱ።*

### ጂኦሜትሪ፣ ኢንቴንሲፋይድ (13141)

ጂኦሜትሪ ኢንቴንሲፋይድ መሰረታዊ ኮርስ ሆኖ አልጀብራ I ኢንቴንሲፋይድን በሚገባ ላጠናቀቁ ሁሉም ተማሪዎች ይዘቱ ላይ ጥልቀት ያለው አሰጣጥን የሚከተል ነው።

የቨርጂኒያ ጂኦሜትሪ ትምህርት ደረጃዎች የይዘት ክፍሎች ተጨማሪ ውስን ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- በተወሰነ ሃሳብና ሁኔታ ውስጥ አመክንዮአዊ ክርክርን ቅቡልነት ለማደራጀትና ለመገመት የሚያበቃ ምክንያታዊ አሰጣጥ።
- ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የጎንዮሽ መስመሮችን ለማረጋገጥ በሁለት ማዕዘናት መካከል በሁለት መስመሮች የተፈጠረውን ግንኙነት መጠቀምና ተጨባጭ መልመጃዎችን መፍታት።
- ሲሜትሪ እና ትራንስፎርሜሽን የሚያካትቱ መልመጃዎችን መፍታትና በዚህም ውስጥ ርቀት፣ አካፋይ ነጥብ፣ ስሎፐና ትርጉሞችን በኮኦርዲኔት ዘዴዎች አማካይነት መጠቀም።
- የተለያዩ ግንባታዎችን መገንባትና ምክንያታዊ ማድረግ።
- የጎን እና/ወይም የማዕዘን ልኬቶችን በሶስት ማዕዘናት ውስጥ ያለውን ርዝመት የሚመለከት መረጃ በመጠቀም ተጨባጭ መልመጃዎችን መፍታት።
- ሁለት ሶስት ማዕዘናት ተስማሚ ወይም ተመሳሳይ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- ፓይታጎሪያን ቴረም፣ ልዩ የቀኝ ሶስት ማዕዘናትና ትራይጎኖሜትሪክ ጥምርታዎችን ጨምሮ የቀኝ ሶስት ማዕዘናትን የያዙ ተጨባጭ መልመጃዎችን መፍታት።
- የኩዋድሪላተራልስ ጠባያትን መልመጃዎች ለመፍታት ማጣራትና መጠቀም።
- የኮንቬክስ ፖሊገንስ ማዕዘናትን በመጠቀም ተጨባጭ መልመጃዎችን መፍታት።
- የክበባትን ጠባያት በተጨባጭ መልመጃዎች ላይ መተግበር።
- የክበባትን ኢኩዌዥንስ የሚመለከቱ መልመጃዎችን መፍታት።
- ባለ ሶስት አቅጣጫ ጂኦሜትሪክ ስእሎችን ስፋትና መጠን መጠቀም።

በተጨማሪም፣ የስታንዳርዶች ይዘት ሒሳብን ለመማር የሚከተሉትን የሒደት ግቦች ለማገዝ የታሰበ ነው፡- ችግር አፈታት፣ ተግባቦቶች፣ ትስስሮች፣ ውክልናዎችና ምክንያት አሰጣጥ።

*ማስታወሻ፡- ይህ ኮርስ ከፍተኛ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት አለው፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶች ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል፣ በተማሪው*

*የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕት ላይም ይጻፋል። ለተጨማሪ መረጃ አባከዎ ገጽ 56 እና APS PIP I-11.6.30 በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲቶች ላይ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ይመልከቱ*

**ሳይንስ**

**የ8ኛ ክፍል አካላዊ ሳይንስ (14125)**

በ8ኛ ክፍል አካላዊ ሳይንስ ወቅት ተማሪዎች ስለ ቁስ አካልና አወቃቀር እና ስለ ኃይል ባህሪያት ጥልቅ ግንዛቤ ያገኛሉ። የአካላዊ ሳይንስ ስታንዳርዶች ቀጣይ ትኩረት ተማሪው የሳይንስን ተፈጥሮ በተመለከተ ግንዛቤው ማደጉ ላይ ነው። ይህ ሳይንሳዊ እይታ የተፈጥሮ ማብራሪያዎች የሚደራጁበትና የሚሞከሩበት ምልከታ፣ ሙከራ፣ ሞዴሎች፣ ማስረጃ፣ እና ስልታዊ ሒደቶችን በመጠቀም ነው የሚለውን ሃሳብ ይገልጻል። ሳይንሳዊ ማብራሪያዎች በአመክንዮአዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን፤ በማስረጃ ሕግ የሚገዙ መሆናቸውን፤ ከምልከታ፣ ከማጣቀሻና ሙከራዊ ማስረጃ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን፤ ለምክንያታዊ ትችት ክፍት መሆናቸውን፤ አዳዲስ ሳይንሳዊ መረጃ ተጨምሮባቸው ለመተራትና ለመቀየር እንደሚችሉ የሚያትቱ ጽንሰ ሃሳቦች በሳይንስ ተፈጥሮ ውስጥ ይካተታሉ። የሳይንስ ባህርይ ስለተፈጥሮ ማብራሪያዎችን መስጠት ይችላል፣ የእርምጃዎችን ተከታይ ውጤቶች ለመተንበይ ይችላል፣ *ነገር ግን ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ ሊያገለግል አይችልም*። ተማሪዎች ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ችግሮችን በመለየት፣ እቅድ በማውጣት እና ምርመራዎችን በማካሄድ፣ መረጃዎችን በመተርጎም፣ በመተንተን እና በመገምገም፣ ማጠቃለያዎችን እና ማብራሪያዎችን በመገንባት እና በመተቸት፣ ሞዴሎችን በማዳበር እና በመጠቀም እንዲሁም ተማሪዎች መረጃን በማግኘት፣ በመገምገም እና ግንኙነት በመፍጠር የሳይንሳዊና የምህንድስና አሰራሮች ግንዛቤን ያሳያሉ። በተጨማሪም ተማሪዎች ራሱን የቻለ የሙከራ ወይም የምህንድስና ዲዛይን ፕሮጀክት ያጠናቅቃሉ።

ተማሪዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች ለመመርመርና ለመገንዘብ ይችላሉ፡

- ቁስ አካል በአተሞች የተዋቀረ ነው፣
- ቁስ አካላት ባህሪያት አሏቸው እንዲሁም በኬሚካል እና በአካላዊ ሂደቶች ይጠበቃሉ፣
- ፔሬዲክ ቴብል በአቶሚክ አወቃቀራቸው ላይ በመመርኮዝ ኤለመንቶችን ለማደራጀት የሚያገለግል ሞዴል ነው፣
- ኃይል ይቆጠባል፣
- ሞገዶች በኃይል እንቅስቃሴ ውስጥ አስፈላጊ ናቸው፣
- የኤሌክትሮማግኔቲክ ጨረር ባህሪዎች አሉት፣
- ሥራ፣ ኃይል እና እንቅስቃሴ ይዛመዳሉ፣
- የኤሌክትሪሲቲና የማግኔቲዝም መሰረታዊ መርሆዎች አሉ።

**ማህበራዊ ጥናቶች**

**የዓለም ጂኦግራፊ (12210)**

የዚህ ኮርስ ትኩረት የዓለም ሕዝቦች፣ ቦታዎችና አካባቢዎችን በማጥናት ለዓለም አካባቢዎች አጽንኦት መስጠት ነው። የኮርሱ እውቀት፣ ክህሎቶችና አተያዮች የሚያተኩሩት በዓለም ሕዝብና ባህላዊ መገለጫ ባህርያት፣ የመሬት አቀማመጥና የአየር ፀባይ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት፣ ፍልሰትና የሰፈራ አካሄዶች ላይ ነው። ስፓሽያል የጂኦግራፊ ፅንሰ ሃሳቦች በሰው ልጆችና በአካባቢያቸው መካከል የሚደረጉ ትስስሮችን ለማጥናት በማዕቀፍነት ያገለግላሉ። ተማሪዎች ጂኦግራፊያዊ ግብዓቶችን በመጠቀም የመጠየቅ፣ የምርምርና የቴክኖሎጂ ክህሎቶችን ተግባራዊ አድርገው ጂኦግራፊያዊ ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ ይችላሉ። ተማሪዎች ጂኦግራፊያዊ ፅንሰ ሃሳቦችን ተገንዝበው በዕለታዊ ሕይወታቸው ላይ ለመተግበራቸው ልዩ አጽንኦት ይሰጠዋል።

የ8ኛ ክፍል መሪ ቃል ተግባቦት የሚል ነው። ዓላማዎቹ እንደ አፍሪካ፣ አንታርክቲካ፣ ኤዥያ፣ አውስትራሊያ፣ ማዕከላዊ አሜሪካ፣ ካሪቢያን፣ አውሮፓ፣ መካከለኛው ምስራቅ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ እና የቀድሞዋ ሶቪዬት ሕብረት በመሳሰሉ የዓለም አካባቢዎች በሚኖሩ ሰዎችና በአካባቢያቸው መካከል የሚደረግ ተግባቦት ነው። ይዘቱ የሚዘጋጀው በአድራሻ፣ ቦታ፣ በሰዎችና በአካባቢ መካከል በሚደረጉ ግንኙነቶች፣ ዝውውርና ክልሎች አበይት ፅንሰ ሃሳቦች ዙሪያ ላይ ነው።

*ተማሪዎች፡-*

- የጂኦግራፊያዊ ትንተና ክህሎቶችን ያዳብራሉ።
- ካርታዎችን፣ ሉሎችን፣ ፎቶዎችና ምስሎችን ይጠቀማሉ።
- የተመረጡ አካላዊና ስነ-ምህዳራዊ ሒደቶች የመሬትን ገጽታ እንዴት እንደሚቀይሩ ይተነትናሉ።
- የክልልን ጽንሰ ሃሳብ ይተገብራሉ።
- ላቲን አሜሪካና ካሪቢያን፣ አውሮፓ፣ ዩናይትድ ስቴትስና ካናዳ፣ ሰሜን አፍሪካና ደቡብ ምስራቅ ኤዥያ፣ ምስራቅ ኤዥያ፣ አውስትራሊያ እና የፓሲፊክ ደሴቶች እና አንታርክቲካን ጨምሮ የዓለም አካባቢዎች ያሉበትን አካባቢና አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መገለጫ ባህርያትን ይተነትናሉ።
  አፍሪካ እና ደቡብ ምስራቅ እስያ፣ ምስራቅ እስያ፣ አውስትራሊያ እና የፓስፊክ ደሴቶች፣ እና አንታርክቲካ።
- የሰዎችን ስርጭት፣ የዕድገት መጠንና መገለጫ ባህርያት ከአሰፋፈር ሁኔታዎችና የተፈጥሮና የካፒታል ሐብቶች አድራሻ አንጻር ማወዳደርና ማነጻጸር ይችላሉ።
- በሰዎች ፍልሰትና የባህል ተግባቦት ውስጥ ያሉ የበፊትና የአሁን አዝማሚያዎችን በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ከሚያሳድርበት ተጽእኖ አንጻር መተንተን ይችላሉ።
- ተፈጥሯዊ፣ ሰብዓዊና ካፒታል ሐብቶችን በመለየት አስፈላጊነታቸውን ያስረዳሉ።
- ባደጉትና በታዳጊ ሃገራት መካከል ያለውን ልዩነት በማስቀመጥ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ደረጃን ከኑሮ ደረጃና ከኑሮ ጥራት ጋር ያስተሳስራሉ።
- በኢኮኖሚያዊ መስክ አንዱ በሌላኛው ላይ ያለውን ጥገኝነት ዓለም አቀፍ ዝንባሌዎችና ኔትወርኮች ይተነትናሉ።
- የግጭትና የትብብር ሃይሎች የመሬት አካል ክፍፍልና ቁጥጥር ላይ የሚኖራቸውን ውጤት ይተነትናሉ።
- የከተማ ልማት አካሄዶችን ይተነትናሉ።
- ጂኦግራፊን በመተግበር የበፊቱን ይተረጉማሉ፣ የአሁኑን ይረዳሉ፣ የወደፊቱን ያቅዳሉ።

*ማስታወሻ፡- ይህን ኮርስ የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች የዓለም ጂኦግራፊ የትምህርት ምዘና ስታንዳርዶችን ይወስዳሉ። ይህ ኮርስ ክፍተኛ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት አለው፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶችም ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል። እባክዎ ለተጨማሪ መረጃ ገጽ 56ን ይመልከቱ።*

---

**የ8ኛ ክፍል በምርጫ የሚወሰዱና መሰረታዊ ያልሆኑ ኮርሶች**

በስድስተኛና ሰባተኛ ክፍል ላይ የተለያዩ የአሰሳ በምርጫ የሚወሰዱ ኮርሶች ያለፉት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተለየ ፍላጎት የሚያሳድሩባቸውን የትምህርት ዓይነቶች ለማጥናት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በምርጫ የሚወሰዱ ጊዜያት ይኖራቸዋል። የኮርሶቹ ጥምረት ከእያንዳንዱ ት/ቤት የጊዜ መርሃ ግብር አንጻር ይለያያል። በምርጫ የሚሰጡ ኮርሶች በድሕረ ት/ቤት አክት II ፕሮግራም በኩል የሚቀርቡ ከሆነ ተማሪዎች በእነዚህ ኮርሶች ላይም ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ። (ገጽ 6ን ተመልከት)።

**የስነ ጥበብ ትምህርት**

**ጊታር፣ ሙሉ ዓመት (19246)**

*ተማሪዎች፡-*

- የሙዚቃ መሳሪያ ትክክለኛ አጠቃቀምና አያያዝን በተግባር ያሳያሉ።
- ገላጭ የሆነ ድምፅ ለማውጣት ትክክለኛውን የአጨዋወት ቴክኒክ በተግባር ያሳያሉ።
- መቃኛ በመጠቀም የሙዚቃ መሳሪያውን ድምፅ የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ።

- የጊታር መሰረታዊያን ትውውቅና ስታንዳርድ የሙዚቃ ኖታዎችን አነባበብ በተመለከተ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
- ተቀዳሚ የህብረ ድምፅ መዋቅሮችንና ሃርመኒ ይጫወታሉ፡፡
- መሰረታዊ የቀኝ እጅ ቴክኒኮችና ሜሎዲክ አቀራረብ ዘይቤዎችን ይጫወታሉ፡፡
- በአነስተኛ ቡድኖች ለመጫወት ወይም ጊታርን በጋራ ለመጫወት አጽንኦት በመስጠት በዝግጅቶችና አቀራረቦች አማካይነት መማርን በተግባር ያሳያሉ፡፡

ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍት መግዛትና አኩስቲክ (ፎልክ ወይም ክላሲካል) ጊታር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ውስን ቁጥር ያላቸው የት/ቤቱ ንብረት የሆኑ የሙዚቃ መሳሪያዎችን መከራየት ይቻላል፡፡

**በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃ**

ከእያንዳንዱ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ዓላማዎች መካከል ከታች የተዘረዘሩት ይገኙበታል፡፡ በእያንዳንዱ ት/ቤት ለእነዚህ የሙዚቃ ቡድኖች የየራሳቸው ስሞች ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

በ ***መካከለኛ ደረጃ ባንድ፣*** ሙሉ ዓመት **(19201)** ተማሪዎች፡

- ለጀማሪ ባንድ (የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ወይም የ6ኛ ክፍል ጀማሪ ባንድ) የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ክህሎት ይኖራቸዋል፡፡
- የሙዚቃ ኖታዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ፣ በዚህም ውስጥ አርቲኩሌሽንስ፣ ኮምፓውንድ ሜትርስ፣ ንኡስ ክፍሎችና የቁልፍ አመልካቾችና በርካታ ድንገተኛዎች ይገኙበታል፡፡
- የአንድ ከግማሽ አክታቭ ወይም የተሟሉ መሰረታዊ ነጥቦችን (የምት መሳሪያዎች) ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል፡፡
- የሙዚቃ መሳሪያውን ቅኝት በጆሮ ሰምተው የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ፡፡
- ርዝመታቸው ከ2-4 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ፡፡
- የቴምፖ፣ የአርቲኩሌሽን እና የዘይቤ ለውጦችን በተመለከተ ከባንዱ መሪ ለሚያዩት የሰውነት እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ የአንደኛና ክፍል ስነ-ጽሑፍን በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ፡፡
- ከኮንሰርት ስነ-ጽሑፍ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ፡፡

በ ***ከፍተኛ ባንድ፣*** ሙሉ ዓመት **(19228)** ተማሪዎች፡-

- ለመካከለኛ ደረጃ ባንድ የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ክህሎት ይኖራቸዋል፡፡
- ለቃላት አወጣጥ ትኩረት በመስጠት የሙዚቃ ማስታወሻዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- የሁለት አክታቭና የተሟሉ መሰረታዊ ነጥቦችን (የምት መሳሪያዎች) ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን ክህሎቶች ለመዋሃድና ለማመጣጠን ከሚሰጥ ስሱነት ጋር የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል፡፡
- የቁልፍ አመላካቾችን በመለየት ተጓዳኝ ስኬሉን በተመረጡ ሜጀር ወይም ማይነር ቁልፎች መጫወት ይችላሉ፡፡
- ከአንድ በላይ ማሌትስ፣ ብዙ የምላስ አጠቃቀም፣ እና አማራጭ የጣት አቀማመጥን የሚያካትቱ ይበልጥ የተራቀቁ የአጨዋወት ቴክኒኮችን ያዳብራሉ፡፡
- ርዝመታቸው ከ4-8 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ፡፡
- በተለያዩ ዓይነቶች ዘይቤዎች በሚደረጉ ዝግጅቶችና ፕረዘንቴሽኖች አማካይነት የተማሩትን በተግባር ያሳያሉ፡፡
- ከኮንሰርት ሙዚቃና ዝማሬ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ፡፡

በ ***ጀማሪ ኦርኬስትራ፣*** ሙሉ ዓመት **(19237)** ተማሪዎች፡

- የሙዚቃ መሳሪያ ትክክለኛ አጠቃቀምና አያያዝንና አመታትን በተግባር ያሳያሉ፡፡
- ፒዚካቶና መሰረታዊ የአመታት ቴክኒኮችን ጨምሮ ገላጭ የሆነ ድምፅ ለማውጣት ትክክለኛውን የአጨዋወት ቴክኒክ በተግባር ያሳያሉ፡፡
- ሙዚቃ ማንበብና ተጓዳኝ ሙዚቃዊ አተረጓጎም ለትክክለኛ ፒች፣ ቅኝት፣ የጊዜ አመልካች፣ የቁልፍ አመልካች፣ ቴምፖ እና ገላጭ ምልክቶችን ለማግኘት መሰረታዊነታቸውን ይገነዘባሉ፡፡
- አንድ አክታቭ (የመጀመሪያ አቀማመጥ) እና ጥንድ ማቆሚያዎችን በአንድ አውታር ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን ክህሎቶች የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል፡፡
- መቃኛ በመጠቀም የሙዚቃ መሳሪያውን ድምፅ የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ፡፡
- ርዝመታቸው ከ1 እስከ 2 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ፡፡
- ሜትሮኖም በመጠቀምና የባንድ መሪውን የሰውነት እንቅስቃሴ በመከተል ቀጥ ካለ ምት ጋር ይጫወታሉ፡፡
- በተለያዩ ዓይነቶች ዘይቤዎች በሚደረጉ ዝግጅቶችና ፕረዘንቴሽኖች አማካይነት የተማሩትን በተግባር ያሳያሉ፡፡

በ ***መካከለኛ ደረጃ ኦርኬስትራ፣*** ሙሉ ዓመት **(19242)** ተማሪዎች፡

- ለ8ኛ ክፍል ጀማሪ ኦርኬስትራ የተቀመጡ እና/ወይም ለመካከለኛ ደረጃ ኦርኬስትራ የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ክህሎት ይኖራቸዋል፡፡
- የሙዚቃ ኖታዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ፣ በዚህም ውስጥ አርቲኩሌሽንስ፣ ኮምፓውንድ ሜትርስ፣ ንኡስ ክፍሎችና የቁልፍ አመልካቾችና ሁለት ከፍታዎች ይገኙበታል፡፡
- ማራዘሚያዎችን በመጠቀምና የመምቻውን ክብደት፣ ፍጥነትና ንክኪ በመቆጣጠር በአንድ ተኩል አክታቭ ሬንጅ የመጫወት ክህሎትን ያዳብራሉ፤ እነዚህን ክህሎቶች የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል፡፡
- የሙዚቃ መሳሪያውን ቅኝት በጆሮ ሰምተው የመቃኘት ችሎታን ያዳብራሉ፡፡
- ርዝመታቸው ከ2-4 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ፡፡
- የቴምፖ፣ የአርቲኩሌሽን እና የዘይቤ ለውጦችን በተመለከተ ከባንዱ መሪ ለሚያዩት የሰውነት እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ፡፡
- ከኮንሰርት ስነ-ጽሑፍ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ፡፡

በ ***በከፍተኛ ኦርኬስትራ፣*** ሙሉ ዓመት **(19243)** ተማሪዎች፡

- ለ8ኛ ክፍል መካከለኛ ደረጃ ኦርኬስትራ የተቀመጡ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል ክህሎት ይኖራቸዋል፡፡
- ለቃላት አወጣጥ ትኩረት በመስጠት የሙዚቃ ማስታወሻዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- የሁለት አክታቭ ለመጫወት ክህሎትን በማዳበር እነዚህን ክህሎቶች ለመዋሃድና ለማመጣጠን ከሚሰጥ ስሱነት ጋር የሙዚቃ ቡድኑ አባል ሆነው ይጠቀሙባቸዋል፡፡
- የቁልፍ አመላካቾችን በመለየት ተጓዳኝ ስኬሉን በተመረጡ ሜጀር ወይም ማይነር ቁልፎች መጫወት ይችላሉ፡፡
- እንደ ቫይብራቶ፣ የጎንዮሽ አመታትና ስፒካቶ የመሳሰሉ ይበልጥ ረቀቅ ያሉ የአጨዋወት ቴክኒኮችን ያዳብራሉ፡፡
- ርዝመታቸው ከ4-8 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ፡፡
- በተለያዩ ዓይነቶች ዘይቤዎች በሚደረጉ ዝግጅቶችና ፕረዘንቴሽኖች አማካይነት የተማሩትን በተግባር ያሳያሉ፡፡
- ከኮንሰርት ሙዚቃና ዝማሬ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ፡፡

**የጃዝ ባንድ፣ *ሙሉ ዓመት* (19239)**
የጃዝ ሁኔታዊ ማሻሻያዎችን ለምሳሌ ብሉዝ፣ ፔንታቶኒክ እና ቤቦፕ ስኬሎችን፣ የህብረ ድምጽ ምልክቶችን፣ የህብረ ድምጽ ለውጦችን መሰረታዊ ጉዳይና ከእነዚህ የሙዚቃ አላባውያን ተነስቶ የአንድ ሰው ዝግጅት የማድረግ ጽንሰ ሃሳቦችን ይማራሉ። በትልቅ ባንድ እና/ወይም በአነስተኛ የጥምር ስብስብ ላይ ዝግጅት ያቀርባሉ።

**የቴአትር ጥበባት - ድራማ**
***ሙሉ ዓመት* (11394)**
**ሴሚስተር (11393)**
*ተማሪዎች፡-*
- ስክሪፕት ያለውና የሌለው ማቴሪያል ለመፍጠር በድንገት የፈጠራ ስራን ይጠቀማሉ።
- የዲዛይን አላባውያን ተጠቅመው ሙድ ይፈጥራሉ።
- የቴአትር ታሪክን አላባውያን ይዳስሳሉ።
- የፕሮዳክሽንን ድራማዊ አላባውያን በተመለከተ የአተረጓጎም የጋራ መግባባትን መተንተንና ማሳካት ይችላሉ።
- የቴክኒካዊ ቴአትር አካላትን ተጠቅመው የገጸ ባህርያት ግንባታን ያዳብራሉ።
- ግላዊ ችሎታዎችንና ፈጠራዊ ጥረቶችን ለማድነቅ ምክንያታዊነትን ያዳብራሉ።

**ቪዥዋል አርትስ I**
***ሙሉ ዓመት* (19040)**
**ሴሚስተር (19041)**
*ተማሪዎች፡-*
- የዲዛይን መርሆዎችና የጥበብን አላባውያን በመተግበር የጥበብ ስራዎችን ይፈጥራሉ።
- የተለያዩ ቴክኒኮችንና ሒደቶችን በማቀናጀት ባለ ሶስት አቅጣጫ ስራዎችን ይፈጥራሉ።
- የተለያዩ የጥበብ ስራዎች ላይ ግላዊ ትርጓሜዎችንና የሕሊና ፍርድን ይሰጣሉ።
- የጥበብን ቃላት በመጠቀም ያለቁ የጥበብ ስራዎችን መተንተንና መተቸት ይችላሉ።
- በጥበብ አዘገጃጀት ላይ ስነ-ምግባራዊ ውሳኔዎችን ማስረዳትና መተግበር ይችላሉ።

**ቪዥዋል አርትስ II**
***ሙሉ ዓመት* (19117)**
**ሴሚስተር (19115)**
*ተማሪዎች፡-*
- የዲዛይን መርሆዎችና የጥበብን አላባውያን ወደ ፖርትፎሊዮ ይተገብራሉ።
- ሼዲንግና የተለያዩ የአተያይ ቅርጾችን በምስል ፕሌን በመጠቀም ጥልቀትን ያስተላልፋሉ።
- የዲዛይን መርሆዎችን በማጣመር ግላዊ የጥበብ ስራዎችን መፍጠርና የእደ ጥበብን ጥራት ማሻሻል ይችላሉ።
- የአርትን አላባውያን እና የዲዛይን መርሆዎችን በመጠቀም ሙድና አገላለጽን ለመፍጠር ይችላሉ።
- በጥበብ ዝግጅት ላይ በስነ-ምግባራዊ ውሳኔዎች ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ።
- የጥበብን ቃላት በመጠቀም ያለቁ የጥበብ ስራዎችን መተንተንና መተቸት ይችላሉ።

***የድምፅ ሙዚቃ***
ከእያንዳንዱ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ዓላማዎች መካከል ከታች የተዘረዘሩት ይገኙበታል። በእያንዳንዱ ት/ቤት ለእነዚህ የሙዚቃ ቡድኖች የየራሳቸው ስሞች ሊሰጣቸው ይችላል።

በ ***ጀማሪ የሙዚቀኞች ስብስብ፣*** ሙሉ ዓመት **(19261)** ሴሚስተር **(19264)** *ተማሪዎች:*
- ጥሩ የድምፅ ቃና ለማውጣት የሚያስፈልግ ትክክለኛ የሰውነት አቋም፣ የትንፋሽ ቁጥጥር እና የአፍ ቅርጽን በተግባር ያሳያሉ።
- ሙዚቃ ማንበብና ተጓዳኝ ሙዚቃዊ አተረጓጎም ለትክክለኛ ፒች፣ ቅኝት፣ የጊዜ አመልካች፣ የቁልፍ አመልካች፣ ቴምፖ እና ገላጭ ምልክቶችን ለማግኘት መሰረታዊነታቸውን ይገነዘባሉ።
- ዲያቶኒክ ፒች ሲስተምን በመጠቀምና በስብስቡ ውስጥ የተወሰነ ክፍልን በመያዝ በትክክል ፒችን የማዛመድ ችሎታን ያዳብራሉ።
- ርዝመታቸው ከ1 እስከ 2 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- የባንድ መሪው ለሚያሳየው የአካል እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።
- ለአንደኛ ወይም ሁለተኛ ክፍል አግባብነት ባላቸው ዝግጅቶችና አቀራረቦች አማካይነት መማርን በተግባር ያሳያሉ።

በ ***መካከለኛ ደረጃ ኦርኬስትራ፣*** ሙሉ ዓመት **(19274)** ሴሚስተር **(19275)**
*ተማሪዎች:-*
- በ *ጀማሪ የሙዚቀኞች ስብስብ* ውስጥ የዳበሩ ክህሎቶችን ማሳደጋቸውን ይቀጥላሉ።
- በትሬብል ክሌፍ ውስጥ ያሉ የሙዚቃ ኖታዎችን ተገንዝበው ምላሽ ይሰጣሉ።
- በጉርምስና ዕድሜ ምክንያት ስለሚከሰት የድምፅ ለውጥና በእነዚህም ምክንያት በሬንጅ እና በድምፅ ቃና ከለር ላይ የሚፈጠሩ ለውጦችን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ይማራሉ።
- ባለ ሁለት እና ሶስት ክፍል ሃርመኒ እና ካፔላ ውስጥ ሲመዘገቡ ራሳቸውን ችለው የመቆም ችሎታን ያዳብራሉ።
- ጆሮ እና ድምፅ ከፒች ጋር እንዲጣጣምና በህብረ ድምጽ ውስጥ እንዲቆይ ለማድረግ ቅኝታቸውን ማዳበር።
- ርዝመታቸው ከ2-4 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- ለፌርማታ፣ አክስሌራንዶ እና ሪታርዳንዶ የባንድ መሪ ለሚያሳየው የሰውነት እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።
- የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ የሁለተኛና ሶስተኛ ክፍል ስነ-ጽሑፍን በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- በደረጃ I ሳይት ንባብ።

በ ***ከፍተኛ ኦርኬስትራ፣*** ሙሉ ዓመት **(19285)** *ተማሪዎች:*
- በትሬብልና ባስ ክሌፍ ውስጥ የሙዚቃ ኖታን በመረዳት ምላሽ ይሰጣሉ።
- ሰፊ በሆነ ሬንጅ ውስጥ የመዝፈን ክህሎትን በላቀ የነጻነት መንፈስ ማሳደግና እነዚህን ክህሎቶች የሙዚቃ ባንድ አካል ሆኖ በተግባር ማሳየት።
- ባለ ሶስትና አራት ክፍል ስነ-ጽሑፍ ላይ በካፔላ ዘፈን የተጣራ የፒች ማዛመድ ማስተካከያዎችን ለማድረግ የሚያስችል ችሎታን ያዳብራሉ።
- ርዝመታቸው ከ4-8 የሚደርሱ ቅኝታዊ ወይም ሜሎዲክ ማሻሻያዎችን ይፈጥራሉ።
- የቴምፖ፣ የአርቲኩሌሽን እና የዘይቤ ለውጦችን በተመለከተ ከባንዱ መሪ ለሚያዩት የሰውነት እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጣሉ።
- የአንድ ሰው ዝግጅትን ጨምሮ እንዳግባብነቱ የ3ኛና 4ኛ ክፍል ስነ-ጽሑፍን በመተግበርና በማቅረብ መማራቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- ከኮንሰርት ስነ-ጽሑፍ ሁለት ደረጃ ዝቅ ብሎ ሳይት ማንበብ ይችላሉ።

**ቢዝነስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ**
**የኮምፒዩተር መተግበሪያዎችና የኢንተርኔት ቴክኖሎጂዎች**
***ሙሉ ዓመት* (13107)**
**ሴሚስተር (13106)**
ይህ ኮርስ የተቀረጸው ውጤት መር አቀራረቦችን በመጠቀም እውነተኛ የተጨባጭ ሕይወት ክህሎቶችን ለማዳበር ነው። ተማሪዎች ስለ ዲጂታል

ዜግነት፣ መሰረታዊ የኮምፒዩተር አጠቃቀሞች፣ የኪቦርድ አጠቃቀም፣ የሶፍትዌር መተግበሪያዎች (ወርድ ፕሮሰሲንግ፣ ስፕሬድሺት፣ መልቲሚድያ መተግበሪያዎች፣ ዳታቤዞች) እና የስራ ዘመን አሰሳን በተመለከተ ይማራሉ። ይህ ኮርስ በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ሊተገበሩ የሚችሉ ክህሎቶችን የሚያጎለብት ሲሆን፣ በት/ቤት፣ በቢዝነስና በግል ሕይወት ውስጥ ጥቅም ላይ ከሚውሉ የ 21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መሰናዶዎች ያቀርባል።

*ተማሪዎች:-*

- የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን አገልግሎት በመለየትና በተግባር በማሳየት መረጃን ለመከወን እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ያስረዳሉ።
- ኮምፒዩተሮች ከሌሎች የኮምፒዩተር ሲስተሞችና መሳሪያዎች ጋር እንዴት ግንኙነት እንደሚፈጥሩ፤ ሶፍትዌርና ሐርድዌር በጋራ ሆነው እንዴት ኤሌክትሮኒክ ስራዎችን እንደሚሰሩ፤ እና ሶፍትዌር እንዴት እንደሚዘጋጅና ደረጃው ከፍ እንደሚል ያስረዳሉ።
- የኮምፒዩተር ኦፕሬቲንግ ሲስተም ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳየት የፋይልና የዲስክ ማኔጅመንትን ጨምሮ የዊንዶውስ ዴስክቶፕ አጠቃቀምና ቁጥጥርን በተግባር ያሳያሉ።
- የሲስተም ቅንብሮችን እንዴት መቀየርና መተግበሪያዎችንም እንዴት መጫንና ማራገፍ እንደሚቻል ያውቃሉ።
- ሰነዶችን ለመጻፍ፣ ለማስተካከል፣ ለመከለስና ለማረም የኪቦርድ አጠቃቀም ክህሎቶችንን ይተገብራሉ።
- አግባብነት ያላቸውን መተግበሪያዎች በመጠቀም ዳታቤዝ፣ ስፕሬድሺት እና ስላይድ ሾው ዲዛይን ማድረግና ማዘጋጀት ይችላሉ።
- የኢሜይል እና የኢሜይል ፕሮቶኮል ትክክለኛ አጠቃቀምን ይለያሉ።
- የተለያዩ የኢንተርኔት መፈለጊያ ኢንጂኖችና ፖርታሎችን አጠቃቀም በተግባር ያሳያሉ።
- እንደ ኮምፒዩተር ሳይንስ ባሉ የተለያዩ የስራ ዓይነቶች ውስጥ የቴክኖሎጂን አጠቃቀም ይዳስሳሉ።
- የኮምፒዩተር መተግበሪያዎች፣ የኢንተርኔት ቴክኖሎጂዎችና የኮምፒዩተር ቴክኖሎጂዎች (አማራጭ) ሃገር አቀፍ የኢንዱስትሪ ብቃት ማረጋገጫ ለሆነው ለኢንተርኔት ኮር ኮምፒዩተር ማረጋገጫ (IC3) ይዘጋጃሉ።

**ዲጂታል የግቤት ቴክኖሎጂዎች**
**ሙሉ ዓመት (16607)**
**ሴሚስተር (16617)**

ይህ ኮርስ አዳዲስና በቅርብ የመጡ የግቤት መሳሪያዎችን (ለምሳሌ:- የንግግርና የእጅ ጽሑፍን ማወቂያ ሶፍትዌሮች፣ ታብሌቶች፣ ክላውድ ኮምፒዩተር መተግበሪያዎች፣ የጆሮ ማዳመጫዎች/ማይክሮፎን፣ ስካነር፣ ዲጂታል ካሜራ፣ ዲጂታል የቪድዮ ካሜራዎች፣ የሞባይል መሳሪያዎች፣ የኮምፒዩተር ሲስተሞች) በማስተዋወቅ ተማሪዎች በስራ ቦታና በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ እየተለመዱ የመጡ መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ ያዘጋጃቸዋል።

*ተማሪዎች:-*

- በመንካት የመጻፍ ቴክኒኮችን በመማር የኪቦርድ አጻጻፍ ፍጥነታቸውንና ትክክለኛነታቸውን ያሻሽላሉ።
- የዴስክቶፕ ፐብሊሺንግ አቅሞችን ጨምሮ የወርድ ፕሮሰሲንግ ሶፍትዌርን ሁሉንም አቅሞችና መለያ ባህርያት ተምረው ተግባራዊ ያደርጋሉ።
- አዲስ መልእክት የመጻፍና የማረም እንደዚሁም ወርድ ፕሮሰሲንግን ተጠቅመው ለአካዳሚክ ክፍሎች ሰነዶችን የማዘጋጀት ክህሎታቸውን ያሻሽላሉ።
- የቢዝነስና የግል ደብዳቤዎች፣ ኤንቨሎፕስ፣ ስፕሬድሽት፣ ቻርቶች፣ ሪፖርቶች፣ የሴሚስተር ወረቀቶችና የቢሮ ውስጥ መጻጻፈያዎችን ጨምሮ የተለያዩ ሰነዶችን ቅርጸት ማስተካከልን ይለማመዳሉ።

- የተለያዩ ዓይነት የስራ ዘመን አማራጮችን በማፈላለግ ስራ ለመቀጠር ስለሚያስፈልጉ ክህሎቶች ማለትም የግል ታሪክ መረጃ አዘገጃጀትና የቃለ መጠይቅ አደራረግ ክህሎቶችን በተመለከተ ግንዛቤ ይኖራቸዋል።
- በአሜሪካ የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ ስለ ቢዝነስ ባለቤትነትና የቢዝነስ ተግባራት መረጃን ያስሳሉ።
- የግል በጀት መያዝ፣ የተንቀሳቃሽ ሒሳብን ማመዛዘን፣ የክፍያ ቼክን ምንነት መፍታት፣ ኢንሹራንስና መኪናን መግዛት፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ቤት መምረጥ፣ ኢንቨስት ማድረግና ሌሎች ከሸማቾች ጋር የተያያዙ ክህሎቶች ላይ ፕሮጄክቶችን ያጠናቅቃሉ።
- ለአዳዲስና በቅርብ ለተጀመሩ ቴክኖሎጂዎች (የስክሪን ላይ አጻጻፍ፣ ንግግርን ማወቂያ፣ iPads እና የሞባይል ቴክኖሎጂዎች) የስራ ቦታ መተግበሪያዎች ላይ ውይይት ያደርጋሉ።

**ኮምፒዩተር ሳይንስን መመርመር (16640)**
**ሙሉ ዓመት፣ አንድ ክሬዲት**

ኮምፒዩተር ሳይንስን የመመርመር (ኮድ መስጠት) ኮርስ የተማሪዎችን ኮድ የመስጠት፣ ስሌት የመስራት፣ የፋይናንስ፣ እና ዲጂታል ግንዛቤና ክህሎቶች የሚያሳድግ ሲሆን፣ የኮምፒዩተር ፕሮግራሞችን ዲዛይን በማድረግና በመጻፍ የቢዝነስና የተጨባጩ ዓለም ችግሮችን ለመፍታት የኮምፒዩተር ሳይንስ ጽንሰ ሃሳቦችን እንዲማሩ ያስችላል። ስርዓተ ትምህርቱ እንደ Python Alice with Java፣ Java፣ Scratch፣ HTML፣ Java Scripting፣ የሞባይል መተግበሪያዎችን በመጠቀም ለኮምፒዩተር ኮድ መስጠትንና የድረ ገጽ ዝግጅትን ያካትታል። የተቀናጁት ፕሮጄክቶች "ተጨባጭ ዓለም" የሒሳብና የፋይናንስ ዕውቀት ትግበራ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።

*ማስታወሻ:- ይህ ኮርስ ከፍተኛ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት አለው፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶችም ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል። እባክዎ ለተጨማሪ መረጃ ገጽ 56ን ይመልከቱ።*

**እንግሊዝኛ**
**የ8ኛ ክፍል የንባብ ስትራቴጂስ፣ ሙሉ ዓመት (11121)**
*የመምህር እና/ወይም የአማካሪ ምክረ ሃሳቦች*

የንባብ ስትራቴጂስ 8 ስፔሻላይዝድ የሆነ በምርጫ የሚወሰድ የእንግሊዝኛ ኮርስ ሲሆን ተማሪዎች መሰረታዊ የእውቀት ማዳበሪያ ክህሎቶችን ለመለማመድ ታላሚ የግንዛቤ መፍጠሪያ መመሪያና ተጨማሪ ጊዜ ይሰጣቸዋል። መምህራን ግልጽ መመሪያ የሚሰጡት ወሳኝ በሆኑ የንባብ ክፍሎች ላይ በማተኮር ነው:- ፎኒክስ፣ ፎነሚክ እውቀት፣ አንደበተ ርቱዕነት፣ የቃላት ግንባታና አንብቦ መረዳት። ከእነዚህ ወሳኝ የኮርስ ክፍሎች በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ ተማሪ የንባብ ስኬት ግቦችን ከማሳካት አንጻር ያሳየውን እመርታ ለመለካት በተወሰነ ወቅት ምዘናዎች ይካሄዳሉ። ተማሪዎች በተናጠልና በአነስተኛ ቡድን ውስጥ ሆነው በመስራት:-

- ንቁ የሆኑ የንባብ ስትራቴጂዎችን መማርና መለማመድ ይችላሉ
- ስርዓት ባላቸው የትምህርት ልማዶች (ግልጽና ስልታዊ የማመስጠር/ኮድ የመፍታት ስራ) ውስጥ ይሳተፋሉ
- የንባብና የአጻጻፍ ጽናትና ርቱዕነት ያዳብራሉ
- የቃላትን ብዛት ይጨምራሉ
- አንብቦ መረዳትን ያሻሽላሉ
- የንባብ ልምዳቸውን ያሰፋሉ።

**ጋዜጠኝነት፣ ሙሉ ዓመት (11201)**

ይህ በምርጫ የሚወሰድ ኮርስ ተማሪዎች የጋዜጣ ወይም የኦዲዮ/ቪድዮ ዜና ስርጭት እንዲያዘጋጁ ይጠይቃል። ተማሪዎች በስራቸው አማካይነት ስለ ጋዜጣና ብሮድካስቲንግ አጻጻፍና አዘገጃጀት ይማራሉ።

*ተማሪዎች፡-*
- የጋዜጠኝነት ዘዴዎችን ተምረው ጥቅም ላይ ያውላሉ።
- የሕትመት እና/ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስቶችን ይዘትና ቴክኒካዊ ጥራት ይተነትናሉ።
- ኤዲቶሪያሎች፣ ፊቸሮችና ስፖርት ጨምሮ የዜና ጽሑፎችን ይጽፋሉ እና/ወይም የንግድ ማስታወቂያዎች፣ የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያዎችን ወይም የዜና ሾው፣ የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያዎችና የንግድ ማስታወቂያዎችን ጨምሮ አጫጭር የብሮድካስት መልእክቶችን ይጽፋሉ።
- የተለያዩ የጋዜጠኝነት ስራ ተግባራትን ለምሳሌ አርትኦት፣ የምስል ንድፍና ኮፒ፣ አርእስት፣ የስክሪፕት ዝግጅት አጻጻፍና የመጨረሻ ፕሮዳክሽን ይለማመዳሉ።

**ዓመታዊ መጽሔት፣ ሙሉ ዓመት (11209)**

በዚህ ኮርስ፣ ተማሪዎች የት/ቤቱን ዓመታዊ መጽሔት ያዘጋጃሉ። ተማሪዎች በስራቸው አማካይነት ስለ ሕትመት አጻጻፍና አዘገጃጀት ይማራሉ።

*ተማሪዎች፡-*
- የተለያዩ የጋዜጠኝነት ስራ ተግባራትን ለምሳሌ አርትኦት፣ የምስል ንድፍና ኮፒ፣ አርእስት፣ የስክሪፕት ዝግጅት አጻጻፍና የመጨረሻ ፕሮዳክሽንና ስርጭትን ይለማመዳሉ።
- የጋዜጠኝነት ዘዴዎችን ተምረው ጥቅም ላይ ያውላሉ።
- ለሕትመት ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ ጽሑፎችን ይጽፋሉ።
- ጽሑፎችን ማረምና ማስተካከል ይችላሉ።

**የቤተሰብና የሸማች ሳይንሶች**
**የሕይወት ስራ አመራር ክህሎቶች**
**ሙሉ ዓመት (18245)**
**ሴሚስተር (18244)**

ይህ ኮርስ የቤተሰብ ሚና መጫወትና ልጆችን መንከባከብ፣ የአጭርና የረዥም ጊዜ ግቦችን መገምገምና ስራንና ቤተሰብን የሚያጣጥሙ የተለያዩ ቴክኒኮች የመሳሰሉ ምስለ የሕይወት ተሞክሮዎችን በመጠቀም ላቅ ያለ የአስተሳሰብ ክህሎቶችን ያስተምራል። ተማሪዎች በራስ በሚመራ መልቲሚድያ ላብራቶሪ ውስጥ የተለያዩ ሞጁሎችን ያጠናቅቃሉ።

*ተማሪዎች፡-*
- ጥሩ የሆነ የጊዜና የገንዘብ አያያዝን ይተገብራሉ።
- የሸማቾች ምርጫዎች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን ይተነትናሉ።
- ከጓደኞችና የቤተሰብ አባላት ጋር አዎንታዊ በሆነ መንገድ ግንኙነት ይፈጥራሉ።
- ዘመን አመጣሽ ማሽኖችን በመጠቀም መሰረታዊ የልብስ አዘገጃጀትና እንክብካቤ አደራረግን ይማራሉ።
- የተመጣጠኑ ምግቦችን በማዘጋጀት የጥሩ ምግብን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ።
- ብሔር ተኮር ምግቦችና ባህሎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ይተገብራሉ።
- የምግብን ደህንነት የሚያረጋግጥ ንጹህ የስራ አካባቢ እንዲኖር ያደርጋሉ።
- ግጭትን እንዴት ማስተናገድና ችግሮችን እንዴት መፍታት እንዳለባቸው ይማራሉ።
- ታዳጊ ልጆችን ለመንከባከብ የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ይተገብራሉ።
- ከሌሎች ጋር የሚደረግ የእርስ በርስ ግንኙነቶችን ይዳስሳሉ።
- የምግብ አዘገጃጀት መመሪያን በመረዳትና በአግባቡ በመጠቀም ስኬታማ የምግብ ውጤትን ያዘጋጃሉ።
- የስራ ዘመን አማራጮችና ተያያዥ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ ምርጫዎችን ይዳስሳሉ።

**ግለሰባዊ ዕድገት (18210)**
**ሙሉ ዓመት፣ አንድ ክሬዲት**

ይህ ኮርስ አዎንታዊ በራስ መተማመንን በማጎልበት፤ ከቤተሰብ፣ ከእኩዮች እና ከማህበረሰብ አባላት ጋር ጤናማ ግንኙነቶችን ለመገንባት ክህሎቶችን በማዳበር፤ ጭንቀትን እና ግጭትን በመቆጣጠር፤ ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁ ለመሆን በመዘጋጀት ላይ ያተኩራል። ይዘቱ የሚያተኩረው በራስ መተማመን፣ እሴቶች፣ በውሳኔ አሰጣጥ እና ግብ የማስቀመጥ ችሎታዎች፣ በግለሰቦች እና በቤተሰብ ግንኙነቶች እና በሙያ እቅድ ላይ ነው።

*ተማሪዎች፡-*
- እሴቶች ለአደጋ በሚያጋልጡ ባህሪዎች ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ይለዩና ይተነትናሉ።
- የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎችን እና የተሳሳተ አመለካከቶችን ተጽዕኖ ያስሳሉ።
- ስለ ምርጫዎች እና ተግዳሮቶች ግንዛቤን ያዳብራሉ።
- አዎንታዊ የግንኙነት እና የግጭት አፈታት ክህሎቶችን በመለማመድ ተገቢ የግንኙነት ባህሪያትን ይማራሉ።
- በኮምፒዩተር የተሠራ አሻንጉሊት በመጠቀም በማስመሰል በሚደረግ የወላጅነት እንቅስቃሴ ውስጥ ይሳተፋሉ።
- የሥራ ፍለጋ ስልቶችን፣ የሥራ መስፈርቶችን እና የሥራ-ጣቢያ ጉብኝቶችን በመጠቀም ሙያዎችን ያስሳሉ።

**ሒሳብ**
**አልጀብራ ስትራቴጂስ፣ ሙሉ ዓመት (13125)**

የአልጀብራ ስትራቴጂስ ኮርስ በምርጫ የሚወሰድ ኮርስ ሆኖ በአልጀብራ I ውጤታማ ለመሆን የሚፈልጉ ተማሪዎች ይወስዱታል። ለኮርሱ የተመዘገቡ ተማሪዎች የመነሻ እውቀት ይገነባሉ፣ ለይዘቱ ይበልጥ ጽንሰ ሃሳባዊ አቀራረቦችን ይተገብራሉ፣ የመሰረታዊ ኮርሱን ይዘት ይበልጥ በጥልቀት ያዳብራሉ።

**የሒሳብ ስትራቴጂስ ለ8ኛ ክፍል**
**ሙሉ ዓመት (13118)**
**ሴሚስተር (13119)**

የስትራቴጂስ ኮርስ በክፍል ደረጃ ሒሳብ ላይ ስኬታማ ለመሆን ተጨማሪ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በአማራጭነት የሚሰጥ ኮርስ ነው። በስትራቴጂስ ኮርስ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የመነሻ እውቀትን ያዳብራሉ፣ ስለይዘቱ ተጨማሪ ጽንሰ ሃሳባዊ አቀራረቦችን ይለማመዳሉ፣ መሰረታዊ የኮርሱን ይዘት ይበልጥ በጥልቀት ያጎለብታሉ።

**የልዩ ፍላጎት ትምህርት**
**ትምህርታዊ ጥናቶች፣ ሙሉ ዓመት (10028)**

*በቅድሚያ የሚወሰድ፡- ተማሪው የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት መሆኑ መለየት አለበት*

በተማሪው ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) መሰረት የኮርስ ስራ ግለሰባዊ የሚደረግ ሲሆን፣ የእያንዳንዱን ተማሪ አጠቃላይ የትምህርት ኮርሶችን ፍላጎትንም ያጠናክራል። በተጨማሪም፣ የማዳመጥ ክህሎቶች፣ የመጻፍ ክህሎቶች፣ የአደረጃጀትና አጠቃላይ የጥናት ክህሎቶች አጽንኦት ይሰጣቸዋል።

**ማህበራዊ ክህሎቶች፣ ሙሉ ዓመት (10023)**

*በቅድሚያ የሚወሰድ፡- ተማሪው የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት መሆኑ መለየት አለበት*

የማሕበራዊ ክህሎቶች ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ደረጃ ተማሪው ከሌሎች ሰዎች ጋር ተገቢነት ያላቸውን ማሕበራዊ ተግባቦቶች ለማድረግ የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን የመቅሰምና የመተግበር ዕድልን ይሰጠዋል። በትምህርትነት ከሚሰጡ ክህሎቶች መካከል ከሌሎች ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ አተያይን ማዳበር፣ የራስን ዕድል በራስ መወሰን፣ ከቡድኖች ጋር መስራት፣ ጫና እና ስልቹነትን የመቋቋሚያ ስትራቴጂዎች እና ለማሕበራዊ ጠባይ "ያልተጻፉ ደንቦችን" መገንዘብ ይገኙበታል። ድርጅታዊና ለራስ የመሟገት ክህሎቶችን ማዛመድም ይሸፈናሉ።

**የተማሪ ድጋፍ**
**ኮር ፕላስ (Core Plus)**
***ሙሉ ዓመት* (11129)**
**ሴሚስተር (11128)**
*ይህ ኮርስ የተቀረጸው የአጠቃላይ ትምህርት ተማሪ ሆኖ ስለ አደረጃጀት፣ ማስታወሻ አያያዝ፣ ፈተና አወሳሰድና ተማሪዎች ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያግዟቸውን ሌሎች ቴክኒኮች በተመለከተ ተጨማሪ ለማወቅ ለሚፈልግ ተማሪ ነው።*
*ተማሪዎች:-*
- *የራሳቸውን የጥናት ጊዜ መርሃ ግብር ያቅዳሉ።*
- *የማዳመጥ ክህሎቶችን ለማሻሻል የሚያስችሉ መንገዶችን ይማራሉ።*
- *በአሁኑ ጊዜ የት/ቤት ስራዎችን በተመለከተ ያሉ አመለካከቶችን ይገመግማሉ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በመለየትና ግቦችን በማስቀመጥ አዎንታዊ የሆኑትን ማጎልበት ይጀምራሉ።*
- *የተጻፈ ማቴሪያልን ለመገንዘብና ይዞ ለመቆየት የሚያስችል የጥናት ክህሎት ቀመርን ይጠቀማሉ።*

**የቴክኖሎጂ ትምህርት**
**የሮቦት ዲዛይን ቴክኖሎጂ (18421)**
***ሙሉ ዓመት፣ አንድ ክሬዲት***
*ተማሪዎች ስለ አውቶሜሽን ሲስተምስ፣ ማይክሮፕሮሰሰርስ እና በማኑፋክቸሪንግ፣ ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን ሲስተሞች ላይ ያላቸውን ትግበራ ያጠናሉ። ከሚካተቱት አርእስት መካከል የኮምፒዩተር መሳሪያና ኦፕሬቲንግ ሲስተምስ፣ ሮቦቲክስ፣ ፕሮግራሚንግ፣ የቁጥጥር ስርዓቶችና የእነዚህ ቴክኖሎጂዎች ማህበራዊ/ባህላዊ ተጽእኖ ይገኙበታል። ችግር ፈቺ ተግባራት ተማሪዎች የኮምፒዩተር ሲስተሞችን ዲዛይን እንዲያደርጉ፣ ፕሮግራም እንዲያደርጉና እንዲያስተሳስሩ ይፈትኗቸዋል። የመማር ተግባራት መካከል ሮቦቲክስ፣ በኮምፕዩተር የታገዘ ዲዛይን፣ በኮምፒዩተር የታገዘ የኤሌክትሮሜካኒካል መሳሪያዎች ማምረትና ዲዛይን፣ እና ቁጥጥር ይገኙበታል።*

*ማስታወሻ:- ይህ ኮርስ ከፍተኛ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት አለው፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶችም ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል። እባክዎ ለተጨማሪ መረጃ ገጽ 56 ን ይመልከቱ።*

**ቴክኖሎጂካል ሲስተምስ**
***ሙሉ ዓመት* (18462)**
**ሴሚስተር (18463)**
*ተማሪዎች ቴክኖሎጂካል ሲስተሞች እንዴት እንደሚሰሩ ይመረምራሉ፤ በተለያዩ ቴክኒካዊ መስኮች የተጨባጩነ ዓለም ሲስተሞች አካላተ ይለያሉ፤ እናም በክፍል ውስጥ ፕሮጀክቶች አማካይነት ሲስተሞችን ዲዛይን ያደርጋሉ፣ ይገነባሉ፣ እንደዚሁም ይገመግማሉ። ተማሪዎች ሲስተሞችን ዲዛይን በማድረግና በመገንባት እንደዚሁም ተጽእኗቸውን በመመዘን የቴክኖሎጂያዊ ዓለምን ችግሮችና አጋጣሚዎች እንዴት መቅረብ እንደሚቻል ጥልቀት ያለው ግንዛቤ ያዳብራሉ። ኮርሱ ተማሪዎች የኢንጂነሪንግ ችግር ፈቺ ሒደትን በመጠቀምና ሶፍትዌር ዲዛይን በማድረግ መፍትሔዎችን ለመፈለግና ባለ ብዙ ክፍል ፕሮጀክቶችን በመፍጠር ኢንዱስትሪያዊ ሒደትን የሚተገብሩባቸውን ተግባራት ያካትታል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው CO2 Drag Racer Project ሲሆን ተማሪዎች ንድፍ ማውጣትና AutoCAD ዲዛይን ያደርጋሉ፤ ሞዴሎችን በቁሳቁስ ላብራቶሪ ውስጥ መብሳት፣ መቁረጥ፣ ማለስለስና ማጠናቀቅ ይችላሉ፤ ከዚያም የፍጥነትና የነፋስ ቱቦ ትንተናን ያካሂዳሉ።*

*ተማሪዎች:-*
- *ስለ ሲስተሞች ምንነት ተገንዝበው በተለያዩ የቴክኖሎጂ መስኮች ውስጥ አካላቸውንና ንዑስ ሲስተማቸውን መለየት ይችላሉ ለምሳሌ በኮንስትራክሽን፣ ትራንስፖርት፣ ኮሙኒኬሽን፣ እና ኤሌክትሮኒክስ ዘርፍ።*
- *ለተምሳሌታዊ ተግዳሮቶች መፍትሔ ለመፈለግ የኢንጂነሪንግ ችግር ፈቺ ሒደቶችን ይጠቀማሉ።*
- *ሲስተም ማለት እርስ በርሳቸው የተሳሰሩና የሚፈለገውን ውጤት ለማስገኘት በጋራ የሚሰሩ አካላት ስብስብ እንደሆነ ይገልጻሉ።*
- *ስለ ግቤት፣ ሒደት፣ ውጤት፣ እና ግብረ-መልስ ለማወቅ ቴክኖሎጂያዊ ሲስተሞችን ያጠናሉ፣ ይገነባሉ።*
- *የችግርን ልዩታ፣ ምርምርና ጥናት፣ ፈጠራና ኢኖቬሽን፣ እና በችግር አፈታት ላይ የሙከራ ስራ መስራት ይችላሉ።*
- *ከመዋቅሮች፣ የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች፣ ግራፊክ ዲዛይን፣ 3D ሞዴሊንግ፣ ሮቦቲክስ ወይም ሌሎች ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎች ጋር የተያያዙ የኢንጂነሪንግ ተግዳሮቶችን ለመፍታት መፍትሔዎችን ቀርጸው ያደራጃሉ።*
- *ችግሮችን በመፍታትና ፕሮቶታይፖችን በመፍታት ረገድ የቡድን ስራንና ትብብርን ይለማመዳሉ።*
- *የፕሮዳክሽን ላብራቶሪውን መሳሪያዎች፣ ማሽኖችና ዕቃዎች በትክክልና ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ያንቀሳቅሳሉ።*
- *የተሻለውን ሃሳብ የመምረጥ ግብን በመያዝ አማራጭ መፍትሔዎችን መርምረው፣ የመመዘንና የመገምገም ስራ ይሰራሉ።*
- *በንድፎች፣ ባለ ብዙ ዕይታ ስእሎችና በኮምፒዩተር የሚታገዝ የዲዛይን ሶፍትዌርን በመጠቀም ሃሳቦችን ማስተላለፍ ይችላሉ*

**የዓለም ቋንቋዎች**
በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ የሚማሩ የ7-12ኛ ክፍል ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውንና የዓለም ቋንቋዎችን በማጥናታቸው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የዓለም ቋንቋ ክሬዲት ሊያገኙ ይችላሉ። የዓለም ቋንቋዎች ክሬዲት ለማግኘት፣ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው:-
- ለእያንዳንዱ ክሬዲት ቢያንስ የ140 ሰዓት <u>መደበኛ</u> የቋንቋ ትምህርት ስለመማሩ የሚያረጋግጥ ትራንስክሪፕት መቅረብ አለበት።
- ተማሪው የማለፊያ ነጥብ ያገኘ መሆን አለበት።
- ተማሪው በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ በቋንቋው ለመቀጠል ከፈለገ፣ በኮርሱ ያገኘው ውጤት “C” ወይም የተሻለ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።
- በፈተና ምዘና በግዛት ደረጃ የተፈቀደ ክሬዲት ተወስዶ ተማሪውም እስከ አራት ክሬዲት ሊያስገኝለት የሚችል የብቃት ደረጃ ያሳዬ መሆን አለበት።

በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ በትምህርትነት የሚሰጡ ሌሎች ቋንቋዎችን የሚናገሩ ተማሪዎች ለምደባ ፈተና ከአማካሪዎች ጋር መመካከር አለባቸው። በምደባ ፈተና ላይ በመመርኮዝ አንድ ተማሪ በከፍተኛ-ደረጃ የዓለም ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከተመደበ ተማሪው ለተዘለሉት ኮርሶች ክሬዲት ለማግኘት በስቴቱ-ደረጃ የጸደቀ በብቃት ላይ የተመሠረተ ፈተና የመውሰድ አማራጭ አለው።

*የአድቫንስድ ስተዲስ ዲፕሎማ ለማግኘት የሚፈልጉ ተማሪዎች በአንድ ቋንቋ የሶስት ዓመት/ደረጃ ወይም በሁለቱ ቋንቋዎች የሁለት ዓመት ጥናት በማጠናቀቅ ወይም በስቴቱ-ደረጃ የጸደቀ በብቃት ላይ የተመሠረተ ፈተና የዓለም ቋንቋ መስፈርቶችን ማሟላት ይችላሉ። ኢያንዳንዱን የዓለም ቋንቋ ኮርስ በሚገባ ማጠናቀቅ ለአድቫንስድ ስተዲስ ዲፕሎማ አንድ ክሬዲት ያስገኛል።*

አንድ ወይም ተጨማሪ የአረብኛ እና ቻይንኛ እና ላቲን የክፍል ደረጃዎች በርቀት የትምህርት ቴክኖሎጂዎች በኩል ሊሰጡ ይችላሉ። በግዛቱ ውስጥ ወይም በሃገሪቱ ውስጥ በሌላ ቦታ የሚገኙ የርቀት ትምህርት ሰጪዎች የሚሰጧቸው ኮርሶች ከ APS የተለየ የውጤት አሰጣጥ፣ የቤት ስራና አቴንዳንስ ፖሊሲ ሊኖራቸው ይችላል።

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ (ASL) በቨርጂኒያ ዩኒቨርሲቲና የማህበረሰብ ኮሌጅ የመግቢያ መስፈርቶች ውስጥ እንደ ዓለም ቋንቋ ሊቆጠር ይችላል። ከግዛቱ ውጭ ያሉ እና የግል አንዳንድ ድሕረ ሁለተኛ ደረጃ ተቋማት ASL እንደ ዓለም ቋንቋ አይቆጥሩትም። ASL ዓለም አቀፍ የባካሎሪያ ቋንቋ አይደለም።**

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ I (15990)**
***ሙሉ ዓመት፣ አንድ ክሬዲት***

*በቅድሚያ የሚወሰድ፦ ምንም*

*ተማሪዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር በቤት፣ በት/ቤትና በማህበረሰብ አካባቢዎች ውስጥ በሚያደርጉት ዕለታዊ መስተጋብር አውድ ውስጥ መቀበያ እና ገላጭ ቋንቋን ይማራሉ። ተማሪዎች ስለ ቤተሰብ፣ ስለ ት/ቤት ዝግጅቶችና ስለ በዓላት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስን ይማራሉ። ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን መለዋወጥ ይችላሉ ለምሳሌ ራስን ማስተዋወቅ፣ ፈቃድ መጠየቅ፣ ትኩረት ማግኘትና አግባብነት ያላቸውን ማንዋል ያልሆኑ ባህርያትን (ለምሳሌ፦ የፊት ገለጻ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ስፓሻል አደረጃጀት) በመጠቀም የመፈረሚያ አካባቢን መደራደር ይችላሉ። ተማሪዎች የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን ታሪክ ተምረው መስማት የተሳናቸውን ሰዎች ባህል ያጠናሉ።*

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ II (15995)**
**ሙሉ ዓመት፣ አንድ ክሬዲት**

*በቅድሚያ የሚወሰድ፦ የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ I በስኬት ማጠናቀቅ*

*ተማሪዎች በ ASL ውስጥ ያለውን የግንኙነት ችሎታ ያሰፋሉ እንዲሁም ያዳብራሉ። ለማብራሪያ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ እንዲሁም ይመልሳሉ እንዲሁም የዕለት ተዕለት ልምዶችን እና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ አስተያየቶችን እና ምርጫዎችን የበለጠ መግለጽ ይችላሉ። ተማሪዎች የበለጠ ረቂቅ ርዕሶችን እና የስነ-ጽሑፍ ስራዎችን በማጥናት የቃላት እና የንግግር ችሎታቸውን ያሰፋሉ። ስለ መስማት የተሳናቸው ማህበረሰብ እና ለቋንቋ ትምህርት ስላላቸው አንድምታ ጥልቅ ግንዛቤ ይጨብጣሉ። ከመማሪያ የክፍል ደረጃ ባሻገር የ ASL ችሎታቸውን በመጠቀም ከሌሎች ጋር እንዲገናኙ ይበረታታሉ።*

**አረብኛ I፣ ሙሉ ዓመት (15800)**

*ይህ ደረጃ ተማሪዎች የአረብኛ ፊደላትንና የድምፅ ስርዓትን እንዲያውቁ ያስችላል። ይህ ኮርስ በባህላዊና ታሪካዊ መረጃዎች በጣም የበለጸገ ነው። የአረብኛ ቋንቋ፣ የአረብኛ ቋንቋ የዘር ግንድና ስክሪፕት ታሪክ ይሰጣሉ። በድምፅና በአጻጻፍ ስርዓቶች ላይ መጀመሪያ ከሚሰጠው ትኩረት በተጨማሪ፣ ተማሪዎች ድምጾችን መማርና ማራባት፣ ለአካሄዶች አጽንኦት መስጠትና ስለቋንቋው የድምፅ ቃና ይማራሉ። መሰረታዊ የሰዋሰው አወቃቀሮችና የቃላት ብዛት የሚተዋወቁ ሲሆን፣ ይህም የሚደረገው ተማሪዎች በጣም መሰረታዊ የሆኑ መደበኛ የመልእክት ልውውጦችን በቀላል ዓረፍተ ነገሮችና የመልእክት ልውውጦች ለደረጃው አግባብነት ባላቸው አውዶች መግለጽ ይችላሉ። ተማሪዎች የሚነበቡላቸውን ቃላትና ዓ.ነገሮች በትክክል መጻፍ ይችላሉ፣ ከዚህ በፊት የተማሯቸውን ቃላትና ዓ.ነገሮች ማንበብ፣ ለሌሎች ሰዎች ሰላምታ መስጠት፣ እና ራስን ማስተዋወቅ፣ ቀላል ጥያቄዎችና መልሶችን ማዘጋጀት፣ መሰረታዊ ማህበራዊ ተግባቦቶች ውስጥ መሳተፍ፣ ስለራሳቸው፣ ስለቤተሰብ አባላቶቻቸውና ስለሌሎች ሰዎች መናገርና መሰረታዊ የሆኑ ግላዊ መረጃዎችን መለዋወጥ ይችላሉ። ቋንቋ የሚዳብርበት መሰረታዊ ርእስ የግልና የቤተሰብ ሕይወት ነው።*

**አረብኛ II፣ ሙሉ ዓመት (15822)**

*በቅድሚያ የሚወሰድ፦ አረብኛ I በሚገባ ማጠናቀቅ ወይም መምህሩ በሚወስነው መሰረት ተመጣጣኝ ብቃት ያለው መሆን አለበት*

ይህ ኮርስ በተወሰነ የብቃት ደረጃ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ፣ እና የመጻፍ ክህሎት ማሳደጉን የሚቀጥል ሲሆን በአረብኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሃገራት ውስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች በዕለታዊ ሕይወታቸው ውስጥ በሚያጋጥሟቸው ሁኔታዎች ላይ ያጠነጥናል።

*ተማሪዎች የቃላት ብዛታቸውን በማሳደግ ስለ መሰረታዊ የአረብኛ ዓረፍተ ነገር አወቃቀር ተጨማሪ ነገር በመማር በተግባራዊ ቋንቋ ውስጥ ለመሳተፍ መሰረታዊ የሰዋሰው መዋቅሮችን መተግበርን ይማራሉ። ተማሪዎች አረብኛ II ሲያጠናቅቁ ማህበራዊ ተግባቦቶችን ለማስጀመር የሚችሉ ሲሆን መሰረታዊ የባህል አተያዮችንም ማወቅ ይችላሉ። ተማሪዎች ቀላል ጥያቄዎች፣ አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችና በተለይ በሚታወቁ አርእስት ላይ በጣም ተደጋጋሚ ትእዛዞችን ለመረዳትና ምላሽ ለመስጠት ይችላሉ። ተማሪዎች ከዚህ በፊት የተለማመዱትን ወይም የሚያስታውሱትን ዓ.ነገርና ሐረጎች በመጠቀም ሰዎችን መግለጽ፣ ምን እንደሚመስሉና ምን እንደሚሰማቸው መናገር፣ ስለ ትርፍ ጊዜ ስራ መረጃ መለዋወጥና ከዚህ በፊት የተማሩትን ማቴሪያል ተጠቅመው ቀላል ዓ.ነገሮችና አንቀጾችን ለማንበብና ለመጻፍ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በመደበኛው አረብኛና በንግግር አረብኛ መካከል ያሉትን አንዳንድ ልዩነቶች ያውቃሉ። በዚህ ውስጥ የሚካተቱ አርእስት የት/ቤትና የቤት ሕይወት፣ ግብይት መፈጸም፣ ሬስቶራንቶች፣ እና ምግብን ጨምሮ ማሕበራዊ ሕይወትና የግል ፍላጎቶችና የማህበረሰብ ሕይወት ናቸው።*

**ቻይንኛ I፣ ሙሉ ዓመት (15615)**

*ተማሪዎች መሰረታዊ የቋንቋ አወቃቀሮችን የያዙ ቀላል ዓ.ነገሮችን በመጠቀም ስለራሳቸውና በቅርባቸው ስላለ አካባቢ መልዕክት የማስተላለፍ ችሎታቸውን ያዳብራሉ። ይህ የመልዕክት ልውውጥ በአራቱም የቋንቋ ክህሎቶች ውስጥ ይንጸባረቃል፦ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣ እና መጻፍ። ይህ ኮርስ የማዳመጥና የመናገር ክህሎቶችን ለማሳደግ አጽንኦት ይሰጣል። ተማሪዎች ከፒንይን ጋር የሚተዋወቁ እና በዚህ ደረጃ ውስጥ ከታሰቡት ጭብጦችና ሰዋሰዋዊ ክፍሎች ጋር የሚያያዙ ቀላል የቻይንኛ ፊደላትንም ይማራሉ። ተማሪዎች ፊደላትን በትክክል በመለየት ለማንበብ ብቻ ሳይሆን የመጻፍ ችሎታቸውንና በኮምፒዩተሮች እና ሌሎች ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ላይ በጽሑፍ መልእክት ለመለዋወጥ በሚያስችል መልኩ ለማሳደግ ይማራሉ። ተማሪዎች የግልና የቤተሰብ ሕይወት፣ የት/ቤት ሕይወት፣ ማሕበራዊ ሕይወትና የማህበረሰብ ሕይወትን በተመለከተ መዳሰስና ማጥናት ይጀምራሉ።*

**ቻይንኛ II፣ ሙሉ ዓመት (15625)**

*በቅድሚያ የሚወሰድ፦ ቻይንኛ I በሚገባ ማጠናቀቅ ወይም መምህሩ በሚወስነው መሰረት ተመጣጣኝ ብቃት ያለው መሆን አለበት።*

*ተማሪዎች መሰረታዊ የቋንቋ አወቃቀሮችን የያዙ ቀላል ዓ.ነገሮችን በመጠቀም ስለራሳቸውና በቅርባቸው ስላለ አካባቢ መልዕክት የማስተላለፍ ችሎታቸውን ማዳበራቸውን ይቀጥላሉ። ይህ የመልዕክት ልውውጥ በአራቱም የቋንቋ ክህሎቶች ውስጥ ይንጸባረቃል፦ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣ እና መጻፍ፤ በቃልና በጽሑፍ መልእክት ለመግለጽ ችሎታም አጽንኦት ይሰጠዋል። ተማሪዎች በደረጃ I ውስጥ የተማሩትን የግልና የቤተሰብ ሕይወት፣ የት/ቤት ሕይወት፣ ማሕበራዊ ሕይወትና የማህበረሰብ ሕይወትን በተመለከተ ጥናታቸውን ማስፋታቸውን ይቀጥላሉ። ተማሪዎች በቀላል ቻይንኛ የመጻፍ ክህሎታቸውን ማጥራት ይቀጥላሉ። ተማሪዎች ፊደላትን በትክክል በመለየት ለማንበብ ብቻ ሳይሆን የመጻፍ ችሎታቸውንና በኮምፒዩተሮች እና ሌሎች ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ላይ በጽሑፍ መልእክት ለመለዋወጥ በሚያስችል መልኩ ለማሳደግ ይማራሉ። በደረጃ I ውስጥ ከተማሯቸው ፊደላት በተጨማሪ ተማሪዎች ከፒንይን ጋር የሚተዋወቁ ሲሆን በዚህ ደረጃ ውስጥ ከታሰቡት ጭብጦችና ሰዋሰዋዊ ክፍሎች ጋር የሚያያዙ ቀላል የቻይንኛ ፊደላትንም ይማራሉ።*

**ፈረንሳይኛ I፣ ሙሉ ዓመት (15110)**

ቋንቋውን የመማር ትኩረት በተጨባጭ ሕይወት፣ በውይይቶች፣ ስኪትስና ሌሎች ፈጠራዊና ተጨባጭ ተግባራት አማካይነት ቋንቋውን ስራ ላይ ማዋል ነው። ተማሪዎች በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብና በመጻፍ ተግባራት አማካይነት ክህሎታቸውን ያዳብራሉ፣ መሰረታዊ መዋቅሮችና የቃላት ብዛታቸውን ያሳድጋሉ።

*ተማሪዎች፦*

- *ሰላምታዎች፣ ስንብቶችና የአክብሮት መግለጫዎችን ይጠቀማሉ።*
- *ስለ ጓደኞች፣ ስለቤተሰብና ት/ቤት በሚደረግ መሰረታዊ ጭውውት ላይ ይሳተፋሉ።*
- *በሚያውቁት ማቴሪያል ላይ ተመስርተው ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ ይችላሉ።*

- የምግብ ዝርዝሮች፣ ምልክቶች፣ የጊዜ መርሃ ግብሮችና ሌሎች እውነተኛ ማቴሪያሎችን ያነብባሉ።
- አጫጭር መግለጫዎች፣ መልዕክቶችና የተመሩ ድርሰቶችን ይጽፋሉ።
- በተደራሹ ቋንቋ ባሕሎች ዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ስላሉ ገጽታዎች ይማራሉ።

**ፈረንሳይኛ II፣ ሙሉ ዓመት (15120)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ:- ፈረንሳይኛ I በሚገባ ማጠናቀቅ ወይም መምህሩ በሚወስነው መሰረት ተመጣጣኝ ብቃት ያለው መሆን አለበት።*
ተማሪዎች በተደራሹ ቋንቋ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ብቃታቸውን ማሳደጋቸውን የሚቀጥሉ ሲሆን ስለ ቋንቋው ባህላዊ ገጽታዎችም ሰፋ ያለ ግንዛቤን ያዳብራሉ።

*ተማሪዎች:-*

- የወደፊትና የሃላፊ ጊዜን በመጠቀም ራሳቸውን መግለጽ፣ ስለጓደኞች፣ ቤተሰብና ት/ቤት ነክ አርእስት፣ ስሜቶች፣ ጊዜ፣ የአየር ሁኔታና አድራሻ ለማውራትና ለመጻፍ ይችላሉ።
- ከተማሩት ማቴሪያል ጋር ይበልጥ ስሜታዊና ሁኔታዊ ውይይቶች ላይ ይሳተፋሉ።
- መሰረታዊ የስነ-ሕዝብ መረጃ ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ ያካሂዳሉ።
- አስተያየቶችን፣ መውደድን እና መጥላትን ይገልጻሉ።
- ለእውነተኛ የሚነበብ ማቴሪያል አጸፋዊ ምላሽ ይሰጣሉ።
- በፈጠራዊ የአጻጻፍ ተግባራት ራሳቸውን መግለጽ ይጀምራሉ።
- በዩናይትድ ስቴትስና በተደራሽ ባህሎች መካከል ያሉትን ተመሳሳይነቶችና ልዩነቶች ያውቃሉ።

**ላቲን I፣ ሙሉ ዓመት (15310)**
በዚህ የመጀመሪያ የላቲን ኮርስ፣ ተማሪዎች ከጥንታዊ ሮም ቋንቋና ሕይወት ጋር ይተዋወቃሉ። የላቲን I ተቀዳሚ ዓላማ የንባብ ክህሎቶችን ማዳበር ሲሆን፣ ይህም በማዳመጥ፣ መናገርና መጻፍ ክህሎቶች የሚደገፍ ነው።
*ተማሪዎች:-*

- ውርስ የላቲን ትረካዎችና ቀላል ኦሪጂናል ላቲን ያነብባሉ።
- የላቲን አነጋገርን መሰረታዊ ክፍሎች ይገነዘባሉ።
- መሰረታዊ የላቲን ቃላት ግንባታን ይማራሉ።
- የላቲን ስሞችና ግሶች መጨረሻና ተግባራቶቻቸውን ይማራሉ።
- የጀማሪ ላቲን ሰዋሰውን መሰረታዊ ግንዛቤ ያዳብራሉ።
- የላቲን ስርወ ቃላት፣ ቅድመ ቅጥያዎችና ድሕረ ቅጥያዎችን በማጥናት በላቲን እና በእንግሊዝኛ ውስጥ የቃላት ግንባታን እውቀት ይጨምራሉ።
- ስለ ሮማውያን ዕለታዊ ሕይወት፣ ልማድ፣ መንግስትና አፈ ታሪክ ይማራሉ።

**ላቲን II፣ ሙሉ ዓመት (15320)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ:- ላቲን I በሚገባ ማጠናቀቅ ወይም መምህሩ በሚወስነው መሰረት ተመጣጣኝ ብቃት ያለው መሆን አለበት።*
ተማሪዎች ይበልጥ ውስብስብና እውነተኛ የሆኑ የላቲን ጽሑፎችን በማንበብ ክህሎታቸውን ያሰፋሉ። የሮማውያን ባህል፣ ታሪክና አፈ ታሪክ በበለጠ ጥልቀት ያጠናሉ።
*ተማሪዎች:-*

- ረዘም ያሉና ይበልጥ አስቸጋሪ የሆኑ ውርስ የላቲን አንቀጾችን ያነብባሉ።
- ኦሪጂናል የላቲን አንቀጾችን በስድ ንባብና በግጥም ማንበብ ይጀምራሉ።
- የላቲን ቃላት እውቀትን ያሰፋሉ።
- እንደ አርእስት፣ የሩቅ ሃላፊ እና ፍላጎትን ገላጭ ግስ የመሳሰሉ የላቲን ቃላትን ቅርጽ መማራቸውን ይቀጥላሉ።
- ውስብስብ የሰዋሰው መርሆዎች ጋር ራሳቸውን ያለማምዳሉ።
- የላቲን ቋንቋ በእንግሊዝኛ እና በሮማውያን ቋንቋዎች ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ ይበልጥ ግልጽ በሆነ መንገድ ማየት ይችላሉ።

**ስፓኒሽ I፣ ሙሉ ዓመት (15510)**
ቋንቋውን የመማር ትኩረት በተጨባጭ ሕይወት፣ በውይይቶች፣ ስኪትስና ሌሎች ፈጠራዊና ተጨባጭ ተግባራት አማካይነት ቋንቋውን ስራ ላይ ማዋል ነው። ተማሪዎች በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብና በመጻፍ ተግባራት አማካይነት ክህሎታቸውን ያዳብራሉ፣ መሰረታዊ መዋቅሮችና የቃላት ብዛታቸውን ያሳድጋሉ።
*ተማሪዎች:-*

- ሰላምታዎች፣ ስንብቶችና የአክብሮት መግለጫዎችን ይጠቀማሉ።
- ስለ ጓደኞች፣ ስለቤተሰብና ት/ቤት በሚደረግ መሰረታዊ ጭውውት ላይ ይሳተፋሉ።
- በሚያውቁት ማቴሪያል ላይ ተመስርተው ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ ይችላሉ።
- የምግብ ዝርዝሮች፣ ምልክቶች፣ የጊዜ መርሃ ግብሮችና ሌሎች እውነተኛ ማቴሪያሎችን ያነብባሉ።
- አጫጭር መግለጫዎች፣ መልዕክቶችና የተመሩ ድርሰቶችን ይጽፋሉ።
- በተደራሹ ቋንቋ ባሕሎች ዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ስላሉ ገጽታዎች ይማራሉ።

**ስፓኒሽ II፣ ሙሉ ዓመት (15520)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ:- ስፓኒሽ I በሚገባ ማጠናቀቅ ወይም መምህሩ በሚወስነው መሰረት ተመጣጣኝ ብቃት ያለው መሆን አለበት*
ተማሪዎች በተደራሹ ቋንቋ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ብቃታቸውን ማሳደጋቸውን የሚቀጥሉ ሲሆን ስለ ቋንቋው ባህላዊ ገጽታዎችም ሰፋ ያለ ግንዛቤን ያዳብራሉ።
*ተማሪዎች:-*

- የወደፊትና የሃላፊ ጊዜን በመጠቀም ራሳቸውን መግለጽ፣ ስለጓደኞች፣ ቤተሰብና ት/ቤት ነክ አርእስት፣ ስሜቶች፣ ጊዜ፣ የአየር ሁኔታና አድራሻ ለማውራትና ለመጻፍ ይችላሉ።
- ከተማሩት ማቴሪያል ጋር ይበልጥ ስሜታዊና ሁኔታዊ ውይይቶች ላይ ይሳተፋሉ።
- መሰረታዊ የስነ-ሕዝብ መረጃ ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ ያካሂዳሉ።
- አስተያየቶችን፣ መውደድን እና መጥላትን ይገልጻሉ።
- ለእውነተኛ የሚነበብ ማቴሪያል አጸፋዊ ምላሽ ይሰጣሉ።
- በፈጠራዊ የአጻጻፍ ተግባራት ራሳቸውን መግለጽ ይጀምራሉ።
- በዩናይትድ ስቴትስና በተደራሽ ባህሎች መካከል ያሉትን ተመሳሳይነቶችና ልዩነቶች ያውቃሉ።

**ስፓኒሽ አቀላጥፈው ለሚናገሩ I፣ ሙሉ ዓመት (15517)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ:- በመምህሩ በሚወስነው መሰረት በስፓኒሽ ንግግር ልህቀትን በተግባር ማሳየት*
ይህ ኮርስ የተቀረጸው በስፓኒሽ ቋንቋ አፍ መፍቻ ቋንቋ በሚመስል ደረጃ ብቃት ኖሯቸው በስፓኒሽ መሰረታዊ የንባብና የመጻፍ ክህሎቶችን በላቀ ብቃት ማከናወን ላልቻሉ ተማሪዎች ነው። ተማሪዎች በንባብ፣ በአጻጻፍና በንግግር ላይ የተግባቦት ክህሎታቸውን በማዳበር የስፓኒሽ ሰዋሰው ማጥናት ይጀምራሉ። ተማሪዎች ስለሂስፓኒክ ባሕል አተያዮችና ልማዶች ጥልቅ ግንዛቤ ያዳብራሉ።

**ስፓኒሽ አቀላጥፈው ለሚናገሩ II፣**
**ሙሉ ዓመት (15527)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ:- ስፓኒሽ አቀላጥፈው ለሚናገሩ I በሚገባ ማጠናቀቅ ወይም በምደባ ፈተና በሚወሰነው መሰረት በቋንቋው ተመጣጣኝ ብቃት ያለው መሆን አለበት*

ይህ ኮርስ የተዘጋጀው ቀደም ሲል በመሰረታዊ ደረጃ ስፓኒሽ ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ተማሪዎች ነው። ተማሪዎች የቃላት አጻጻፋቸውንና ሜካኒክስ በማሻሻል አጫጭር ድርሰቶችን ይጽፋሉ። ወጥ ስራዎችን ማንበብና ትረካዎችና ግጥሞችን መተርጎም እና/ወይም መተንተን ይጀምራሉ። የሰዋሰው ጥናት ይቀጥላል። ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚኖራቸው ፕረዘንቴሽንና ሌሎች የእርስ በርስ ተግባራት አማካይነት የቃል ተግባቦት ክህሎታቸውን ያሻሽላሉ። ባህላዊ አተያዮች ልማዶች ይፈተሻሉ፣ በስነ-ጽሑፍ አውድ በኩልም ጥልቅ የሆነ ግንዛቤ ይፈጠራል።

**ስፓኒሽ አቀላጥፈው ለሚናገሩ III፣**
**ሙሉ ዓመት (15537)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ፦ ስፓኒሽ አቀላጥፈው ለሚናገሩ II በሚገባ ማጠናቀቅ ወይም በምደባ ፈተና በሚወሰነው መሰረት በቋንቋው ተመጣጣኝ ብቃት ያለው መሆን አለበት*
ይህ ኮርስ የተቀረጸው ይበልጥ አድቫንስድ በሆነ ደረጃ ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ተማሪዎች ነው። ተማሪዎች ደብዳቤዎችን፣ ድርሰቶችንና ሪፖርቶችን መጻፍና ይበልጥ ውስብስና ረዘም ያሉ ትረካዎችን መተርጎም እና/ወይም መተንተን ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች በተለያዩ አርእስት ላይ የቃልና የጽሑፍ ሪፖርቶችን ያቀርባሉ። ባህላዊ አመለካከቶችና ልማዶች ይፈተሻሉ፣ በስነ-ጽሑፍ አውድ በኩልም ጥልቅ የሆነ ግንዛቤ ይፈጠራል።

**GUNSTON መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

**የስፓኒሽ ባለ ሁለት ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም**

የስፓኒሽ ባለ ሁለት ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች የስፓኒሽ ቋንቋን ጥበብ፣ ማህበራዊ ጥናትና ሳይንስ (የሳይንስና ማህበራዊ ጥናቶችን ስርዓተ ትምህርት መግለጫ ተመልከት) በስፓኒሽ ለ6ኛ፣ 7ኛና 8ኛ ክፍሎች ይማራሉ።

**የስፓኒሽ ቋንቋ አርትስ**
የስፓኒሽ ቋንቋ አርትስ ፕሮግራም የሁለት ቋንቋ ተማሪዎች በስፓኒሽ አዳምጦ የመረዳት፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ እድሎችን ይፈጥርላቸዋል። ባህላዊ አሰራሮችና አተያዮች ላይ ግንዛቤን ለማሳደግ አጽንኦት ይሰጣል።

የስፓኒሽ ቋንቋ አርትስ ፕሮግራም ተማሪዎች የሚከተሉትን ደረጃዎች የያዘ ሒደትን እንዲከተሉ ይጠይቃል፡-
1. መረጃ መሰብሰብ
2. ፕሮጀክተቶች ውስጥ መሳተፍ
3. በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ መስራት
4. የቃል መግለጫዎችን መስጠት
5. በስራ ላይ ሃሳብን መግለጽና መመዘን

የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች፡-
- የተለያዩ አርእስትን በሚሸፍኑ ጭውውቶች ላይ ይሳተፋሉ።
- አንብቦ ለመረዳት አግባብነት ያላቸው የንባብ ስትራቴጂዎችን ይተገብራሉ።
- ለመዝናናት ማንበብና በስነ-ጽሑፍ ቡድኖች ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ።
- በተለያዩ ዘውጎች ውስጥ ይጽፋሉ።
- የሚማሩትን ባህል ቋንቋ፣ የአኗኗር ዘይቤና እሴቶች ከራሳቸው ጋር ያወዳድራሉ/ያነጻጽራሉ።
- የባህል ብዝሃነት የአንድ ማህበረሰብ የማይነጣጠል መገለጫ መሆኑን እውቅና ይሰጣሉ።

የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች፡-
- መጠነ ሰፊ አርእስትን በሚሸፍኑ ጭውውቶች ላይ ይሳተፋሉ።
- አንብቦ ለመረዳት አግባብነት ያላቸው የንባብ ስትራቴጂዎችን ይተገብራሉ።
- ለመዝናናት ማንበብና በስነ-ጽሑፍ ቡድኖች ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ።
- በተለያዩ ዘውጎች ውስጥ ይጽፋሉ።
- በጽሑፍ አማካይነት የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን ያሰባስባሉ።
- የቋንቋን ጥናት ከሌሎች አካዳሚክ ከሆኑና ካልሆኑ መስኮች ጋር ያስተሳስራሉ።
- የሂስፓኒክ ባህል በአሜሪካውያን ቅርስ ላይ ስላሳደረው ተጽእኖ መሰረታዊ ግንዛቤ ያዳብራሉ።
- በእውነተኛ ምንጮች አማካይነት ስለ ሂስፓኒክ ባህል መረጃ ያገኛሉ።

የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች፡-
- የተለያዩ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችና ቃላት ያሉትን ውስብስብ ንግግር ይረዳሉ።
- መጠነ ሰፊ አርእስትን በሚሸፍኑ ጭውውቶች ላይ ይሳተፋሉ።
- አንብቦ ለመረዳት አግባብነት ያላቸው የንባብ ስትራቴጂዎችን ይተገብራሉ።
- መረጃ ለማግኘትና ለመዝናናት ያነብባሉ።
- ንባቦችን ከታሪካዊና ባህላዊ ተጽእኖዎች ጋር ያስተሳስራሉ።
- ገላጭ አጻጻፍን ያዳብራሉ።
- ከመማሪያ ክፍል ውጭ መዳረሻ ቋንቋውን መጠቀም ይጠበቅባቸዋል።
- መዳረሻ ቋንቋው በሚነገርባቸው የተለያዩ ሃገራት ውስጥ ስላሉ ባህሎች መረጃ ያገኛሉ።

*ማስታወሻ፡- ይህ ኮርስ 7ኛና 8ኛ ክፍል ለተመዘገቡ ተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት አለው፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶችም ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል። እባክዎ ለተጨማሪ መረጃ ገጽ 56ን ይመልከቱ።*

**ሞንቴሶሪ**

በገንስተን የሞንቴሶሪ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም በጊዜ ክፍልፋይና የተለያየ የዕድሜ ክልል ላይ በሚያስተምሩ መማሪያ ክፍሎች አማካይነት የእርስ በርስ የመማር ተሞክሮዎችን ያጎለብታል። የ6ኛና 7ኛ ክፍል ተማሪዎች በሞንቴሶሪ ማህበረሰብ ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት፣ ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ እና ታሪክን ይማራሉ፤ በምርጫ የሚወሰዱ ኮርሶችን መምህራን በልማዳዊው የ Gunston ፕሮግራም ውስጥ

ያስተምራሉ። የ8ኛ ክፍል ሞንቴሶሪ ተማሪዎች ለጂኦግራፊና ሒሳብ ወደ ልማዳዊ የትምህርት ክፍሎች የሚሸጋገሩ ሲሆን ለሳይንስና እንግሊዝኛ ደግሞ በሞንቴሶሪ ውስጥ ይቆያሉ።

ከአካዳሚክስ በተጨማሪ፣ ፕሮግራሙ የተቀረጸው የተማሪዎችን አካዳሚክ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ዕድገትን ለመደገፍ ነው። እነዚህ መስኮች በሞንቴሶሪ ትምህርት ውስጥ የማይነጣጠሉ ናቸው። የሞንቴሶሪ የመከካለኛ ዓመታት ፕሮግራም የተቀረጸው ውጤታማ ተግባቦት፣ ለሌሎችና ለአካባቢ ርህራሄና እንክብካቤ ማድረግ፣ የግጭት አፈታት ክህሎቶችን፣ ለአዳዲስ ልምዶች ራስን ክፍት ማድረግ፣ ለሕይወት የጋለ፣ በእንክብካቤ የተሞላና አዎንታዊ አመለካከት ማዳበርን ለመደገፍ ታስቦ ነው። የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች ራሳቸውን ነጻ ለማድረግና ነጻነታቸውን ለማስጠበቅ ጥረት ሲያደርጉ፣ መማሪያ ክፍሉ ደግሞ ማህበራዊ ሃላፊነትና ዲስፕሊን ባለበት ሁኔታ የምርጫ ነጻነት ያስገኝላቸዋል። መምህራን እንደ አርአያ ሰባት ሆነው የምርመራ ጥያቄን፣ ፈጠራዊ ችግር አፈታት፣ ትብብርና ማህበራዊ ትስስርን በትምህርት በኩል ለማጎልበት መሪ ሆነው ይሰራሉ።

ዓለም አቀፍ የባካሎሪያ መካከለኛ ዓመታት ፕሮግራም (IBMYP) የተቀረጸው ተማሪዎች በተለዋዋጭና እርስ በርስ በተሳሰረ ዓለም ውስጥ በንቃትና ሃላፊነት በተሞላው መንገድ ለመሳተፍ የሚያስፈልጋቸውን እውቀት፣ አመለካከት፣ እና ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ለማገዝ ነው። ይህም ማለት ከ"ማወቅ" በላይ የሚጠይቅ ስርዓተ ትምህርት ጋር መስተጋብር መፍጠር ማለት ነው። የአሰላሳይነት አስተሳሰብ፣ ጥልቅና ፈጠራ የችግር አፈታት፣ በግል አስተያየት ላይ ትንተና እና ውይይት ማድረግን ያካትታል።

በመላው ዓለም የሚገኙ መካከለኛ ዓመታት ፕሮግራሞች ፍልስፍናዊ መሰረት የተወሰዱ ሶስት መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች፡- ባህል ተሻጋሪ ግንዛቤ፣ ተግባቦትና ሁሉን አቀፍ ትምህርት። *ባህል ተሻጋሪ ግንዛቤ* ማለት ለሁሉም ሰዎች በሚገለጽ አክብሮት፣ መቀበል፣ እና ማመስገን የሚወክል ሲሆን ይህም የተለያዩ አተያዮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት በአካባቢ፣ ሃገራዊና ዓለም አቀፍ ማህበረሰቦችን ውስጥ ለመሳተፍ ወሳኝ ነው። *ተግባቦት* አንድ ወጣት ስኬታማ የመሆን ችሎታው ወሳኝ ክፍል ነው። IBMYP ሁሉም መምህራን የተግባቦት አስተማሪዎች ናቸው ብሎ የሚያስብ ሲሆን የእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት መምህር የተማሪዎችን የተግባቦት ክህሎቶች ለማሳደግ ላላቸው ወሳኝ ሚና አጽንኦት ይሰጣል። በሌላ ቋንቋ ግንኙነት ማድረግ መቻልም እንደዚሁ ጠቃሚ በመሆኑ እያንዳንዱ የ IBMYP ተማሪ ሁለተኛ ቋንቋ ይማራል። *ሁሉን አቀፍ ትምህርት* የሚወከለው ሃሳብ ሁሉም እውቀት እርስ በርስ የተሳሰረና ስርዓተ ትምህርቱም የመላውን ተማሪ ፍላጎቶች ማስተናገድ አለበት የሚለውን ነው። ተማሪዎች የተማሩትን ክህሎትና እውቀት በአዲስና ተዛማጅ ሁኔታዎች ላይ እንዲተገብሩ ሲጠየቁ ሁሉን አቀፍ ትምህርት ይመቻቻል። በተጨማሪም፣ የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን የሚያስተምሩ መምህራን በተለመዱ ጽንሰ ሃሳቦችና ጭብጦች ዙሪያ ትምህርትን በማቀድ በዲስፕሊኖቹ መካከል ትስስርን በተመለከተ ግንዛቤ ያሳድጋሉ። የ Thomas Jefferson መምህራን ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት መስኮችና ከክፍል ውጭ ወደሌላ አካል የሚተላለፍ የስራ ልማድ፣ ክህሎት፣ እና የስኬት አመለካከትን እንዲያዳብሩ ለማገዝ ይጥራሉ።

ሁሉም የ IB ፕሮግራሞች ትኩረት የ IB ተማሪ ፕሮፋይል ልዩ ባህርያት የመገለጫ ባህርያቸው አካል አድርገው የሚያዋህዱ ተማሪዎች ናቸው። እነዚህ ልዩ ጠባያት አስር መገለጫ ባህርያትና አመለካከቶች ሆነው የዓለም አቀፍ ማህበረሰብን የዕድሜ ልክ ተማሪዎች የሚያጎለብቱ ናቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እውቀት ያለው | አሰላሳይ | ነጻ አስተሳሰብ ያለው | መልእክት አስተላላፊ | ጠያቂ |
| አሳቢዎች | ሚዛናዊ | ለመርህ የሚገዛ | ስጋትን የሚጋፈጥ | ተንከባካቢ |

**ጥያቄ**
በ TJMS ውስጥ ያለን አካላት ግብ በጥያቄ ላይ የተመሰረቱና ተማሪዎች ምንጊዜም ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉባቸው የመማሪያ ክፍሎች እንዲኖሩ ማድረግ ነው። የተዘጋጀ ጥያቄ አቀራረብ ተማሪዎች ጥልቅ አሳቢዎች ሆነው ነገሮችን እንዲፈትሹና እንዲጎለብቱ የሚያስችላቸው ሲሆን የትምህርት ዓይነት መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች የሚሸፈኑ ሲሆን የመጠየቅ ክህሎቶችንም ይካናሉ። MYP ትምህርትን ለማቀድ የትብብር አቀራረብን መከተልን የሚጠይቅ ሲሆን ይህ ደግሞ ሁሉም ተማሪዎች ተመጣጣኝ የሆነ የትምህርት ዕድል እንዲኖራቸውና የግል ፍላጎቶቻቸው እንዲሟሉላቸው ለማስቻል ነው። የትምህርት ክፍሎችና ተዛማጅ የምዘና ተግባራት የሚታቀዱት በመምህራን ቡድኖች ነው። መምህራንም ተምህርቶችን እንዴት መለያየት እንዳለባቸው በትብብር ይሰራሉ። መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ሲያቅዱ፣ የመማሪያ ክፍሉ ደግሞ መምህራንና ተማሪዎች በማስተማርና መማር ሒደት ውስጥ በአጋርነት የሚሰሩበት ነው።

**እርምጃ**
በ MYP የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ንቁ በሆነ የመማሪያ ክፍል ተሳትፎ አማካይነት እርምጃ ይወስዳሉ። ተሳትፏቸው የሚያተኩረው ሃላፊነት ለተሞላባቸው ምርጫዎች አማራጮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተጨባጨን ዓለም ጉዳዮች መዳሰስ ይሆናል። ከሚወሰዱ እርምጃዎች መካከል ለራሳችንና ለሌሎች መሟገትና ማስተማር ይገኙበታል። እርምጃው የአገልግሎት ትምህርት ቅርጽ ሊይዝም ይችላል። ሁሉም ተማሪዎች በ Thomas Jefferson ውስጥ በሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ በአገልግሎት ተግባራት ውስጥ መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች በሳምንታዊ ተግባራት አማካይነት የአገልግሎት ሰዓት መሰብሰብ የሚችሉ ሲሆን በዚህም ውስጥ ት/ቤቱ የሚሰጣቸውም ይካተታሉ፤ ለምሳሌ በ Thomas Jefferson Community Garden መማርና መስራት። ሌሎች የአገልግሎት ዕድሎች ከስርዓተ ትምህርት ጋር የተያያዘ ጥያቄ ቀጥተኛ ውጤቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ተማሪዎች የአገልግሎት እድሎችን ሲከታተሉ፣ ጉዳዮችን ወይም መንስኤዎችን እንዲደግፉ ይበረታታሉ። በተወሰኑ የፍላጎት መስኮቻቸው ላይ መማርና መሳተፋቸው ለሚያስፈልጋቸው የ8ኛ ማህበረሰብ ፕሮጀክት፣ የ MYP መደምደሚያ እርምጃ ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የፍላጎት ርዕሳቸው ሆነው ብቅ ማለቱ አይቀርም።

**ማሰላሰል**
በ MYP መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ጥልቀት ባለው ማሰላሰል ውስጥ ይሳተፋሉ፣ ማስረጃን እንዴት እንደሚጠቀሙ፣ የተለያዩ ዘዴዎችን እንዴት እንደሚተገብሩና የተወሰኑ ውሳኔዎች ላይ እንዴትና ለምን እንደሚደርሱ በጥልቀት ያስባሉ። ተማሪዎች የራሳቸውን አስተሳሰብ እንዲተነትኑ፣ የሚፈጥሯቸውን የስሜት ማዳላት እንዲያውቁና በራሳቸውና በሌሎች ሰዎች ስራ ላይ ያሉ ስህተቶችን እንዲፈልጉ ይሞገታሉ።

በመጨረሻም፣ ተማሪዎች በ Jefferson ውስጥ በሚኖራቸው የ3 ዓመታት ቆይታ የ IBMYP ፖርትፎሊዮ ይገነባሉ። ይህ ፖርትፎሊዮ ተማሪዎች የ Jefferson Middle School ተልዕኮን ለማሳካት የሰሯቸውን ስራዎች ያንጸባርቃል፡-

**<u>የ6ኛ ክፍል IBMYP Four Rotation Elective ለ 2021-22</u>**

Thomas Jefferson መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የመካከለኛ ዓመታት ፕሮግራም (MYP) የሚያቀርብ የዓለም አቀፍ ባካሎሪያ ዓለም ት/ቤት ነው። IB እያንዳንዱ ተማሪ በሚከተሉት የትምህርት ዓይነቶች በእያንዳንዳቸው በዓመት ቢያንስ 50 ሰዓት እንዲኖራቸው ይጠይቃል፡- ሳይንስ፣ ዲዛይን ቴክኖሎጂ፣ ሂውማኒቲስ፣ ስነ-ጥበብ፣ ሒሳብ፣ ቋንቋ ኤ፣ ቋንቋ ቢ እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት። የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በ Four Rotation Elective ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፉ ሲሆን ይህም የ MYP መስፈርቶችን ለማሟላት ነው።

ሁሉም ተማሪዎች ዓመቱን በሙሉ በሁለት ቀን አንድ ጊዜ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ይወስዳሉ። በተጨማሪም፣ ዲዛይን ቴክኖሎጂን ከስነ-ጥበብ ጋር የሚያመጣጥኑ የትምህርት ክፍሎችን ይመርጣሉ። የስነ-ጥበብ ትምህርት ክፍሎች ድራማ፣ የሙዚቀኞች ስብስብ (ሴሚስተር) እና ቪዥዋል አርትስ

ናቸው። የዲዛይን ቴክኖሎጂ የትምህርት ክፍሎች ኮምፒዩተሮች፣ የቤተሰብና የሸማቾች ሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ናቸው። እነዚህ የትምህርት ክፍሎች ለሴሚስተሩ በየሁለት ቀን ይገናኛሉ። የሙሉ ዓመት ባንድ፣ ኦርኬስትራ እና የሕብረት ሙዚቃ በየቀኑ የሚገናኙ ሲሆን እንደ ስነ-ጥበብና የዲዛይን ቴክኖሎጂ የትምህርት ክፍሎች ይቆጠራሉ።

የ6ኛ ክፍል ተማሪዎችም በየሁለት ቀኑ የሚገናኝ የሙሉ ዓመት የዓለም ቋንቋ ትምህርት መውሰድ አለባቸው። የሚሰጡት የዓለም ቋንቋዎች የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ (ASL)፣ አረብኛ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ላቲን፣ ስፓኒሽ፣ እና ስፓኒሽ አቀላጥፈው ለሚናገሩ ናቸው። የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ (ASL) ዓለም አቀፍ የባካሎሪያ (IB) ቋንቋ አለመሆኑንና የዓለም ቋንቋ ለመባል ግን የቨርጂኒያ ዩኒቨርሲቲ እና የማህበረሰብ የመግቢያ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን እባክዎ ያስተውሉ። ከግዛቱ ውጭ ያሉ እና የግል አንዳንድ ድሕረ ሁለተኛ ደረጃ ተቋማት ASL እንደ ዓለም ቋንቋ አይቆጥሩትም።

**7ኛ ክፍል ተጨማሪ ትምህርቶች፦** *ተማሪዎች 6ኛ ክፍል ላይ የዓለም ቋንቋ ትምህርት መግቢያን ስለሚማሩ፣* Jefferson ኢንቴንሲፋይድ ደረጃ I የዓለም ቋንቋ ትምህርት ይሰጣል። እነዚህ ኢንቴንሲፋይድ ኮርሶች ከተለመዱት ደረጃ I የዓለም ቋንቋ ትምህርቶች በተጨማሪ ሆነው በሚገባ ለሚያጠናቅቅ ተማሪም ከፍተኛ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ያስገኛሉ።

**አረብኛ I፣ ኢንቴንሲፋይድ**
**ሙሉ ዓመት (15816)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ፦ ትውውቅ ከአረብኛ ጋር*
አረብኛ I ኢንቴንሲፋይድን የሚወስዱ ተማሪዎች በቅድሚያ ከአረብኛ ጋር የሚያስተዋውቀውን ኮርስ በሚገባ ማጠናቀቅ አለባቸው። የዚህ ኮርስ ግብ ተማሪዎች ከዚህ በፊት በተማሩት የአረብኛ ጥናት መሰረት ደረጃው ከፍ ያለ ብቃት እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። ስርዓተ ትምህርቱ በስፓኒሽ I ውስጥ የተቀመጡትን ሁሉንም ዓላማዎች የሚያሳካ ሲሆን ጠንከር ያለ ይዘትና ተጨማሪ አድቫንስድ አርእስትን ያቀርባል። ይህ ኮርስ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው የቃል ተግባቦት ክህሎቶችን ለማዳበርና የአረብኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሃገራትን ባህላዊ አተያዮችና ልማድ በበለጠ ጥልቀት ለማጥናት ነው።

**ቻይንኛ I፣ ኢንቴንሲፋይድ**
**ሙሉ ዓመት (15616)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ፦ ትውውቅ ከቻይንኛ ጋር*
ቻይንኛ I ኢንቴንሲፋይድን የሚወስዱ ተማሪዎች በቅድሚያ ከቻይንኛ ጋር የሚያስተዋውቀውን ኮርስ በሚገባ ማጠናቀቅ አለባቸው። የዚህ ኮርስ ግብ ተማሪዎች ከዚህ በፊት በተማሩት የቻይንኛ ጥናት መሰረት ደረጃው ከፍ ያለ ብቃት እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። ስርዓተ ትምህርቱ በቻይንኛ I ውስጥ የተቀመጡትን ሁሉንም ዓላማዎች የሚያሳካ ሲሆን ጠንከር ያለ ይዘትና ተጨማሪ አድቫንስድ አርእስትን ያቀርባል። ይህ ኮርስ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው የቃል ተግባቦት ክህሎቶችን ለማዳበርና የቻይናን ባህላዊ አተያዮችና ልማድ በበለጠ ጥልቀት ለማጥናት ነው።

**ፈረንሳይኛ I፣ ኢንቴንሲፋይድ**
**ሙሉ ዓመት (15116)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ፦ ትውውቅ ከፈረንሳይኛ ጋር*
ፈረንሳይኛ I ኢንቴንሲፋይድን የሚወስዱ ተማሪዎች በቅድሚያ ከፈረንሳይኛ ጋር የሚያስተዋውቀውን ኮርስ በሚገባ ማጠናቀቅ አለባቸው። የዚህ ኮርስ ግብ ተማሪዎች ከዚህ በፊት በተማሩት የፈረንሳይኛ ጥናት መሰረት ደረጃው ከፍ ያለ ብቃት እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። ስርዓተ ትምህርቱ በፈረንሳይኛ I ውስጥ የተቀመጡትን ሁሉንም ዓላማዎች የሚያሳካ ሲሆን ጠንከር ያለ ይዘትና ተጨማሪ አድቫንስድ አርእስትን ያቀርባል። ይህ ኮርስ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው የቃል ተግባቦት ክህሎቶችን ለማዳበርና የፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሃገራትን ባህላዊ አተያዮችና ልማድ በበለጠ ጥልቀት ለማጥናት ነው።

**ላቲን I፣ ኢንቴንሲፋይድ**
**ሙሉ ዓመት (15316)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ፦ ትውውቅ ከላቲን ጋር*
ላቲን I ኢንቴንሲፋይድን የሚወስዱ ተማሪዎች በቅድሚያ ከላቲን ጋር የሚያስተዋውቀውን ኮርስ በሚገባ ማጠናቀቅ አለባቸው። የዚህ ኮርስ ግብ ተማሪዎች ከዚህ በፊት በተማሩት የላቲን ጥናት መሰረት ደረጃው ከፍ ያለ ብቃት እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። ስርዓተ ትምህርቱ በላቲን I ውስጥ የተቀመጡትን ሁሉንም ዓላማዎች የሚያሳካ ሲሆን ጠንከር ያለ ይዘትና ተጨማሪ አድቫንስድ አርእስትን ያቀርባል።

**ስፓኒሽ I፣ ኢንቴንሲፋይድ**
**ሙሉ ዓመት (15516)**
*በቅድሚያ የሚወሰድ፦ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚሰጥ የውጭ ቋንቋ (FLES) እና/ወይም መሸጋገሪያ/የስፓኒሽ መግቢያ*
ስፓኒሽ I ኢንቴንሲፋይድ የሚማሩ ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚሰጥ የውጭ ቋንቋ (FLES) ፕሮግራም ውስጥ ቢያንስ ለሶስት ዓመት የተሳተፉና የመሸጋገሪያ ስፓኒሽ/የስፓኒሽ መግቢያ ኮርስን ያጠናቀቁ ናቸው። የዚህ ኮርስ ግብ ተማሪዎች ከዚህ በፊት በተማሩት የስፓኒሽ ጥናት መሰረት ደረጃው ከፍ ያለ ብቃት እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። ስርዓተ ትምህርቱ በስፓኒሽ I ውስጥ የተቀመጡትን ሁሉንም ዓላማዎች የሚያሳካ ሲሆን ጠንከር ያለ ይዘትና ተጨማሪ አድቫንስድ አርእስትን ያቀርባል። ይህ ኮርስ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው የቃል ተግባቦት ክህሎቶችን ለማዳበርና የስፓኒሽ ቋንቋ ተናጋሪ ሃገራትን ባህላዊ አተያዮችና ልማድ በበለጠ ጥልቀት ለማጥናት ነው።

## KENMORE መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

### የጥበባት እና የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ላይ ያተኮረ ፕሮግራም

Kenmore መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የጥበባትና የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ላይ ያተኮረ ት/ቤት በመሆን 24ኛ ዓመቱን ሊይዝ ነው። የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ስርዓተ ትምህርት የሚሰጠው በጥበባትና በኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አማካይነት ነው። የ Kenmore ተማሪዎች ጥያቄ ይጠይቃሉ፣ ትስስር ይፈጥራሉ፣ ይፈጥራሉ፣ እንደዚሁም መልእክት ያስተላልፋሉ። በትምህርት ቀን የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን፣ ቪዥዋል አርት፣ ድራማ፣ ሙዚቃና ውዝዋዜን የሚያቀናጁ የመማር ተግባራት ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ። በመላው አርሊንግተን ውስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች ወደ Kenmore ለመግባት ማመልከት ይችላሉ። ከመኖሪያ አካባቢ የአቴንዳንስ ዞን ውጭ ለሚኖሩ ተማሪዎች የአውቶብስ ትራንስፖርት ይቀርባል።

የት/ቤቱ የጥበብና ቴክኖሎጂ ትኩረት ለተማሪዎች አማራጭ የመማሪያ መንገዶችን ያቀርባል። ይህ አቀራረብ ደግሞ በ Howard Gardner የብዙሃን አስተውሎቶች ሕልዮት ላይ የተመሰረተ ሲሆን ተማሪዎች ስምንት አስተውሎቶችን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፦ ሙዚቃዊ፣ ቪዥዋል፣ ቃላዊ፣ አመክንዮአዊ፣ ስነ-ውበታዊ፣ የእርስ በርስ፣ ከሌላ ሰው ጋር የሚኖር ግንኙነትና አካባቢያዊ። ተማሪዎች በጥልቀት እንዲያስቡና በመማሪያ ክፍል ትምህርት አማካይነት በትብብር እንዲሰሩ ይሞገታሉ። የመማር ሒደቱ ንቁና አሳታፊ። ማህበራዊና ስሜታዊ ዕድገት በአዎንታዊ ባህርይ እርምጃዎችና ድጋፎች (PBIS) ማዕቀፍ በኩል የሚደገፍ ሲሆን፣ ማዕቀፉም ከአርሊንግተን የድጋፍ ሲስተም (ATSS) ሞዴል ጋር የተጣጣመ ነው። አካዳሚያዊ እርምጃ በተለዋዋጭ የመምህር አማካሪ ቡድኖችና ተጨማሪ የምርጫ ትምህርቶችና ድሕረ ት/ቤት ድጋፍ ይታገዛል። Kenmore ዘወትር ማክሰኞና ሐሙስ በሚሰጠው የድሕረ ት/ቤት አክት II ፕሮግራም አማካይነት በምርጫ የሚወሰዱ ኮርሶችን ያቀርባል።

ት/ቤቱ ጥበብን የማገዝ ልማድ ያለው ሲሆን ከ Kennedy Center for the Performing Arts ጋር ዘላቂ ግንኙነት አለው። Kenmore ለቴአትር ጥበብ፣ የሙዚቀኞች ስብስብ፣ ኦርኬስትራ እና የባንድ ፕሮግራሞች ዓመቱን ሙሉ የተለያዩ ዝግጅቶችን ያቀርባል። የ Kenmore ተማሪዎች የዳንስ አካላዊ ትምህርትንም የሚወስዱ ሲሆን በዚህም ውስጥ ለማህበረሰቡ የሚቀርቡ ዝግጅቶች አሉበት። መምህራን ጥበብን ወደ ትምህርት ይዘታቸው ለማካተት የሙያዊ ማጎልበቻ ስልጠና ይሰጣቸዋል። ታብሎ፣ የአንባቢያን ቴአትር፣ ቪዥዋል አርትና ሌሎች ቴክኒኮች ዓመቱን በሙሉ በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ይካተታሉ።

ጥበባዊ የቴክኖሎጂ ትግበራ የት/ቤቱ የትምህርት አሰራር ዋና መሰረት ነው። ተማሪዎች iPads፣ SMART ቦርዶች፣ አሳታፊ የምላሽ መስጫ ሲስተሞች፣ የቴሌቪዥን ስቱዲዮ እና መማርን የሚያግዙ የተለያዩ የሶፍትዌር መተግበሪያዎችን ማግኘት ይችላሉ። የ Kenmore ተማሪዎች ሮቦቲክስና የዲዛይን አስተሳሰብ ትምህርቶችን በአማራጭነት የመውሰድ እድል አላቸው። እነዚህ ኮርሶች የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ ጥበብና ሒሳብ (STEAM) ውህደትን ይደግፋሉ። ተማሪዎች ተከታታይ STEAM ነክ ኮርሶችና ተሞክሮዎችን በሚገባ ማጠናቀቃቸውን ለማረጋገጥ በሚዘጋጅ የማረጋገጫ ፕሮግራም ውስጥ ለማሳተፍ ሊመርጡ ይችላሉ። ት/ቤቱ ለብዙ አገልግሎት የሚውል የማምረቻ ላብራቶሪ (STEAM ክፍል) እንደዚሁም በቴክኖሎጂ የጎለበቱ የመማሪያ ክፍሎች አሉት። ሁሉም የመማሪያ ክፍሎች የ SMART ቦርዶች አላቸው። አንድ መማሪያ ክፍል ከአንድ በላይ የ SMART ቦርዶች የሚኖሩት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ አገናኝ ግድግዳ አለው።

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤትን ሞዴል በመከተል፣ ተማሪዎች ለመሰረታዊ ክፍሎች በክፍል ደረጃ ቡድኖች ይከፋፈላሉ። ተማሪዎች አምስት ወይም ስድስት መምህራን ባሉበት ምድብ ውስጥ የሚመደቡ ሲሆን እነርሱም በቡድን ሆነው በመስራት በቡድናቸው ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ፈታኝና ደጋፊ የአካዳሚክ ተሞክሮ እንዲያገኙ ያደርጋሉ። የፋኩልቲና የመ/ቤት ሰራተኞች ጥበብና ቴክኖሎጂን ለማቀናጀት በሞያዊ ዕድገት ማጎልበቻ ላይ በመደበኛነት ይሳተፋሉ። በተጨማሪም፣ መምህራን በትብብር በሚሰሩ የትምህርት ቡድኖች ውስጥ በመደበኛነት እየተገናኙ የሁሉም ተማሪዎች ፍላጎት መሟላቱን ለማረጋገጥ የተማሪውን አካዳሚክ እመርታ ይከታተላሉ።

**<u>6ኛ ክፍል</u>**

**የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት**
**የ6ኛ ክፍል የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ዳንስ 6 ሙሉ ዓመት (17111)**
ሁሉም የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፋሉ። የዚህ ኮርስ የዳንስ ክፍል ተማሪዎች ለዳንስ አጽንኦት በመስጠት የቨርጂኒያን የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ስታንዳርዶችን እንዲማሩ ያስችላቸዋል። የጤና ትምህርት ፕሮግራም አጽንኦት የሚሰጠው ተማሪዎች ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ለማሳካት ምን ማወቅ፣ መገንዘብና ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ነው። ከጥናት መስኮች መካከል ስሜታዊ፣ አእምሯዊ፣ ማሕበራዊ፣ እና የአካባቢ ጤና፣ ደህንነትና የአጣዳፊ ሁኔታ ዝግጁነት፣ ግንኙነቶች፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነትና በሽታ መከላከልና የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ይገኙበታል።

በ6ኛ ክፍል መሰረታዊ የጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ከተቀመጡት ዓላማዎች በተጨማሪ፣ ተማሪዎች፦
- የዳንስን አላባውያን ተረድተው ተግባራዊ ያደርጋሉ።
- የባሌ፣ የጃዝ፣ የዘመናዊ ዳንስና የሂፕ ሆፕ ዳንስን መሰረታዊ መነሻ ተገንዝበው በተግባር ያሳያሉ።
- ባህላዊ ዳንሶችን ተገንዝበው በተግባር ያሳያሉ።

**የስነ ጥበብ ትምህርት**
**በመሳሪያ ብቻ የቀነባበረ ሙዚቃ - ጀማሪ ፒያኖ**
**ሴሚስተር (19252)**

የዚህ ሴሚስተር ኮርስ የተዘጋጀው ተማሪዎች መሰረታዊ የፒያኖ ክህሎት እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። ተማሪዎች የጀማሪ ደረጃ SOL ዝግጅት የሙዚቃ ስታንዳርዶችን የሚሸፍኑ ሲሆን ጥቂቶቹን የምርመራ ስታንዳርዶችም ያካትታሉ። ተማሪዎች ፒያኖ ወይም ኪቦርድ እንዲገዙ አይገደዱም። ት/ቤቱ ኤሌክትሮኒክ ኪቦርዶችን የሚያቀርብ ሲሆን ኪቦርዱም ት/ቤት ውስጥ የሚቀመጥ ነው።

ተማሪዎች፦
- መሰረታዊ የፒያኖ ክህሎቶችን ይማራሉ።
- ቀላል ዜማዎችና ቅኝቶችን ማንበብና መጫወት ይችላሉ።
- ስኬሎችን መጫወትና የሙዚቃ ምልክቶችን ማንበብን ይማራሉ።
- የተለያዩ ቅኝታዊ ፓተርኖችን ለይቶ ማወቅና መተግበርን ይማራሉ።
- መሰረታዊ የፔዳል አጠቃቀም ቴክኒክን ይማራሉ።

**SHOWTIME፣ ሙሉ ዓመት (11402)**
ShowTime ለአጠቃላዩ የትምህርት ዘመን በየቀኑ ይገናኛል። በተለይ የተቀረጸው የመረጡት ፍላጎታቸው ጥበብ ውስጥ መሆኑን አስቀድመው ላወቁ ተማሪዎች ነው። ዓመቱን በሙሉ ከድምጻዊያን ስብስብና ድራማ ጋር ተጣምሮ የሚሰጠው ይህ ኮርስ ተማሪዎች ከጥበብ ጋር የተቀናጀ ተሞክሮ እንዲኖራቸው ፕሮፌሽናል ፕሮዳክሽን ያመቻቻል። በእያንዳንዱ ሴሚስተር፣ የ ShowTime ተማሪዎች ስራዎቻቸው ቢያንስ በአንድ ዝግጅት ላይ ለእይታ ይቀርቡላቸዋል።

ShowTime ለቡድን ስራ አጽንኦት በመስጠት የሚሰጥ ትምህርት ነው። ዓመቱን በሙሉ፣ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የዲስፒሊን መስክ የክህሎት ደረጃቸውን ለማሳደግ የሚሰሩ ሲሆን፣ በተመሳሳይም በቡድን ጥረት አቀማመጥ ውስጥ የተማሪዎችን የምቾት ደረጃ ያሳድጋሉ።

**7ኛ ክፍል**

**የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት**

**የ7ኛ ክፍል የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ዳንስ 7 ሙሉ ዓመት (17121)**
ሁሉም የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፋሉ። የዚህ ኮርስ የዳንስ ክፍል ተማሪዎች ለዳንስ አጽንኦት በመስጠት የቨርጂኒያን የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ስታንዳርዶችን እንዲማሩ ያስችላቸዋል። የጤና ትምህርት ፕሮግራም አጽንኦት የሚሰጠው ተማሪዎች ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ለማሳካት ምን ማወቅ፣ መገንዘብና ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ነው። ከጥናት መስኮች መካከል ስሜታዊ፣ አእምሯዊ፣ ማሕበራዊ እና የአካባቢ ጤና፣ ደህንነትና የአጣዳፊ ሁኔታ ዝግጁነት፣ ግንኙነቶች፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነትና በሽታ መከላከልና የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ይገኙበታል።

በ7ኛ ክፍል መሰረታዊ የጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ከተቀመጡት ዓላማዎች በተጨማሪ፣ ተማሪዎች፡-

- የባሌ፣ የጃዝ፣ የዘመናዊ ዳንስና የሂፕ ሆፕ ዳንስን መሰረታዊ መነሻ ተገንዝበው በተግባር ያሳያሉ።
- በተመልካች ፊት የዳንስ ቅደም ተከተሎችን ያቀርባሉ።
- ከሙዚቃ ጋር ቅኝትን ጠብቀው መጫወታቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- የባህላዊ ዳንሶችን መነሻዎች ይገነዘባሉ።

**የስነ ጥበብ ትምህርት**

**በመሳሪያ ብቻ የቀነባበረ ሙዚቃ - ጀማሪ ፒያኖ ሴሚስተር (19252)**
የዚህ ሴሚስተር ኮርስ የተዘጋጀው ተማሪዎች መሰረታዊ የፒያኖ ክህሎት እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። ተማሪዎች የጀማሪ ደረጃ SOL ዝግጅት የሙዚቃ ስታንዳርዶችን የሚሸፍኑ ሲሆን ጥቂቶቹን የምርመራ ስታንዳርዶችም ያካትታሉ። ተማሪዎች ፒያኖ ወይም ኪቦርድ እንዲገዙ አይገደዱም። ት/ቤቱ ኤሌክትሮኒክ ኪቦርዶችን የሚያቀርብ ሲሆን ኪቦርዱም ት/ቤት ውስጥ የሚቀመጥ ነው።
*ተማሪዎች፡-*

- *መሰረታዊ የፒያኖ ክህሎቶችን ይማራሉ።*
- *ቀላል ዜማዎችና ቅኝቶችን ማንበብና መጫወት ይችላሉ።*
- *ስኬሎችን መጫወትና የሙዚቃ ምልክቶችን ማንበብን ይማራሉ።*
- *የተለያዩ ቅኝታዊ ፓተርኖችን ለይቶ ማወቅና መተግበርን ይማራሉ።*
- *መሰረታዊ የፔዳል አጠቃቀም ቴክኒክን ይማራሉ።*

**ቢዝነስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ**

**መልቲሚድያ ቴክኖሎጂ I ሴሚስተር (16606)**
*ተማሪዎች መልቲሚድያ እና የዴስክቶፕ ሕትመት ፕረዘንቴሽኖች በድምፅ፣ ግራፊክስ እና ዲጂታል ቪድዮ በማካተት ለመሰረታዊ ትምህርቶቻቸው አገልግሎት ማዋልን ይማራሉ።*

*ተማሪዎች፡-*

- Microsoft Office እና Adobe ሶፍትዌር መተግበሪያዎችን በመጠቀም መሰረታዊ የዴስክቶፕ ሕትመት ክህሎቶችን በላቀ ሁኔታ ይማራሉ።
- የኢንተርኔት ክህሎቶችና ቴክኒኮችን ያውቃሉ።
- በኮምፒዩተር ላይ መሰረታዊ የቴክኖሎጂ ክህሎቶችን ይካናሉ
- ፕሮግራሚንግ (ኮድ አሰጣጥ) ምን እንደሆነ ያውቃሉ
  - የታሪክ ቦርዶች (ምን እንደሆኑ፤ ለምን እንደሚያገለግሉ፤ እንዴት እንደተፈጠሩ)
  - ቀላል አኒሜሽንና ቪዥዋል ኢፌክትስ በመፍጠር ፕረዘንቴሽኖችን የሚያጎሉ አኒሜትድ ቁልፎች።
- የቪድዮ ካሜራ መጠቀምና የቪድዮ ፕረዘንቴሽን ማዘጋጀት ይችላሉ።
- Microsoft Movie Maker መጠቀምን ይማራሉ
  - የመሳያና ቀለም ቅብ መሳሪያዎችን በመጠቀም መልቲሚድያ ፕረዘንቴሽን ያዘጋጃሉ
- ዲጂታል ካሜራ በመጠቀም በ Adobe Creative Cloud አማካይነት ለፕረዘንቴሽን የሚሆኑ ፎቶዎች ማንሳትና ማስተካከል ይችላሉ።
- ስካነር በመጠቀም ስካን የተደረጉ ምስሎችን ወደ ፕረዘንቴሽኖች ያክላሉ።

**መልቲሚድያ ቴክኖሎጂ II ሴሚስተር (16609)**
*ተማሪዎች፡-*

- HTML እና የተለያዩ የድረ ገጽ መፍጠሪያ ሶፍትዌሮችና የኢንተርኔት ጣቢያዎችን በመጠቀም ድረ ገጾችን ዲዛይን ማድረግና ማዘጋጀት ይችላሉ።
- ወደ ሌሎች ገጾች፣ ጣቢያዎች፣ እና ሶፍትዌሮች (PowerPoint፣ Excel፣ Word፣ ወዘተ…) የሚያገናኙ ማስፈንጠሪያዎችን ይፈጥራሉ
- በመልቲሚድያ እና ዴስክቶፕ ሕትመት መስኮች ላይ የስራ አማራጮችን ያስሳሉ።

**የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት**

**በሕዝብ ፊት ንግግር ማድረግ - ሴሚስተር (11301)**
ተማሪዎች በሕዝብ ፊት ንግግር ለማድረግ መሰናዶ፣ ትግበራና አፈጻጸምን ክፍሎች በሙሉ የሚተገብሩ ሲሆን በዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይካተታሉ።

- ንግግሮችን በማፈላለግ፣ በማደራጀትና በዝርዝር ያስቀምጣሉ።
- አስቀድሞ ያልተዘጋጀ እና በማስታወሻ የተደገፉ ንግግሮችን የማድረጊያ ቴክኒኮችን ይፈጥራሉ።
- ከተዘረዘሩትና ከተዘጋጁት ጽሑፎች በመነሳት ንግግር ያደርጋሉ።
- እጅግ ውጤታማ የሆኑ የተግባቦት ቴክኒኮችን ለምሳሌ ለዛ፣ ጥቅስ፣ ቀልድና በግራፍ የታገዘ መረጃ ቴክኒኮችን ያዘጋጃሉ።
- ለውጤታማ ንግግር የሚሆኑ የአነጋገር ክህሎቶችን ይማራሉ።

**የቴክኖሎጂ ትምህርት**

**STEAM ፋውንዴሽንስ፣ ሴሚስተር (18482)**

STEAM ፋውንዴሽንስ አንድ ሴሚስተር የሚፈጁ ኮርሶች ሲሆኑ አምስት ዲስፕሊኖች (ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ ጥበብና ሒሳብ) የተጨባጩ ዓለም መተግበሪያዎች ባሏቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ ይዋሃዳሉ። ተማሪዎች በውድድራዊና ትብብራዊ ተግባራት አማካይነት ችግሮችን መፍታትን ይማራሉ። የሒሳብና የሳይንስ ክህሎቶች ከእነዚህ ተግባራት ጋር ተሳስረው በትምህርትነት ይሰጣሉ። ተማሪዎች የኢንጂነሪንግ ዲዛይን፣ እና ሳይንሳዊ የአጠያየቅ ዘዴን የሚማሩ ሲሆን የሚከተሉትን እንዲገምቱ፣ ዲዛይን እንዲያደርጉና እንዲገነቡም ይፈተናሉ፦ መዋቅሮች፣ የትራንስፖርት ሲስተሞች፣ የሃይልና ኢነርጂ ሲስተሞችና በቴክኖሎጂ ውድድሮች ውስጥ መወዳደር። የስነ-ውበት እንደዚሁም የቅርጽና ተግባራት ስምረት አስፈላጊነቱ ይዳሰሳል። በኮርሱ አጠቃላይ ቆይታ፣ ተማሪዎች ፈተና ይቀርብላቸዋል፣ ተግዳሮቱን ለማለፍ የሚያስፈልግ የ STEAM ይዘትን ይማራሉ፣ መፍትሔ/ዲዛይን ይፈጥራሉ፣ ዲዛይኑን ፈትሸው፣ በዲዛይናቸው/መፍትሔያቸው ላይ አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ያደርጋሉ።

ተማሪዎች በሚከተሉት አራት መስኮች ላይ መሰረታዊ የአተገባበር ግንዛቤን ያዳብራሉ፦
የተመራ ጥያቄ፣ ጥበብና ዲዛይን፣ የቴክኖሎጂ ምርታማነት፣ እና በመሰረታዊ ትምህርት ውስጥ የተማሩትን ኢንጂነሪንግ መተግበር። እነዚህ መስኮች በትምህርት መልክ የሚሰጡት አምስቱን የ STEAM መስኮች (ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ ጥበብና ሒሳብ) እና ችግር ተኮር የማስተማር ሒደት ከአውድ ውስጥ በማስገባት ነው።

## 8ኛ ክፍል

### የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት

**የ8ኛ ክፍል የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ዳንስ 8 ሙሉ ዓመት (17205)**

ሁሉም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፋሉ። የዚህ ኮርስ የዳንስ ክፍል ተማሪዎች ለዳንስ አጽንኦት በመስጠት የቨርጂኒያን የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ስታንዳርዶችን እንዲማሩ ያስችላቸዋል። የጤና ትምህርት ፕሮግራም አጽንኦት የሚሰጠው ተማሪዎች ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ለማሳካት ምን ማወቅ፣ መገንዘብና ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ነው። ከጥናት መስኮች መካከል ስሜታዊ፣ አእምሯዊ፣ ማሕበራዊ፣ እና የአካባቢ ጤና፣ ደህንነትና የአጣዳፊ ሁኔታ ዝግጁነት፣ ግንኙነቶች፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነትና በሽታ መከላከልና የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ይገኙበታል።

በ8ኛ ክፍል መሰረታዊ የጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ከተቀመጡት ዓላማዎች በተጨማሪ፣ ተማሪዎች፦

- የዳንስን አላባውያን ተጠቅመው አጭር የዳንስ ቅደም ተከተል ኮሪዮግራፊ ማዘጋጀት ይችላሉ።
- የባሌ፣ የጃዝ፣ የዘመናዊ ዳንስና የሂፕ ሆፕ ዳንስን መሰረታዊ መነሻ ተገንዝበው በተግባር ያሳያሉ።
- በተመልካች ፊት የዳንስ ቅደም ተከተሎችን ያቀርባሉ።
- ከሙዚቃ ጋር ቅኝትን ጠብቀው መጫወታቸውን በተግባር ያሳያሉ።
- የባህላዊ የዳንስ ቅደም ተከተሎችን ያሳያሉ።

### የስነ ጥበብ ትምህርት

**በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃ**

**ጀማሪ ፒያኖ - ሴሚስተር (19252)**

የዚህ ሴሚስተር ኮርስ የተዘጋጀው ተማሪዎች መሰረታዊ የፒያኖ ክህሎት እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። ተማሪዎች የጀማሪ ደረጃ SOL ዝግጅት የሙዚቃ ስታንዳርዶችን የሚሸፍኑ ሲሆን ጥቂቶቹን የምርመራ ስታንዳርዶችም ያካትታሉ። ተማሪዎች ፒያኖ ወይም ኪቦርድ እንዲገዙ አይገደዱም። ት/ቤቱ ኤሌክትሮኒክ ኪቦርዶችን የሚያቀርብ ሲሆን ኪቦርዱም ት/ቤት ውስጥ የሚቀመጥ ነው።

*ተማሪዎች፦*

- *መሰረታዊ የፒያኖ ክህሎቶችን ይማራሉ።*
- *ቀላል ዜማዎችና ቅኝቶችን ማንበብና መጫወት ይችላሉ።*
- *ስኬሎችን መጫወትና የሙዚቃ ምልክቶችን ማንበብን ይማራሉ።*
- *የተለያዩ ቅኝታዊ ፓተርኖችን ለይቶ ማወቅና መተግበርን ይማራሉ።*
- *መሰረታዊ የፔዳል አጠቃቀም ቴክኒክን ይማራሉ።*

**ቪዥዋል አርት Art III፣ ሙሉ ዓመት (19118)**

ይህ ኮርስ የተዘጋጀው ቪዥዋል አርትን ለማጥናት ቁርጠኛ ለሆነና ከፍተኛ ተነሳሽነት ላለው የአርት ተማሪ ነው። ተማሪዎች በተለያዩ ባለ ሁለትና ባለ ሶስት አቅጣጫ ተሞክሮዎች ውስጥ በመሳተፍ በቪዥዋል አርትስ I እና ቪዥዋል አርትስ II ሲማሩ ያገኟቸውን ክህሎቶች ማዳበራቸውን ይቀጥላሉ። የአርት ኮምፒዩተር ላብራቶሪ ለፈጠራዊ ሒደቱ አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። ለአተያይና ለገለጻ ልዩ አጽንኦት ይሰጠዋል። ስራዎቻቸው፣ ዓላማዎቻቸውና ሃሳቦቻቸው ለተማሪዎች የተሰጡትን የዲዛይን ችግሮች የሚቀርቡ ወይም የሚያሰፉ አርቲስቶችን በማጥናት የጥበብ ታሪክ ይፈተሻል። ተማሪዎች ሃሳቦቻቸውን የሚመዘግቡበት የንድፍ ደብተር ይይዛሉ። በቪዥዋል አርትስ III ውስጥ የሚሰጡ የስኬች አሳይመንቶች ፈጠራዊ አስተሳሰብን ለማነሳሳትና የመስመር ክብደትና ዋጋን ጨምሮ ጥሩ የአሳሳል ቴክኒኮችን መጠቀምንም ያካትታል። ተማሪዎች ፖርትፎሊዮዋቸውን መገንባትንም ይቀጥላሉ።

*ተማሪዎች፦*

- የጥበብ አላባውያን ውጤቶችና መርሆዎችን ይተነትናሉ።
- ተገቢውን የጥበብ መዝገበ ቃላት በመጠቀም የግል ስራንና የሌሎችን ስራ በቃልና በጽሑፍ መተቸት ይችላሉ።
- የጥበብ ስራዎችን የሚመለከቱ ትርጉም ያላቸው ጥያቄዎችን በምልከታዎችና ትርጉሞች ላይ ተመስርተው ማዘጋጀትና መመለስ ይችላሉ።
- በሰርቶ ማሳያ አማካይነት መረጃና ሃሳቦችን ያስተላልፋሉ።
- የጥበብ አላባውያንና የዲዛይን መርሆዎችን ባለ ሁለት አቅጣጫና ባለ ሶስት አቅጣጫ የጥበብ ስራዎች ላይ ይተገብራሉ።
- ለተወሰኑ መደበኛ የቀለም ግንኙነቶች አጽንኦት የሚሰጡ የጥበብ ስራዎችን ይፈጥራሉ።
- የተለያዩ መሪ ቃላትና ሒደቶችን ተጠቅመው ባለ ሶስት አቅጣጫ የጥበብ ስራዎችን ይፈጥራሉ።
- በባለ ሁለት አቅጣጫ ስዕል ውስጥ ጥልቀትን ለማሳየት አተያይን ይጠቀማሉ።
- የጥበብ ፖርትፎሊዮ ማዘጋጀትና ማቆየት ይችላሉ።
- በቋሚነት በት/ቤት ውስጥ የሚሰቀል የቡድን ፕሮጀክት ላይ ይሰራሉ።

### ቢዝነስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ

**መልቲሚድያ ቴክኖሎጂ I፣ ሴሚስተር (16606)**

ተማሪዎች መልቲሚድያ እና የዴስክቶፕ ሕትመት ፕረዘንቴሽኖች በድምፅ፣ ግራፊክስ እና ዲጂታል ቪድዮ በማካተት ለመሰረታዊ ትምህርቶቻቸው አገልግሎት ማዋልን ይማራሉ።
*ተማሪዎች፦*

- Microsoft Office እና Adobe ሶፍትዌር መተግበሪያዎችን በመጠቀም መሰረታዊ የዴስክቶፕ ሕትመት ክህሎቶችን በላቀ ሁኔታ ይማራሉ።
- የኢንተርኔት ክህሎቶችና ቴክኒኮችን ያውቃሉ።

- በኮምፒዩተር ላይ መሰረታዊ የቴክኖሎጂ ክህሎቶችን ይካናሉ።
- ፕሮግራሚንግ (ኮድ አሰጣጥ) ምን እንደሆነ ያውቃሉ፡-
  - የታሪክ ቦርዶች (ምን እንደሆኑ፤ ለምን እንደሚያገለግሉ፤ እንዴት እንደተፈጠሩ)።
  - ቀላል አኒሜሽንና ቪዥዋል ኢፌክትስ በመፍጠር ፕረዘንቴሽኖችን የሚያጎሉ አኒሜትድ ቁልፎች።
- የቪድዮ ካሜራ መጠቀምና የቪድዮ ፕረዘንቴሽን ማዘጋጀት ይችላሉ።
- Microsoft Movie Maker መጠቀምን ይማራሉ፡-
  - የመሳያና ቀለም ቅብ መሳሪያዎችን በመጠቀም መልቲሚድያ ፕረዘንቴሽን ያዘጋጃሉ።
- ዲጂታል ካሜራ በመጠቀም በ Adobe Creative Cloud አማካይነት ለፕረዘንቴሽን የሚሆኑ ፎቶዎች ማንሳትና ማስተካከል ይችላሉ።
- ስካነር በመጠቀም ስካን የተደረጉ ምስሎችን ወደ ፕረዘንቴሽኖች ያክላሉ።

**መልቲሚድያ ቴክኖሎጂ II፣ ሴሚስተር (16609)**

*ተማሪዎች፡-*

- HTML እና የተለያዩ የድረ ገጽ መፍጠሪያ ሶፍትዌሮችና የኢንተርኔት ጣቢያዎችን በመጠቀም ድረ ገጾችን ዲዛይን ማድረግና ማዘጋጀት ይችላሉ።
- ወደ ሌሎች ገጾች፣ ጣቢያዎች፣ እና ሶፍትዌሮች (PowerPoint፣ Excel፣ Word፣ ወዘተ…) የሚያገናኙ ማስፈንጠሪያዎችን ይፈጥራሉ
- በመልቲሚድያ እና ዴስክቶፕ ሕትመት መስኮች ላይ የስራ አማራጮችን ያስሳሉ።

**እንግሊዝኛ**

**በሕዝብ ፊት ንግግር ማድረግ - ሴሚስተር (11301)**

ተማሪዎች በሕዝብ ፊት ንግግር ለማድረግ መሰናዶ፣ ትግበራና አፈጻጸምን ክፍሎች በሙሉ የሚተገብሩ ሲሆን በዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይካተታሉ፡-

- ንግግሮችን በማፈላለግ፣ በማደራጀትና በዝርዝር ያስቀምጣሉ።
- አስቀድሞ ያልተዘጋጀ እና በማስታወሻ የተደገፉ ንግግሮችን የማድረጊያ ቴክኒኮችን ይፈጥራሉ።
- ከተዘረዘሩትና ከተዘጋጁት ጽሑፎች በመነሳት ንግግር ያደርጋሉ።
- እጅግ ውጤታማ የሆኑ የተግባቦት ቴክኒኮችን ለምሳሌ ለዛ፣ ጥቅስ፣ ቀልድና በግራፍ የታገዘ መረጃ ቴክኒኮችን ያዘጋጃሉ።
- ለውጤታማ ንግግር የሚሆኑ የአነጋገር ክህሎቶችን ይማራሉ።

**የቴክኖሎጂ ትምህርት**

**STEAM አፕሊኬሽንስ፣ ሴሚስተር (18258)**

STEAM አፕሊኬሽንስ አንድ ሴሚስተር የሚፈጅ ኮርስ ሲሆን አምስት ዲስፕሊኖች (ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂሪንግ፣ ጥበብ፣ እና ሒሳብ) የተጨባጩ ዓለም መተግበሪያዎች ባሏቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ ይዋሃዳሉ። በዚህ ኮርስ ውስጥ፣ ተማሪዎች ማህበረሰብ ተኮር ፕሮጄክቶች ወይም ክልላዊና ሃገር አቀፍ ውድድሮችን ራሳቸውን ችለው እንዲያከናውኑ የሚያስችላቸው ቦታ፣ ግብዓት፣ እና እገዛ ከመምህሩ ይቀርብላቸዋል። ተማሪዎች በመሰረታዊ ኮርሶች ውስጥ የተማሩትን የኢንጂነሪንግ ዲዛይን እና ሳይንሳዊ የአጠያየቅ ዘዴን ከውድድር ወይም የማህበረሰብ ፍላጎቶች የሚመነጩ እውነተኛ ችግሮች ላይ ይተገብራሉ። ተማሪዎች እነዚህን ተግዳሮቶች ለማለፍ በሚከተሉት አራት መስኮች ላይ መሰረታዊ የአተገባበር ግንዛቤን ያዳብራሉ፡- የተመራ ጥያቄ፣ ጥበብና ዲዛይን፣ የቴክኖሎጂ ምርታማነትና በመሰረታዊ ትምህርት ውስጥ የተማሩትን ኢንጂነሪንግ መተግበር። ተማሪዎች ተግዳሮታቸውን ለማለፍ የሚያስፈልጓቸውን የሒሳብና የሳይንስ ክህሎቶች ይማራሉ።

**<u>በምርጫ የሚወሰድ የዓለም ቋንቋ</u>**

**<u>የዓለም ቋንቋዎች ማስተዋወቂያ</u>** ኮርሶች የተቀረጹት ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የሚያሰጥ ኮርስ ከመወሰዱ በፊት ለቋንቋው ተጋላጭነትን ለመፍጠር ነው። ይህ ተጋላጭነት በመዳረሻ ቋንቋ መዋቅር ውስጥ መሰረት በማስቀመጥ ተሳታፊ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቂያ መስፈርቶችን ለማሟላት ባገለገለው የተመረጠ ቋንቋ ላይ ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። ለመሳተፍ፣ ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸው ወይም ከዚያ በላይ የሚያነብቡ መሆን አለባቸው። ለተጨማሪ መረጃ፣ የልጅዎን ት/ቤት አማካሪ ያነጋግሩ።

**የ6ኛ ክፍል የዓለም ቋንቋዎች ማስተዋወቂያ ኮርስ የሚያስገኛቸው፡-**
ከዚህ በታች ካሉት አማራጮች ውስጥ አንዱን የሚመርጡ ተማሪዎች ከመረጡት የስራ ቋንቋ ትምህርት ከአንድ የንባብ ሴሚስተር ጋር በአንድ ሴሚስተር ይሳተፋሉ።

**የፈረንሳይኛ ማስተዋወቂያ (15101)**
**የሴሚስተር ኮርስ**
ተማሪዎች መዳረሻ ቋንቋን እንዲያውቁ ተደርገው የሚከተሉትን መሰረታዊ የተግባቦት ክህሎቶች ይማራሉ፡- ስለ ራስ መገንዘብ፣ ጥያቄ መጠየቅና መመለስ፤ በመሰረታዊ ማህበራዊ ተግባቦቶች ውስጥ ይሳተፋሉ፤ ከሰላምታ፣ ቀለማት፣ ቁጥሮችና ምግብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ውስን ሐረጋትና የመልዕክት ሃሳቦች ተገንዝበው ይጠቀማሉ። ይህ ኮርስ የተቀረጸው ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የሚያሰጥ ኮርስ ከመወሰዱ በፊት ለቋንቋው ተጋላጭነትን ለመፍጠር ነው። በመዳረሻ ቋንቋ መዋቅር ውስጥ መሰረት በማስቀመጥ ተሳታፊ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቂያ መስፈርቶችን ለማሟላት ባገለገለው የተመረጠ ቋንቋ ላይ ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።

**የላቲን ማስተዋወቂያ (15301)**
**የሴሚስተር ኮርስ**
ተማሪዎች የሮማውያን ቋንቋና ባሕልን ይተዋወቃሉ። ተማሪዎች ጀማሪ የላቲን ቃላትን ሲማሩ ቋንቋን የተመለከቱ መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች ይቀርባሉ። የላቲን ቃላት ምስረታ ላይ ጠንካራ አጽንኦት ይሰጣል።

**የስፓኒሽ ማስተዋወቂያ (15501)**
**የሴሚስተር ኮርስ**
ተማሪዎች መዳረሻ ቋንቋን እንዲያውቁ ተደርገው የሚከተሉትን መሰረታዊ የተግባቦት ክህሎቶች ይማራሉ፡- ስለ ራስ መገንዘብ፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ እና መመለስ፤ በመሰረታዊ ማህበራዊ ተግባቦቶች ውስጥ ይሳተፋሉ፤ ከሰላምታ፣ ቀለማት፣ ቁጥሮችና ምግብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ውስን ሐረጋትና የመልዕክት ሃሳቦች ተገንዝበው ይጠቀማሉ። ይህ ኮርስ የተቀረጸው ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የሚያሰጥ ኮርስ ከመወሰዱ በፊት ለቋንቋው ተጋላጭነትን ለመፍጠር ነው። በመዳረሻ ቋንቋ መዋቅር ውስጥ መሰረት በማስቀመጥ ተሳታፊ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቂያ መስፈርቶችን ለማሟላት ባገለገለው የተመረጠ ቋንቋ ላይ ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።

## ልዩ ሕዝቦች

### የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች

በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ያሉ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርት አሰጣጥ በፌዴራልና በግዛት ሕጎች መሰረት ይሆናል። በልዩ ትምህርት ውስጥ የሚካተቱት አገልግሎቶች በአካል ጉዳታቸው ምክንያት በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ናቸው። አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራማቸው (IEP) መሰረት ገዳቢነቱ እጅግ ዝቅተኛ በሆነ አካባቢ አገልግሎቶችን ያገኛሉ። አንድ IEP አካል ጉዳተኛ መሆናቸው ለታወቀ ተማሪዎች የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን፣ መስተንግዶዎችን እና/ወይም ማሻሻያዎችና ምደባን በዝርዝር ያስቀምጣል።

### የእንግሊዝኛ ተማሪ (EL) አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች

የእንግሊዝኛ ተማሪ (EL) አገልግሎቶች የሚሰጡት የእንግሊዝኛ ተማሪ መሆናቸው ለተለዩ ተማሪዎች ነው። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማጎልበቻ (ELD) ስርዓተ ትምህርት ከ WIDA የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት መስፈርቶችና የቨርጂኒያ የትምህርት ስታንዳርዶች ጋር የተጣጣመ ነው።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃታቸው (ELP) ደረጃ 1 ወይም ደረጃ 2 የሆኑ ተማሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ባለው የ ESL መምህር ንባብ/ቋንቋ ጥበባትን ያጠናሉ። ተማሪዎች ሳይንስና ማህበራዊ ጥናቶችን የብቃት ማረጋገጫ በተሰጠው የ ESL መምህር ይማራሉ ወይም በጥምር በሚማር መማሪያ ክፍል ውስጥ ይማሩና በአጠቃላይ የትምህርት ምርጫዎችና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ውስጥ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች በዝግጁነታቸው መሰረት የሒሳብ ኮርሶችን እንዲወስዱ ይመከራሉ።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃታቸው (ELP) ደረጃ 3 ወይም ደረጃ 4 የሆኑ ተማሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ባለው የ ESL መምህር ንባብ/ቋንቋ ጥበባትን (ባለ ሁለት ክፍለ ጊዜ) ያጠናሉ። ተማሪዎች ሳይንስና ማህበራዊ ጥናቶችን በጠቅላላ መምህር ይማራሉ ወይም በጥምር በሚማር መማሪያ ክፍል ውስጥ ይማሩና በአጠቃላይ የትምህርት ምርጫዎችና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ውስጥ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች በዝግጁነታቸው መሰረት የሒሳብ ኮርሶችን እንዲወስዱ ይመከራሉ።

የእንግሊዝኛ ተማሪዎች (ELs) መሆናቸው የተለዩ ተማሪዎች በ WIDA ACCESS for ELLs የምዘና ውጤት መሰረት ወደቀጣዩ የብቃት ደረጃ ይሸጋገራሉ። ወደ ቀጣዩ ደረጃ ለሚሸጋገሩ ተማሪዎች እንደ Reading Inventory፣ SOL ነጥቦች፣ የናሙና አጻጻፍ እና/ወይም የመምህር ግብዓት ተጨማሪ አስተያየት ይሰጣል።

ELD 1 እንግሊዝኛ 10786
ELD 2 እንግሊዝኛ 10790
ELD 1 ንባብ 10787
ELD 2 ንባብ 10791
ELD 1 ሳይንስ 10780
ELD 2 ሳይንስ 10781
ELD ሒሳብ (10880)
ELD 1 10789 (በ SOL የታሪክ ኮርስ ላልተመዘገቡ ጀማሪ ደረጃ 1 ተማሪዎች የቀረበ አማራጭ)
ELD 1-2 የዩኤስ ታሪክ፣ ስነ-ዜጋ እና ኢኮኖሚክስ እስከ 1865 10800
ELD 1-2 የዩኤስ ታሪክ፣ ስነ-ዜጋ እና ኢኮኖሚክስ ከ1865 እስካሁን 10801
ELD 3 እንግሊዝኛ 10796
ELD 4 እንግሊዝኛ 10799
ELD 3 ንባብ 10794
ELD 4 ንባብ 10797
ELD 3-4 የዩኤስ ታሪክ፣ ስነ-ዜጋ እና ኢኮኖሚክስ እስከ 1865 10795
ELD 3-4 የዩኤስ ታሪክ፣ ስነ-ዜጋ እና ኢኮኖሚክስ ከ1865 እስካሁን 10798

## ስጦታ ያላቸው አገልግሎቶች

የትብብር ክላስተር ሞዴል ለባለተሰጥኦ አገልግሎቶች የአገልገሎት መስጫ ሞዴል ነው። ባለተሰጥኦ መሆናቸው የተለየ ተማሪዎች በተለዩበት ተሰጥኦ መሰረት ከ5 – 8 አባላት ባሉት ምድብ ውስጥ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት፣ በሳይንስና ማህበራዊ ጥናቶች ውስጥ ተመሳሳይነት በሌላቸው ክፍሎች ይሰባሰባሉ። እያንዳንዱ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለባለተሰጥኦ ተማሪዎች የሙሉ ጊዜ መምህር (RTG) አለው። በትብብራዊ የክላስተር ሞዴል ውስጥ፣ RTG እና የክላስተር መምህራን ዕለታዊ የመለየት ስራን በተለያዩ መንገዶች ያቅዳሉ፦ የአድቫንስድ ተማሪዎች ምርጥ ተሞክሮዎች የመረጃ ጥራዝ ውስጥ የተዘረዘሩትን የስርዓተ ትምህርት ግብዓቶች መተግበር፤ በጥልቅና ፈጠራዊ አስተሳሰብ ማዕቀፍ ላየ የተለዩ ስትራቴጂዎችን በማካተት ለክፍሎችና ትምህርቶች ጥንካሬ፣ ጥልቀትና ውስብስብነትን ማስገኘት፤ የቅድመ ምዘናዎችና ስርዓተ ትምህርት አመዳደብን፣ ተለዋዋጭ የቡድን ምደባ፣ የተማሪ ድምፅና መርጫ፣ ተከታታይ

አሳይመንቶች፣ ችግርና ፕሮጀክት ተኮር ትምህርት፣ ግላዊ ትምህርት፣ ገለልተኛ የጥናት እና/ወይም የምርምር ፕሮጀክቶችን በመጠቀም ትምህርቶችን መለያየት።

ዝግጁነታቸውን ለሚያሳዩ ተማሪዎች በአድቫንስድ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት በሚያሰጡ ኮርሶች አማካይነት ይዘት የሚለይባቸው ተጨማሪ ዕድሎች አሉ። ልምድ ያላቸውን የሒሳብ መምህራን የያዘ ቡድን ለሁሉም ተማሪዎች የሒሳብ ኮርስ ምክረ ሃሳቦችን ይወስናል። ቡድኑ ተማሪዎች ስለይዘት ያላቸውን እውቀት፣ የምክንያት አሰጣጥ ችሎታና ለትምህርት ያላቸው ዝግጁነት ጋር የተያያዙ በርካታ እርምጃዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባል። ይህ ዳታ ከአሁኑ የሒሳብ መምህራቸው ከሚሰጥ የኮርስ ምክረ ሃሳብ ጋር በጣምራ የሚታይ ነው። ባለተሰጥኦ ተብለው የተለዩ ተማሪዎች በስድስተኛ ክፍል ለ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ቅድመ አልጀብራ፣ በሰባተኛ ክፍል ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ቅድመ አልጀብራ፣ ለሰባተኛ ወይም ስምንተኛ ክፍል አልጀብራ ኢንቴሲፋይድ ወይም ለስምንተኛ ክፍል ጂኦሜትሪ ኢንቴንሲፋይድ ትምህርት በፍጥነት እንዲዛወሩ ምክረ ሃሳብ ሊሰጣቸው ይችላል። ሁሉም ተማሪዎች ዝግጁ በሆኑ ጊዜ በፍጥነት መዛወር ይችላሉ።

ባለተሰጥኦና ከፍተኛ ችሎታ እንዳላቸው ለተለዩ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከሚሰጡ ሌሎች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ያላቸው ኮርሶች መካከል የዓለም ጂኦግራፊ፣ ላቲን I እና II፣ ስፓኒሽ I እና II እና ፈረንሳይኛ I እና II እና የኮምፒዩተር ሳይንስ ምርመራ ይገኙበታል። የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በስራ ዘመን ማዕከል ውስጥ ወደ ፍሬሽማን ለመግባት ማመልከት ይችላሉ። ወደ ክልላዊ የትምህርት ዘመን የቨርጂኒያ ገዥ ት/ቤት (Thomas Jefferson የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ አድራሻ Annandale, VA, የሆነና በ Fairfax County Public Schools, VA የሚተዳደር) ለመግባትም ሊያመለክቱ ይችላሉ።

የአርትና የሙዚቃ መምህራን ከተማሪዎች ጋር በቀጥታ በመስራት ለተማሪዎቻቸው አግባብነት ያለው ልዩታን ያካሂዳሉ። መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች በባንድ፣ የሙዚቀኞች ስብስብ፣ እና ኦርኬስትራ መስኮች ላይ ኢንቴንሲፋይድ አማራጮችን ሊወስዱ ይችላሉ።
እያንዳንዱ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የባለተሰጥኦ አገልግሎቶችን መረጃ ለወላጆች የሚሰጥ ሲሆን አገልግሎቶች እንዴት እንደሚተገበሩ እና/ወይም የማጣራትና የሪፈራል ሒደቱ ምን እንደሚመስል መረጃ ይሰጣል።

## የቤተ መጻሕፍት አገልግሎቶች

የት/ቤቱ ቤተ መጻሕፍት በት/ቤቱ ኮሙኒቲ ውስጥ የመማር ማስተማሩ ሒደት ማዕከል ነው። የቤተ መጻሕፍት ባለሙያው ለመማርና ራሱን ለቻለ ንባብ የሚሆኑ የሕትመትና ዲጂታል የመረጃ ምንጮችን በማዘጋጀት የሁሉንም ተማሪዎች አእምሯዊ፣ ስሜታዊ፣ እና ማህበራዊ ዕድገትን ያጎለብታሉ። ተማሪዎች ጥልቅና ፈጠራዊ አስተሳሰብና ተግባቦት እንደዚሁም የመተባበር ክህሎቶችን የሚማሩ ሲሆን ይህም መረጃውን ዕድሜ ልክ በሚገባ እንዲጠቀሙበት ለማስቻል ነው። የቤተ መጻሕፍት ባለሙያው ወቅቱን የጠበቀ የመረጃ ስብስብ የሚይዝ ሲሆን ይህም ስብስብ ከት/ቤትና ከቤት ሆኖ ማየት የሚቻል ነው፤ የሁሉንም ተማሪዎች የስርዓተ-ትምህርት ፍላጎቶች፣ የዕድገት ፍላጎቶችና ማህበራዊ፣ ባህላዊና የብሔር ብዝሃነትን የሚያንጸባርቅ ነው።

የት/ቤት ቤተ መጻሕፍት ሰራተኞች ተማሪዎች መረጃን እንዲያገኙ፣ እንዲገመግሙና በሁሉም የይዘት መስኮች ላይ ከይዘት መስኮች መምህራን ጋር በመተባበር ወደተለያዩ የትምህርት ተሞክሮዎች እንዲያካትቱ አመራር ይሰጣሉ።
ተማሪዎች የሕትመትና ዲጂታል የቤተ መጻሕፍት ማቴሪያሎችን በመጠቀም መረጃ መልሶ ማግኘት፣ ማደራጀት፣ መሰነድ፣ መተንተን፣ መገምገም፣ መዘርዘር፣ እና ማቅረብ ይችላሉ። ተማሪዎች የስነ-ምግባር ደንብና መረጃን በአግባቡ ለመጠቀም ተቀባይነት ያላቸው ፖሊሲዎችን እንዲያከብሩም ይማራሉ። የቤተ መጻሕፍት ባለሙያዎች ከሰራተኞች ጋር በመተባበር የስርዓተ-ትምህርት ክፍሎችና ልዩ ፕሮግራሞችን ይገነባሉ። የት/ቤት ቤተ መጻሕፍት የተማሪዎችን የትምህርት ዕድሎች ለማጎልበት እንዲችሉ ሰፊ ሰዓት ይኖራቸዋል።

ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው የቤተ መጻሕፍቱን ግብዓቶች ከት/ቤትና ከቤት ሆነው የቤተ መጻሕፍቱን ድረ ገጽና በ Canvas ያሉ የ APS የቤተ-መጽሐፍት አገልግሎቶች የመረጃ ምንጮችን በማየት እንዲጠቀሙበት ይበረታታሉ።

## ከስርዓተ-ትምህርቱ ውጭ ያለ የአትሌቲክስ ፕሮግራም

በት/ቤት ውስጥና በት/ቤቶች መካከል የሚካሄዱ የስፖርት ፕሮግራሞች የትምህርት ፕሮግራሙ የማይነጣጠሉ አካላት ናቸው። እነዚህ ፕሮግራሞች የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ፕሮግራም ከፍተኛ ደረጃ ሆነው ያገለግላሉ። ተማሪዎች ዋጋ ያላቸው የት/ቤታቸውና የማህበረሰባቸው አካላት እንደሆኑ እንዲገነዘቡ በማገዝ ለተማሪዎች አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ፍላጎቶች አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

በት/ቤት ውስጥ የሚካሄዱ ውድድሮች ዘወትር ሰኞ፣ ረቡዕ እና ሐሙስ ከ 2:50 p.m. እስከ 4:00 p.m. ድረስ ከትምህርት ሰዓት በኋላ ይካሄዳሉ። ዋና ዓላማው ት/ቤት አቀፍ ተሳትፎ እንዲኖር ማድረግ ነው፤ ስለዚህ፣ ሁሉም ተማሪዎች በተለያዩ የት/ቤት ውስጥ ተግባራት ላይ ለመሳተፍ ብቁ ናቸው። Ultimate ከሌሎች የት/ቤት ውስጥ ተግባራት የተለየ አደረጃጀት ያለው ተግባር ነው። በጾታ ተከፋፍሎ የሚካሄድ ሲሆን በት/ቤቶች መካከልም ውድድር ይኖራል (እያንዳንዱ ት/ቤት አንድ ጊዜ እርስ በርስ ይጋጠማል)

በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል የሚካሄዱ ስፖርቶች ፕሮግራም ተማሪዎች በውሃ ዋና፣ በወንዶችና ሴቶች እግር ኳስ፣ ቴኒስና ቅርጫት ኳስ፣ ነጻ ትግል፣ አልቲሜት እና የትራክና የመስክ ውድድሮችን የያዘ ነው። ለመሳተፍ ወቅታዊ የሆነ የአካል ምርመራ ውጤትና የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የአትሌቲክስ ስምምነት ቅጽ መሙላት ያስፈልጋል።

## የማሕበረ-ስሜታዊ ዕድገት

እያንዳንዱ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የአፍላ ወጣቶችን ማህበራዊና ስሜታዊ ዕድገት የሚያጎለብተው በተወሰኑ ተግባራት፣ በሚሰጡ አገልግሎቶች፣ ትምህርታዊ አሰራሮች፣ እና አደረጃጀት አማካይነት ነው። ግዙፍ ት/ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ማንነት የማይታወቅበትን ዕድል ለመቀነስ ሲባል ተማሪዎች በቡድን

(በክፍል ደረጃዎች፣ በክፍል ደረጃ ወይም በፕሮግራም ደረጃ) ሊመደቡ ይችላሉ። እነዚህ አነስተኛ "ማህበረሰቦች" በተማሪዎች ላይ የያገባኛል ስሜትና የበለጠ በራስ የመተማመን ስሜት የሚፈጥሩ ሲሆን አካዳሚያዊ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ዕድገት እንዲኖራቸው ያስችላሉ። መምህራንም የማስተማሪያ ተግባራቶቻቸውን በሚያቅዱበት ወቅት የአፍላ ወጣቶችን ማህበራዊና ስሜታዊ ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ ያስገባሉ። ተማሪዎች በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ ለመስራት፣ ለመተባበርና ፍላጎቶቻቸውንና ችሎታዎቻቸውን የሚያሳድጉ አሳይመንቶችን ለመምረጥ በርካታ ዕድሎች አሏቸው። ለመካከለኛ ደረጃ ተማሪ እንዲህ ዓይነት ትኩረት መሰጠቱ እያንዳንዱ ተማሪ አካዳሚ ስራውን እየሰራም ቢሆን ስሜታዊና ማህበራዊ ዕድገት እንዲኖረው ያስችለዋል።

## የመምህር አማካሪ ፕሮግራም

እያንዳንዱ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ወደ መምህር አማካሪ (T/A) ቡድን ይመደባል። እነዚህ አነስተኛ የተማሪዎች ቡድኖች በትምህርት ሰዓት በየሳምንቱ ከተመደበላቸው ሰራተኛ ጋር ስብሰባ የሚያደርጉ ሲሆን ሰራተኛውም ከማህበራዊና ስሜታዊ ዕድገትና ከት/ቤት ጋር መላመድና ፍላጎቶቹ ጋር በተያያዙ አርእስት ላይ አብሯቸው ይሰራል። ከሚካተቱ የትምህርት ክፍሎች መካከል ወደ አዲስ ት/ቤት ሲገባ የሚሰጥ ገለጻ (ሎከር እንዴት መክፈት እንደሚቻልና የጂም አድራሻ የት እንደሚገኝ) አዳዲስና የቆዩ ጓደኝነቶች፣ የአጠናን ክህሎቶች፣ የመገለጫ ባህርይ ትምህርትና ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መዘጋጀት ይገኙበታል። በዋነኝነት ደግሞ፣ የመምህር አማካሪ በት/ቤቱ ውስጥ የሚገኝ ጎልማሳ ሰው ሆኖ ተማሪውን/ምክር ተቀባዩን በሚገባ የሚያውቅና ተማሪው ጥያቄ ወይም ችግር ሲኖረው የሚያወያየው ሰው ነው። የመምህር አማካሪ ቡድኖች በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ሰፊ አውድ ውስጥ ለተማሪዎች አነስተኛ ቡድንን እንደ "መነሻ ቤት" ይሰጣሉ።

## የተማሪዎች አገልግሎቶችና ልዩ ትምህርት

የማስተማርና መማር መምሪያ በውስጡ አማካሪዎች፣ የት/ቤት የስነ-ልቡና ባለሙያዎች፣ የት/ቤት ማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች፣ የአቴንዳንስ ስፔሻሊስቶች፣ የፀረ-አደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነት አማካሪዎችና የልዩ ትምህርት አመቻች ሰራተኞች ያሉት ሲሆን እነርሱም የተማሪዎች ድጋፍ ሰጪ፣ አስተባባሪዎች፣ የንግግር/የቋንቋ ፓቶሎጂስቶች፣ የእይታ ስፔሻሊስቶች፣ የጆሮ ስፔሻሊስቶች፣ የአካታችነት አመቻቾችና የስራ ላይና አካላዊ ቴራፒስቶች ይገኙበታል። መምሪያው ከት/ቤት የጤና አገልግሎቶች ጋር የትብብር ግንኙነት ይመሰርታል። የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን ማህበራዊና ስሜታዊ ዕድገት ለመደገፍ ከተለያየ ዲስፒሊን የተውጣጣ ቡድን ሞዴል ጥቅም ላይ ይውላል። አማካሪዎች ተቀማጭነታቸው በት/ቤቶች ውስጥ ሲሆን፣ ሌሎች ሰራተኞች ደግሞ ለእያንዳንዱ ሳምንት ቀሪ ክፍል ወደ ት/ቤቶች ይመደባሉ።

የሚከተሉት ትምህርቶች በተግባራዊ የሕይወት ክህሎቶች ፕሮግራም ውስጥ ይቀርባሉ። የስርዓተ-ትምህርቱ ይዘት በተማሪው ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) እና የቨርጂኒያ አማራጭ የምዘና ፕሮግራምን (VAAP) በሚደግፈው የተጣጣመ የትምህርት ስታንዳርዶች መሰረት ነው። ስርዓት ትምህርቱ በተግባቦት፣ ራስ አገዝ፣ ማህበራዊ ክህሎቶች፣ ቅድመ ሞያዊ ክህሎቶችና ተግባራዊ የአካዳሚክ ክህሎቶችን በመሳሰሉ መስኮች ተግባራዊ የሕይወት ክህሎቶችን ማዳበር ላይ ያተኩራል። የትምህርት አሰጣጡ በት/ቤቱ ውስጥ እና ባጠቃላይ በማህበረሰቡ ውስጥ ባለ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ መሰረት ነው።

**እንግሊዝኛ (10035)**
ይህ ኮርስ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ የተዘጋጀ ፕሮግራም ሲሆን በእያንዳንዱ ተማሪ IEP ውስጥ የተለዩትን ፍላጎቶች ለማሟላት የተቀረጸ ነው። የኮርስ ስራው የሚያተኩረው በአንብቦ መረዳት፣ የቃላት አቀማመጥ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የዓ.ነገር አመሰራረት፣ የአንቀጽ አደረጃጀትና የስነ-ጽሑፍ ጥናትን በአጭር ታሪክ፣ በግጥምና በአጭር ልቦለድ መልክ ማጥናት ላይ ነው። በተማሪው የንባብ ደረጃ መሰረት ማቴሪያሎችና የመማሪያ መጻሕፍት ይመረጣሉ።

**ሒሳብ (10036)**
ይህ ኮርስ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ የተዘጋጀ ፕሮግራም ሲሆን በእያንዳንዱ ተማሪ IEP ውስጥ የተለዩትን ፍላጎቶች ለማሟላት የተቀረጸ ሲሆን ሙሉ ቁጥሮች፣ ክፍልፋዮች፣ ዴሲማሎች፣ ኢንቲጀሮች፣ ጥምርታዎችና ድርሻዎች፣ መቶኛ፣ ልኬትና ተግባራዊ ሒሳብ ላይ ያተኩራል።

**ማህበራዊ ጥናቶች (10039)**
ይህ ኮርስ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ የተዘጋጀ ፕሮግራም ሲሆን በእያንዳንዱ ተማሪ IEP ውስጥ የተለዩትን ፍላጎቶች ለማሟላት የተቀረጸ ነው።

**ሳይንስ (10038)**
ይህ ኮርስ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ የተዘጋጀ ፕሮግራም ሲሆን በእያንዳንዱ ተማሪ IEP ውስጥ የተለዩትን ፍላጎቶች ለማሟላት የተቀረጸ ነው።
**ማንበብ (10014)**
ይህ ኮርስ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ የተዘጋጀ ፕሮግራም ሲሆን በእያንዳንዱ ተማሪ IEP ውስጥ የተለዩትን ፍላጎቶች ለማሟላት የተቀረጸ ነው። የኮርስ ስራው የተዘጋጀው በተማሪው ላይ የሚታዩ ውስን የንባብ ፍላጎቶችን ለማሟላት ነው። በተጨማሪም፣ ሌሎች የመማሪያ ክፍል ማቴሪያሎችን ለመጠቀም አስፈላጊ ለሆኑ የተወሰኑ ክህሎቶች ለመዝናናትና ለመረዳት ማንበብ።

## የቤት ውስጥ ትምህርት

የስነ-አእምሮ ጤና ችግርን ጨምሮ በጤና ችግር ምክንያት ወደ ት/ቤት ለመምጣት ያልቻሉ ተማሪዎች የቤት ውስጥ ትምህርት ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የቤት ውስጥ ትምህርት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በቀጣዩ የ ድረ ገጽ ላይ ይገኛል፦ https://www.apsva.us/special-education/homebound-instruction/ . የማመልከቻው ኮፒዎችን በየትኛውም የ APS ት/ቤት ሊጠየቁ ይችላሉ። ማመልከቻዎች ለተማሪው ት/ቤት

ቀርበው ከታዩ በኋላ ወደ ልዩ ትምህርት ጽ/ቤት ይላካሉ። የቤት ውስጥ ትምህርት እንዲሰጥ ከተፈቀደ በኋላ፣ የሚያስፈልገውን የአገልግሎት ደረጃ ለመወሰን ሲባል የ IEP ቡድን ስብሰባ ይካሄዳል። በሁሉም ሁኔታዎች ለቤት ውስጥ ትምህርት ብቁነት በየዘጠኝ ሳምንቱ ይገመገማል።

## የተማሪዎች ተግባራት

ክበባት፣ የተማሪ መንግስትና ሌሎች ድርጅቶች ተማሪዎች ማህበራዊና ስሜታዊ ዕድገት ይኖራቸው ዘንድ በርካታ ዕድሎች ይፈጥሩላቸዋል። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ቡድኖች የሚገናኙት ከትምህርት ሰዓት በኋላ ነው። ተማሪዎች እንዲሳተፉ ይበረታታሉ፣ እና አባልነት የሚገድብ አይደለም።

## የቤት/ትምህርት ቤት ትብብር እና ግንኙነት

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ አእምሯዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊና አካላዊ ዕድገት እንዲኖረው ሲባል ቤትና ት/ቤት ለተማሪው ጥቅም ሲሉ መተባበር አለባቸው። ለመተባበር ደግሞ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ መምህራንና ሰራተኞች ግንኙነት ማድረግ አለባቸው። መደበኛና ኢ-መደበኛ የሆኑ በርካታ የመገናኛ ዘዴዎች አሉ።

### ለወላጆች/አሳዳጊዎች ሪፖርት ማድረግ

ተማሪዎች በእያንዳንዱ የዘጠኝ ሳምንት የውጤት መስጫ ጊዜ መጨረሻ ላይ ሪፖርት ካርድ የሚሰጣቸው ሲሆን ይህም በሴፕቴምበር ወር ላይ ታትሞ ለወላጆች በሚሰራጨው የጊዜ መርሃ ግብር መሰረት ነው። በእያንዳንዱ አራት የውጤት መስጫ ጊዜያት አጋማሽ ላይ እያንዳንዱ ተማሪ ከመሰረታዊ የመምህራን ቡድን ሪፖርት የሚሰጠው ሲሆን፣ ሪፖርቱም የተማሪውን ወቅታዊ እመርታ የሚያመለክት ነው። በምርጫ የሚወሰዱ/ገላጭ ትምህርት መምህራንም ጊዜያዊ ሪፖርቶችን የሚያወጡ ሲሆን፣ በዚህም አጥጋቢ ያልሆነ ስራ፣ ከበቂ በታች የሆነ ስራን ወይም ከተማሪው የችሎታ ደረጃ እጅግ የወረደ ስራን ያመለክታሉ። ከእነዚህ መደበኛ የሆኑ ለወላጆች ሪፖርት ማድረጊያ ዘዴዎች በተጨማሪ፣ በርካታ ቡድኖችና የተናጠል መምህራን በዜና መዋዕሎች፣ በማስታወሻዎችና በተማሪ ስራ አማካይነት ግንኙነት የሚያደረጉ ሲሆን እነዚህም ወደ ቤት የሚላኩ ናቸው።

### ኮንፈረንሶች

ሁሉም ቤተሰቦች በበልግና በፀደይ ወቅት ተማሪ በማይኖርባቸው ቀናት ከተወካይ መምህራን ጋር በሚካሄድ ኮንፈረንስ ላይ እንዲሳተፉ ይጋበዛሉ። በተጨማሪም፣ አንድ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም መምህር በማንኛውም ወቅት የተማሪው እመርታ ላይ ለመወያየት ኮንፈረንስ እንዲዘጋጅ መጠየቅ ይችላል። ወላጅ/አሳዳጊ በአንድ ተማሪ ላይ ለመወያየት የተማሪው መሰረታዊ ቡድን ጋር ሊገናኝ ይችላል። የወላጅ/አሳዳጊ/መምህር ኮንፈረንሶችን በተደጋጋሚ የሚያዘጋጀው አማካሪው ነው።

### የስልክ ጥሪዎችና ማስታወሻዎች

አንድ ወላጅ/አሳዳጊ (አብዛኛውን የትምህርት ሰዓት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚያጠፋ መምህር) የስልክ መልእክት ሊተው ወይም ምላሽ የሚጠይቅ ማስታወሻ ወይም ኢሜይል ሊልክ ይችላል። መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ማናቸውንም ምርጫቸውን በኮርስ መርሃ-ትምህርታቸው ላይ ይጠቁማሉ። መምህራን በተቻለ ፍጥነት ምላሽ ለመስጠት የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ይደርጋሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች የተማሪውን እመርታ በተመለከተ ጥያቄ ለመጠየቅ በቀጥታ ለአማካሪው ስልክ መደወል ይችላሉ።

### ጉብኝቶችና በጎ-ፈቃደኝነቶች

ወላጆች/አሳዳጊዎች በት/ቤቱ ስራዎች ውስጥ የበለጠ ተሳትፎ በማድረግ የተማሪውን አካባቢ በተለያዩ መንገዶች ለማወቅ ይችላሉ። የወላጆችና መምህራን ማህበር (PTA) እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ወላጆች ፍላጎትና ቁርጠኝነትን የሚያሳዩባቸው ሁለት መንገዶች ናቸው። ተማሪዎች በተለይ የሚደሰቱት ወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው በተማሪዎች ዝግጅቶች፣ የአትሌቲክስ ውድድሮች ወይም የተለዩ ስብሰባዎች ላይ ሲገኙላቸው ነው፣ ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች ግላዊ ድጋፍ በተግባር የሚታይባቸው ናቸው።

## በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ያለ ደረጃውን የጠበቀ ፈተና አሰጣጥ

የቨርጂኒያ የትምህርት ቦርድ የ6ኛ፣ 7ኛና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች የንባብ፣ የሒሳብ፣ የታሪክና ማህበራዊ ሳይንሶችን የትምህርት መለኪያ (SOL) ምዘናዎች እንዲወስዱ ይጠይቃል። የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችም የጽሑፍና የሳይንስ ፈተናን ይወስዳሉ። ለአልጀብራ ወይም ጂኦሜትሪ ወይም የዓለም ጂኦግራፊ የተመዘገቡ ተማሪዎችም በዚያ የትምህርት ዓይነት የ SOL የኮርስ ማጠናቀቂያ ፈተና ይወስዳሉ። የ SOL ፈተናዎች የቨርጂኒያ SOLን ለማሟላት የተዘጋጁ መስፈርት ተኮር ፈተናዎች ናቸው።

ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ዲፕሎማ ለማግኘት ቢያንስ አምስት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ ማጠናቀቂያ (EOC) ፈተናዎችን ማለፍ አለባቸው። ለተጨማሪ መረጃ፣ በዚህ ሰነድ መጨረሻ ላይ የሚገኙትን የመመረቂያ መስፈርቶች ማየትና ከተማሪዎ አማካሪ ጋር መነጋገር አለብዎ።

### የምዘና ውጤቶች

ተማሪዎች የተፈተኗቸው ፈተናዎች ውጤቶች እያንዳንዱ የፈተና መስጫ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ለወላጆች ይላክላቸዋል። የት/ቤቶችና የአርሊንግተን አጠቃላይ ውጤቶች በቀጣዩ የ APS ድረ ገጽ ላይ ይለጠፋሉ፦ www.apsva.us ።

## በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የሚያስገኙ ኮርሶች

አንድ ተማሪ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ያለውን ኮርስ (ለምሳሌ፣ አልጀብራ፣ ጂኦሜትሪ፣ አረብኛ I/II፣ ቻይንኛ I/II፣ ፈረንሳይኛ I/II፣ ላቲን I/II፣ ስፓኒሽ I/II፣ የዓለም ጂኦግራፊ፣ ወይም ኮምፒዩተር ሳይንስ መመርመር) በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ሲወስድ፣ የዚያ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ የሚከተሉት ምርጫዎች አሉት።

- ክሬዲቱ (ከተገኘ) እና ኮርሱ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶች ውስጥ እንዲቆጠርና የኮርሱን የማጠቃለያ ውጤት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ ሲታሰብ በተማሪው አማካይ የፈተና ውጤት (GPA) ውስጥ እንዲካተት ማድረግ።

- ክሬዲቱ (ከተገኘ) እና ኮርሱ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶች ውስጥ እንዳይቆጠርና የኮርሱን የማጠቃለያ ውጤት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ ሲታሰብ በተማሪው አማካይ የፈተና ውጤት (GPA) ውስጥ እንዳይካተት ማድረግ።

ወላጆች ይህን ምርጫ በተመለከተ ማሳወቂያ ከልጃቸው የማጠቃለያ ሪፖርት ካርድ ጋር ይላክላቸዋል። የመከካለኛ ደረጃ ት/ቤቱ ሰራተኞች ኮርሱ እንዳይካተት ከወላጅ የሚቀርብ ጥያቄ በተወሰነ ቀን ላይ ካልደረሳቸው፣ ማንኛውም የተገኘ ክሬዲትና የፈተና ውጤት በተማሪው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መረጃዎች ውስጥ ይካተታል (በቨርጂኒያ የአክሬዲቴሽን ስታንዳርዶች መሰረት)።

አንድ ወላጅ/አሳዳጊ በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የተወሰዱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች የያዙ ኮርሶች የተማሪው የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ክፍል እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከመጨረሻ ትራንስክሪፕታቸው እንዲሰረዙ መጠየቅ ይችላሉ።

## የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አማራጮች

በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ ያሉ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተማሪዎችን አእምሯዊና ማህበራዊ/ስሜታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሁሉን አቀፍ ፕሮግራም ያቀርባሉ። ከአጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በተጨማሪ፣ የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ወላጆች ሊያዩዋቸው የሚወዱ ሌሎች በርካታ አማራጮች አሉት። እነዚህ በአማራጭነት የቀረቡ ፕሮግራሞች መካከል H-B Woodlawn Program፣ የ International Baccalaureate Program፣ the Foundation Program for Academic Excellence እና የ Thomas Jefferson የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ይገኙበታል። STEM Career እና ቴክኒካዊ ኮርሶችም በ Career Center በኩል ለአርሊንግተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤተ ተማሪዎች ይቀርባሉ።

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዓለም አቀፍ ባካሎሪያ ለመቀጠል የሚፈልጉ ተማሪዎች 7ኛ ክፍል እያሉ ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ፣ ቻይንኛ ወይም ላቲን I እና ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ፣ ቻይንኛ ወይም ላቲን II ደግሞ 8ኛ ክፍል እያሉ እንዲወስዱ ይበረታታሉ። 8ኛ ክፍል ላይ ለአልጀብራ I መመዝገብም አለባቸው። ለክረምት ት/ቤቶች የመስተንግዶ አገልግሎቶች ሊመቻቹ ይችላሉ።


የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አማራጮችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የሚገኙትን የማማከር አገልግሎት ጽ/ቤቶች ወይም የማስተማርና መማር መምሪያን ያነጋግሩ።

**የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አማራጮች**

**ማስታወሻ፡- ለእነዚህ አማራጮች በሙሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ይቀርባል።**

| ፕሮግራም | ቦታ | የቅበላ ፖሊሲ |
|---|---|---|
| Arlington Tech | Arlington Career Center | • በአሁኑ ጊዜ ለ8ኛ ወይም 9ኛ ክፍል የተመዘገበ ማንኛውም የ APS ተማሪ በመላው ካውንቲው የሚካሄድ የእጣ አወጣጥ ዕድል ላይ ለመሳተፍ የዝውውር ቅጽ ማቅረብ አለበት።<br>• የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች Arlington Tech ውስጥ ከመመዝገባቸው በፊት በአልጀብራ I የተረጋገጠ ክሬዲት ማግኘት ያለባቸው ሲሆን፣ የ10ኛ ክፍል አመልካቾች ደግሞ በጂኦሜትሪ የተረጋገጠ ክሬዲት ማግኘት አለባቸው።<br>• ስለ ፕሮግራሙ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- Arlington Tech Program |
| Foundation Program for Academic Excellence | Wakefield ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | • በአሁኑ ጊዜ ለ8ኛ የተመዘገበ ማንኛውም የ APS ተማሪ ለመመዝገብ የዝውውር ቅጽ ማቅረብ አለበት።<br>• ስለ ፕሮግራሙና ስለ ዝውውር ሒደቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- Freshman Foundations at Wakefield |
| H-B Woodlawn | H-B Woodlawn | • በአሁኑ ጊዜ ለ8ኛ ክፍል የተመዘገበ ማንኛውም የ APS ተማሪ በመላው ካውንቲው የሚካሄድ የእጣ አወጣጥ ዕድል ላይ ለመሳተፍ የዝውውር ቅጽ ማቅረብ አለበት።<br>• ስለ ፕሮግራሙና ስለ ዝውውር ሒደቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡-<br>• H-B Woodlawn Program |
| International Baccalaureate Program | Washington-Liberty ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | **የ W-L ቅድመ IB በቅድሚያ የሚወሰዱ ትምህርቶች**<br>- ለ8ኛ ክፍል አልጀብራ I ወይም ከዚያ በላይ ወይም ለ9ኛ ክፍል ጂኦሜትሪ ወይም ከዚያ በላይ<br>- ለ8ኛ ክፍል ስፓኒሽ II፣ ፈረንሳይኛ II፣ ቻይንኛ II ወይም ላቲን II ወይም ለ9ኛ ክፍል ስፓኒሽ III፣ ፈረንሳይኛ III፣ ቻይንኛ III ወይም ላቲን III<br>- በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ያገኘው ነጥብ ኤ እና ቢ መሆን አለበት<br>- አጭር ምላሽ ያላቸው ጥያቄዎች<br>• በዋሽንግተን ሊበርቲ አካባቢ የማይኖሩ ተማሪዎች ከ IB ማመልከቻ በተጨማሪ የዝውውር ማመልከቻ ማቅረብ ያስፈልጋቸዋል።<br>• ስለ ፕሮግራሙና ስለ ዝውውር ሒደቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- የ IB ፕሮግራም በዋሽንግተን ሊበርቲ |
| የስፓኒሽ ባለ ሁለት ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም | Wakefield ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | • በት/ቤቱ አካባቢ የሚኖሩ ተማሪዎች፣ በ Gunston የኢመርሽን ፕሮግራሙ ውስጥ የተሳተፉ ተማሪዎችና በስፓኒሽ ትምህርት ተገቢውን ብቃት ያሳዩ ተማሪዎች መመዝገብ ይችላሉ።<br>• በ Wakefield አካባቢ የማይኖሩ ተማሪዎችም የዝውውር ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።<br>• ስለ ፕሮግራሙና ስለ ዝውውር ሒደቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- Spanish Immersion Program at Wakefield |
| Thomas Jefferson የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | Thomas Jefferson High School for Science and Technology፣ ፌርፋክስ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች | • በአሁኑ ጊዜ ለ8ኛ ክፍል ወይም ለአልጀብራ I (ወይም ለበለጠ የሒሳብ ኮርስ) የተመዘገበ ማንኛውም የ APS ተማሪ ለመመዝገብ ማመልከት ይችላል።<br>• ሁሉም ተማሪዎች Thomas Jefferson የመግቢያ ፈተናን መውሰድ አለባቸው<br>• ስለ ፕሮግራሙና ስለ ቅበላ ሒደቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- TJHSST Admissions |


# የሚጠቆሙ የ APS መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሒሳብ ትምህርት መስመሮች




በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ላይ ተጨማሪ "የሒሳብ ስትራቴጂዎች" ኮርሶች ያሉ ሲሆን እነዚህም የክፍል ደረጃ ብቃትን ለማሳካት የሚሰጥ ድጋፍ ተጠቃሚ ለሚሆኑ ተማሪዎች በምርጫ የሚሰጡ ናቸው።

## የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የሒሳብ ኮርስ መስመሮች ከአልጀብራ I ጀምሮ (2020-2021)

*ተማሪዎች ወደነዚህ መስመሮች የሚገቡት በየትኛውም የአልጀብራ I ኮርስ (በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ላይ የሚከሰት) ውስጥ ሲመዘገብ ነው። ተማሪዎች በሚኖራቸው ዝግጁነት መሰረት ሊወስዷቸው የሚችሏቸው የተለያዩ መስመሮችና ኮርሶች አሉ። በቅድሚያ ለሚወሰዱ መስፈርቶች እባክዎ የተወሰኑ የኮርስ መግለጫዎችን ይመልከቱ*




ለተወሰነ IB እና በዚህ ውስጥ ያለተዘረዘሩ የጥምር ምዝገባ ኮርሶችን ለማየት፣ እባክዎ በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚሰጡ ኮርሶችን ማውጫ ይመልከቱ።
ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በአልጀብራ I፣ ጂኦሜትሪ፣ ወይም አልጀብራ II እና የስትራቴጂስ ኮርስ ውስጥ በጥምር መመዝገብ ይችላሉ።
*AFDA በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ብቻ ከአልጀብራ I በኋላ እና ከጂኦሜትሪ በፊት ወይም ከጂኦሜትሪ በኋላ እና ከአልጀብራ II በፊት ሊወሰድ ይችላል።

## የዓለም ቋንቋዎች የጥናት ቅደም ተከተል[1]

### የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ

| 7ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛ ክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | | |
| | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | |
| | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 |
| | | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 |
| | | | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 |

### አረብኛ

| 7ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛ ክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 | |
| | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
| | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 |

### ቻይንኛ

| 7ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛ ክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | የቻይንኛ ቋንቋና ባህል፣ AP | |
| | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | የቻይንኛ ቋንቋና ባህል፣ AP |
| | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 |

### ፈረንሳይኛ

| 7ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛ ክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 ወይም ፈረንሳይኛ ቋንቋና ባህል፣ AP | ፈረንሳይኛ ቋንቋና ባህል፣ AP ወይም አድቫንስድ ስተዲስ በፈረንሳይኛ |
| | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 ወይም የፈረንሳይኛ ቋንቋና ባህል፣ AP |
| | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 |

### ጀርመንኛ

| 7ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛ ክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | |
| | | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 |
| | | | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 |

### ጃፓንኛ

| 7ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛ ክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|

[1] ይህ ቅደም ተከተል ለመደበኛ ፕሮግራሞች ነው። በዓለም አቀፍ ባካሎሪያ የሚቀርቡ ቋንቋዎችን ሙሉ ዝርዝር ለማግኘት፣ እባክዎ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የጥናቶች ፕሮግራምን ተመልከት።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | |
| | | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 |
| | | | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 |

**ላቲን**

| 7ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛ ክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 ወይም ላቲን፣ AP | ላቲን፣ AP ወይም በላቲን አድቫንስድ ስተዲስ |
| | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 ወይም ላቲን፣ AP |
| | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 |

**ስፓኒሽ**

| 7ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛ ክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 ወይም የስፓኒሽ ቋንቋና ባህል፣ AP | የስፓኒሽ ቋንቋና ባህል፣ AP ወይም የስፓኒሽ ስነ-ጽሑፍ፣ AP ወይም አድቫንስድ ስተዲስ በስፓኒሽ |
| | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 ወይም የስፓኒሽ ቋንቋና ባህል፣ AP |
| | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 |

**ስፓኒሽ አቀላጥፈው ለሚናገሩ**

| 7ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛ ክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | የስፓኒሽ ቋንቋና ባህል፣ AP | የስፓኒሽ ስነ-ጽሑፍ፣ AP | አድቫንስድ ስተዲስ በስፓኒሽ |
| | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | የስፓኒሽ ቋንቋና ባህል፣ AP | የስፓኒሽ ስነ-ጽሑፍ፣ AP ወይም አድቫንስድ ስተዲስ በስፓኒሽ |
| | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | የስፓኒሽ ቋንቋና ባህል፣ AP |

ማስታወሻዎች:-

1. ላቲን ለ Wakefield ተማሪ ብቻ። ጀርመንኛ እና ጃፓንኛ የሚሰጡት በሙያ ማእከል ብቻ ነው። ተማሪዎች እነዚህን ትምህርቶች ለመውሰድ ወደ ሙያ ማዕከል ሊሄዱ እና ለቀሩት ትምህርቶች በአካባቢያቸው ወደሚገኝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሊመለሱ ይችላሉ።
2. በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቻይንኛን የሚያስተምረው የ APS መምህር ነው። ከዋሽንግተን ሊበርቲ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በስተቀር፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ቻይንኛ በኦንላይን ትምህርት አቅራቢ በኩል የሚሰጥ ሲሆን የአፍ መፍቻ ቋንቋው ቻይንኛ በሆነ ረዳት ይታገዛል።
3. የ AP ወይም IB ፈተና በአሜሪካ የምልክት ቋንቋ ወይም አረብኛ ውስጥ አይሰጥም።
4. የ AP ፈተና ለአረብኛ አይሰጥም።
5. IB አረብኛ እና ቻይንኛ በዋሽንግተን ሊበርቲ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ይሰጣሉ
6. የ AP ኮርስ በጀርመንኛም ሆነ በጃፓንኛ አይሰጥም።
7. በአንድ ወይም ከአንድ በላይ የውጭ ቋንቋዎች ጠንካራ ብቃትን ያሳዩ የ APS ተማሪዎች በፈተና አማካይነት በክሬዲት በሚገባ በመሳተፍ እስከ 4 ክሬዲቶች (ደረጃ 1-4) ማግኘት ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ www.apsva.us/worldlanguages ይመልከቱ። የተባዙ ክሬዲቶች አይፈቀዱም።

## የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመመረቂያ መስፈርቶች

አንድ ተማሪ ከቨርጂኒያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ለማግኘትና ለመመረቅ የሚያስፈልጉት መስፈርቶች ተማሪው ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ 9ኛ ክፍል ሲገባ ተግባራዊ የነበሩት ናቸው። ተማሪዎች ከቨርጂኒያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲመረቁ ዲፕሎማ ይሰጣቸዋል።
ከ9ኛ ክፍል በታች ያሉ ተማሪዎች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ የሚሰጡትን ኮርሶች በሚገባ ሲያጠናቅቁ ለምረቃ የሚያስፈልጉ መደበኛ መለኪያዎችን ለማሟላት ክሬዲቱ ታሳቢ ይደረጋል። ለእነዚህ ኮርሶች የተረጋገጠ ክሬዲት ለማግኘት ተማሪዎች የቨርጂኒያ የጥራት ደረጃዎችን (.8VAC20-131-110) ማሟላት አለባቸው።
የአካባቢው የት/ቤት ቦርድ በትምህርት ቦርዱ የጸደቁ ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶችን ካላስቀመጠ በስተቀር የሚከተሉት መስፈርቶች ብቻ ናቸው ለዲፕሎማ የሚያስፈልጉት። በትምህርት ቦርዱ የጸደቁና በአካባቢው የት/ቤት ቦርድ የተቀመጡ ተጨማሪ መስፈርቶች በሙሉ የአካባቢው ት/ቤት ቦርድ ለማሻሻል ወይም ለማስቀረት ለቦርዱ ጥያቄ እስከሚያቀርብበት ጊዜ ድረስ ጸንተው ይቆያሉ።

### የመደበኛ ዲፕሎማ መስፈርቶች።

ከ2013 በፊት ጀማሪ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከ2018-19 እና ከዚያ በኋላ ያሉ ዘጠነኛ ክፍሎች ጀምሮ ተማሪዎች የሚያስፈልግ ስታንዳርድና የተረጋገጠ የክሬዲት መለኪያዎችን ማግኘት አለባቸው።
አንድ ተማሪ በመደበኛ ዲፕሎማ ለመመረቅ የሚያስፈልጉና አማራጭ ኮርሶችን በማለፍ ቢያንስ 22 መደበኛ የክሬዲት መለኪያዎችን ማግኘትና የኮርስ ማጠናቀቂያ የ SOL ፈተናዎች ወይም በትምህርት ቦርድ የሚጸድቁ ሌሎች ምዘናዎችን በማለፍ ቢያንስ አምስት የተረጋገጡ ክሬዲቶችን ማግኘት አለባቸው።

በተጨማሪም ተማሪዎች የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡

- የላቀ ምደባን፣ ሆነርስን፣ ዓለም አቀፍ ባካሎሪያ ወይም የሁለት ምዝገባ ኮርስን ማጠናቀቅ፣ የተሟላ ጥራት ያለው ሥራን መሠረት ያደረገ የስራ ላይ ትምህርት ተሞክሮን ማጠናቀቅ፤ ወይም የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ማስረጃ ማግኘት።
- አንድ ቨርቹዋል ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ።
- በድንገተኛ ጊዜ የመጀመሪያ እርዳታ፣ የልብና የደም ሥር ማስታገሻ (CPR) እና ካርዲዮፑሉሙናሪ ሪሰሲቴሽን ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶችን በተግባር ላይ ማዋልን ጨምሮ በራስ-ሰር የውጭ ዲፊብሪላተሮች (AED) አጠቃቀም የሰለጠኑ መሆን።
- በቨርጂኒያ 5 C ውስጥ መሠረታዊ ችሎታዎችን ያገኙ እና ማሳየት፡ ጥልቅ አስተሳሰብ፣ ፈጠራዊ አስተሳሰብ፣ ትብብር፣ ግንኙነት እና ዜግነት።

| የትምህርቱ መስክ | የሚያስፈልግ ክሬዲት መደበኛ መለኪያ | የሚያስፈልግ የተረጋገጠ ክሬዲት |
|---|---|---|
| እንግሊዝኛ (ማንበብና መጻፍ) | 4 | 2 |
| ሒሳብ | 3 | 1 |
| ሳይንስ | 3 | 1 |
| ታሪክ እና ማህበራዊ ሳይንስ | 3 | 1 |
| ጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት | 2 | |
| የዓለም ቋንቋዎች ስነ-ጥበብ ወይም የስራ ዘመንና የቴክኒክ ትምህርት | 2 | |
| ኢኮኖሚክስ እና የግል ፋይናንስ | 1 | |
| በምርጫ የሚወሰዱ | 4 | ይህንን መስፈርት ለማሟላት የሚረዱ ኮርሶች ቢያንስ ሁለት ተከታታይ ተመራጮችን ያካትታሉ። |
| አጠቃላይ | 22 | 5 |

### የአድቫንስድ ጥናቶች ዲፕሎማ መስፈርቶች።

በ2018-19 የትምህርት ዘመንና ከዚያ በኋላ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ተማሪዎች አስፈላጊ ስታንዳርድና የተረጋገጠ የክሬዲት መለኪያ ማግኘት አለበት።
አንድ ተማሪ በአድቫንስድ ጥናቶች ዲፕሎማ ለመመረቅ የሚያስፈልጉና አማራጭ ኮርሶችን በማለፍ ቢያንስ 26 መደበኛ የክሬዲት መለኪያዎችን ማግኘትና የኮርስ ማጠናቀቂያ የ SOL ፈተናዎች ወይም በትምህርት ቦርድ የሚጸድቁ ሌሎች ምዘናዎችን በማለፍ ቢያንስ አምስት የተረጋገጡ ክሬዲቶችን ማግኘት አለባቸው።

በተጨማሪም ተማሪዎች የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡

- የላቀ ምደባን፣ ሆነርስን፣ ዓለም አቀፍ ባካሎሪያ ወይም የሁለት ምዝገባ ኮርስን ማጠናቀቅ፣ የተሟላ ጥራት ያለው ሥራን መሠረት ያደረገ የስራ ላይ ትምህርት ተሞክሮን ማጠናቀቅ፤ ወይም የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ማስረጃ ማግኘት።

- አንድ ቨርቹዋል ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ።
- በድንገተኛ ጊዜ የመጀመሪያ እርዳታ፣ የልብና የደም ሥር ማስታገሻ (CPR) እና ካርዲዮፑልሙናሪ ሪሰሲቴሽን ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶችን በተግባር ላይ ማዋልን ጨምሮ በራስ-ሰር የውጭ ዲፊብሪላተሮች (AED) አጠቃቀም የሰለጠኑ መሆን።
- በቨርጂኒያ 5 C ውስጥ መሠረታዊ ችሎታዎችን ያገኙ እና ማሳየት፡ ጥልቅ አስተሳሰብ፣ ፈጠራዊ አስተሳሰብ፣ ትብብር፣ ግንኙነት እና ዜግነት።

| የትምህርቱ መስክ | የሚያስፈልግ ክሬዲት መደበኛ መለኪያ | የሚያስፈልግ የተረጋገጠ ክሬዲት አስፈላጊ |
|---|---|---|
| እንግሊዝኛ (ማንበብና መጻፍ) | 4 | 2 |
| ሒሳብ | 4 | 1 |
| ሳይንስ | 4 | 1 |
| ታሪክ እና ማህበራዊ ሳይንስ | 4 | 1 |
| የዓለም ቋንቋዎች | 3 | ይህንን መስፈርት ለማሟላት የሚረዱ ኮርሶች ሶስት ዓመት የአንድ ቋንቋ ወይም ሁለት ዓመት የሁለት ቋንቋዎች ትምህርትን ማካተት አለባቸው። |
| ጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት | 2 | |
| ስነ-ጥበብ ወይም የስራ ዘመን እና የቴክኒክ ትምህርት | 1 | |
| ኢኮኖሚክስ እና የግል ፋይናንስ | 1 | |
| በምርጫ የሚወሰዱ | 3 | ይህንን መስፈርት ለማሟላት የሚረዱ ኮርሶች ቢያንስ ሁለት ተከታታይ ተመራጮችን ያካትታሉ። የዓለም ቋንቋዎች ደረጃዎች 1 እና 2 እንደ ቅደም ተከተል ተመራጭ ሆነው እንዲያገለግሉ አይፈቀድላቸውም፣ ምክንያቱም የዓለም ቋንቋዎች የተለየ መስፈርት በመሆናቸው ነው። |
| አጠቃላይ | 26 | 5 |

የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በጾታዊ ዝንባሌ፣ በብሔር፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት፣ በእርግዝና፣ ወይም በጋብቻ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አድልዎ ይከለክላል። ይህ መመሪያ ለክፍለ-ትምህርቶች እና ለፕሮግራሞች፣ ለምክር አገልግሎቶች፣ ለአካል እንቅስቃሴ እና ለአትሌቲክስ ትምህርት፣ ለሙያ ትምህርት፣ ለትምህርታዊ ቁሳቁሶች እና ለተጨማሪ - ሥርዓተ-ትምህርት እንቅስቃሴዎች እኩል ተደራሽነትን ይሰጣል። የዚህ መመሪያ ጥሰቶች ለአስተዳደራዊ አገልግሎቶች ረዳት ዋና ተቆጣጣሪ በ (703) 228-6008 ወይም ለሠራተኛ ረዳት ተቆጣጣሪ በ (703) 228-6110 ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

Arlington
Public
Schools